2017

ሚያዝያ - ሰኔ

ቅጽ. 101፣ ቁጥር 2

የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት



ክፍል ሁለት

# ወንጌል እንደ ዮሐንስ መሠረት

መልካሙ እረኛ የሚመራውን መንጋውን በርኅራኄ ይጠብቃል።

የጎልማሶች የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች
ክፍል ሁለት

# ወንጌል እንደ ዮሐንስ መሠረት

*መልካሙ እረኛ የሚመራውን መንጋውን በርኅራኄ ይጠብቃል።*

**ሚያዝያ - ሰኔ 2017 ጥራዝ 101፣ ቁ. 2**

**ማውጫ**


1. የሱስ የሕይወት እንጀራ ........................................ 5
2. ቀውስ በገሊላ ........................................ 10
3. የሱስ በዳስ በዓል ........................................ 15
4. እንደዚህ ሰው ማንም ከቶ አልተናገረም .................... 20
5. “እኔም አልፈርድብሽም” ........................................ 26
6. የሱስ የዓለም ብርሃን ........................................ 31
7. ብርሃኑ ቾላ ተባለ ወይስ ተንጸባርቀ? ........................ 36
8. የሱስ እና አብርሃም ........................................ 41
9. የሱስ እና አይነ ስውሩ ሰው ........................................ 46
10. መንፈሳዊ እውርነትን መጋፈጥ ................................ 52
11. የሱስ፣ መልካም እረኛ ........................................ 57
12. የሱስ እና አልዓዛር ........................................ 62
13. ትንሣኤና ሕይወት ........................................ 67


*የሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ፣ የዕለት ተዕለት የጥናት መርሃ ግብር፣ ያለ ተጨማሪ አስተያየት በመጽሐፍ ቅዱስ እና በትንቢት መንፈስ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው። ጥቅሶቹ እጥር ምጥን እንዲሉ እና ቀጥተኛ ሀሳቦችን ለማቅረብ በተቻለ መጠን አጭር እንዲሆኑ ተደርገዋል። ቅንፎች [] ግልጽነትን፣ ትክክለኛ አውድ እና ምቹ ተነባቢነትን ለማረጋገጥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጨምሯል። ከምንጭ ላይ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ በጥብቅ ይመከራል።*


*ምሳሌዎች ፡ አዶቤ ስቶክ በገጽ.* 25፣ 72፤ *የካርታ መርጃዎች በገጽ* 4፣ 51፣ 72፤ *የፊት ሽፋን ላይ የስብከት እይታ*


*የቅጂ መብት* © 2025 *በሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ተሃድሶ እንቅስቃሴ አጠቃላይ ጉባኤ፣ የሰንበት ትምህርት ክፍል መምሪያ፣* 5240 *ሆሊንስ መንገድ፣ ሮአኖክ፣ ቨርጂኒያ* 24019፣ *አሜሪካ።*


**ስልክ፡** 1-540-362-1800 • **ድር፡** www.sdarm.org • **ኢ-ሜይል፡** info@sdarm.org

# መቅድም

እንደ ዮሐንስ የወንጌል አጻጻፍ ከሌሎቹ (ሲኖፕቲክ ወንጌሎች ከሚባሉት) ከሦስቱ ወንጌሎች ዘግየት ያለ ቢሆንም አሁንም ግን በ1ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነበር የተጻፈው። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ተቺዎች ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው የሚለውን እውነታ ለመቃወም ጥረት ሲያደርጉ፣ ከ150 ዓ.ም. በፊት መጻፉን ለመካድ ሞክረው ነበር። ተቺዎቹ የግኖስቲክ ፍልስፍናን እንደሚያንፀባርቅ እና ስለዚህ ግኖስቲሲዝም ለእምነት ከባድ ስጋት ከመሆኑ በፊት ሊጻፍ እንደማይችል ከሰሱ። (ግኖስቲሲዝም ከእምነት ይልቅ እውቀት ለመዳን ቁልፍ እንደሆነ በሚናገሩ የጥንት ኑፋቄዎች የፍልስፍና እና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነበር።) እንዲህ ያለው የተዛባ ክስ ውድቅ ተደርጓል።

በተቃራኒው፣ ውጫዊ መረጃዎች አራተኛው ወንጌል እንዳለ እና በ 115ኛው ዓ.ም፣ መጀመሪያ አከባቢ ይሰጠው የነበረውን ከፍተኛ ግምት እነደነበረ ይመሰክራል። ከእነዚህ ማስረጃዎች አንዱ ጥቂት የዮሐንስ ወንጌል ጥቅሶችን የያዘ ትንሽ የፓፒረስ (የጥንት ግብጻዊያን ወረቀት) ቁራጭ በተገኘበት ወቅት ነው። (ምዕራፍ 16፣ ቁጥር 31-33፣ 37፣ 38)፣ ራላንድስ ፓፒረስ (Rylands Papyrus) በመባል የሚታወቀው እና በተለምዶ P52 ተብሎ የተሰየመው፣ ይህ በፓሌኦግራፊያዊ (ስለጥንት ጽሑፎች በሚያጠና ሳይንስ) መረጃ መሠረት በ125ኛው ዓ. ም. አከባቢ የተጻፈ ማስረጃ ነበር። በ2ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በግብፅ የተገኘው ይህ ቁርጥራጭ፣ ለአራተኛው ወንጌል ጅማሮ እና መስፋፋት እንደ ተጨባጭ ማስረጃ ይቆጠራል። ይህንንም ታዋቂው የአዲስ ኪዳን ምሁር አዶልፍ ዴይስማን እንዲህ ሲል አረጋግጧል።

"የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው እጅግ በኋላ ነው የሚሉ ብዙ መላምቶች እንደ ሙቅ ቤት በፍጥነት ይደርቃሉ። የዮሐንስ ወንጌል በ2ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ የነበረ ብቻ ሳይሆን ቅጂዎቹ ግብፅ ድረስ የደረሱ ስለመሆኑ በራላንድ ፓፒረስ የተረጋገጠ ዘጋቢ ማስረጃ አለን። ስለዚህ የዚህ የወንጌል አመጣጥ መቼ ነበር የሚለውን ለመመለስ ወደ ቀደመው ዘመን መመለስ አስፈላጊ ነው።"—Deutsche Allgemeine Zeitung, Dec. 3, 1935.

የዮሐንስ ጽሕፈት በጥንቶቹ ክርስቲያኖች መካከል የተለየ ዓላማ ያለው ብቻ ሳይሆን፤ ከዘመናት ጀምሮ፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ለክርስቶስ ተከታዮች መንፈሳዊ መመሪያን፣ እርዳታንና ማበረታቻን ያመጣ ነው።

ጌታ "ለእኛ አዲስ የሆነ ብርሃን አለው፣ ይህም ደግሞ ከእውነት ቃል የሚወጣ የከበረ አሮጌ ብርሃን አካል ነው። እኛ ገና ወደ እኛ የሚመጡት የብርሃን ጨረሮች ብልጭታዎች ብቻ እያየን ነው። ጌታ ቀድሞ የሰጠንን ብርሃን በአግባቡ እየተጠቀምን አይደለም፣ እና በዚህም ተጨማሪ ብርሃን ለመቀበል ተሰናናል፤ በላያችን በበራው ብርሃን አልሄድንምና።


"እኛ እራሳችንን የሕጉ ጠባቂ ሕዝቦች ብለን እንጠራለን፣ ነገር ግን እጅግ ሰፊ የሆነውን የእግዚአብሔር ህግ መርሆዎችን አንረዳም። ቅዱስ ባህሪውን አንረዳም። የእውነት አስተማሪዎች ነን የሚሉ ብዙ ሰዎች ስለ ጌታ የሱስ ክርስቶስ ሕያው እውቀት ስለሌላቸው የአምላክን ሕግ በማስተማር ረገድ ስለሚያደርጉት ነገር ትክክለኛ ግንዛቤ የላቸውም።"—Selected Messages, bk. 1, pp. 401, 402.

የዚህ ወንጌል ቀጣይ ጥናት የሱስን የበለጠ እንድናውቀው ይርዳን!

የጄነራል ኮንፈረንስ ሰንበት ትምህርት ክፍል

## የመጀመሪያ ሰንበት መባ

## ሰንበት፣ መጋቢት 27፣ 2017




# በፕሮክሆሮቭካ፣ ሩሲያ ውስጥ ያለውን ቤተ ክርስቲያን እንደገና ለመገንባት



ሩሲያ በቆዳ ስፋት 6,612,073.2 ስኩዌር ማይል (17,125,191 ኪ.ሜ²) የሚሸፍን ሲሆን 147,000,000 ህዝብ አላት። ከ180 የሚበልጡ ብሔረሰቦች የተውጣጡ ሰዎች በዚህ ሰፊ ሀገር ውስጥ ይኖራሉ፣ ደግሞ ብዙ የተለያየ ሃይማኖትም አላቸው። ከነዚህ ኃይማኖቶች መካከል በጣም ታዋቂው የሩሲያ ኦርቶዶክስ (41.1%) ፣ ሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች (6.3%) ፣ እስላም (6.5%) ፣ ኒዮፓጋን እና ቴንግሪስት (1.2%) ፣ ቡዲዝም (1.2%) ፣ አማኞች ያልሆኑ (25.2%) ፣ አምላክ የለሽ (13%)፣ የተቀሩት ምንም ዓይነት ሃይማኖት የላቸውም።

ከኤስዲአርም መጀመሪያ ጀምሮ፣ የዘላለም ወንጌል መልእክት በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እዚህ አልፏል። ብዙ አማኞች ከባድ ስደት ደርሶባቸዋል—እንዲሁም አንዳንዶቹ ለተሰቀለውና ከሙታን ለተነሳው አዳኝ የህይወት መስዋዕትነትም ከፍለው መስክረዋል።

በ1990ዎቹ መጨረሻ ላይ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሠራተኛ ከሚስቱ ጋር የሚስዮናዊነት ሥራ ለመፈጸም ወደ መካከለኛው ሩሲያ ሄደ። ከጥረታቸውና ከጸሎታቸው የተነሣ የምእመናን ቡድን ተደራጀ። ግን ለስብሰባና ለአምልኮ ቦታ አልነበራቸውም። በመጨረሻም በ 2006 በቤልጎሮድ ክልል የፕሮኮሆሮቭስኪ አውራጃ የከተማ አስተዳደር ማዕከል በሆነውና ሰፊ የብረት ማዕድን ክምችቶች ካላት ከኩርስክ ከተማ በስተደቡብ ምሥራቅ - በፕሶል ወንዝ አጠገብ፤ እህል፣ ቀይስር፣ የሱፍ አበባ እና ፍራፍሬ የሚመመረትበት አከባቢ በሆነዉ በፕሮኮሆሮቭካ ውስጥ አንድ ትንሽ ቤት ያለበት ቁራጭ መሬት አገኙ።

ብዙ መሰናክሎችን በተአምር አስወግዶ የዚህን ቤት ግዢ ሲባርክ የእግዚአብሔርን እጅ ከእኛ ጋር ሲሰራ አይተናል። በዚህ ክልል ውስጥ ያለው ሥራ እድገቱን የቀጠለ ሲሆን ብዙም ሳይቆይ ቤቱ በጣም ትንሽ በመሆኑ ሁሉንም የእግዚአብሔርን አምላኪዎች ለመያዝ በቂ ሊሆን አልቻለም። ከጥቂት ዓመታት በፊት ከባለሥልጣናት ፈቃድ አግኝተን የ አምልኮ ቤት መገንባት ጀመርን። ወንድሞች መዋጮ አድርገዋል እንዲሁም ጠንክረው ሠርተዋል፣ ነገር ግን ይህንን ፕሮጀክት ለመጨረስ ጌታን የሚወዱ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ልግስና እርዳታ እንፈልጋለን። የዚህ ፕሮጀክት መጠናቀቅ በአጎራባች ክልሎች የወንጌል ስራን የበለጠ ለማዳረስ እድል ይሰጣል፣ ይህም የመጨረሻውን የድነት መልእክት ለማሰራጨት የብርሃን ማማ ይሆናል። በዚህ የአለም ክፍል ያለውን እውነትን ማዳረስ ሥራ ለመርዳት ልቡ ዝግጁ የሆነውን እያንዳንዱን ሰዉ ጌታ ይባርክ!

ከፕሮክሆሮቭካ ቤተክርስትያን እና ከሩሲያ ዩኒየን

ሰንበት፣ ኤፕሪል 5፣ 2025 **1ኛ ትምህርት**

# የሱስ የሕይወት እንጀራ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “የሱስም እንዲህ አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።” (ዮሐ. 6፡35)**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Thoughts From the Mount of Blessing, **pp. 18–21.**

*“የክርስቶስን ሥጋ መብላት ማለት. . . በእምነት እርሱን አዳኛችን አድርገን መያዝ ማለት ነው።”*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, p. 1135.

## 1. ታላቅ ቅንዓት — እሁድ፣ መጋቢት 21

### ሀ. ከእንጀራው ተአምር በኋላ ብዙ ሰዎች ምን ብለው አመኑ? ዮሐንስ 6፡14 ምን ለማድረግስ ጓጉተው ነበር? ዮሐንስ 6፡15 (የመጀመሪያ ክፍል)።

*“ይህ እምነታቸው ቀኑን ሙሉ ከሰዓት ወደ ሰዓት እየበረታ መጣ። የሱስ የሠራው ታላቅ ተአምር ለረጅም ዘመን ሲጠበቅ የነበረው ነጻ አውጪ ንጉሥ በመካከላቸው እንዳለ አረጋገጠላቸው። የሰዎቹ ተስፋ ከሰዓት ወደ ሰዓት እየተጠናከረ መጣ። ይሁዳን ማርና ወተት እንደ ውሃ የሚፈስባት ምድራዊ የተድላ ገነት የሚያደርጋት ይህ ሰው ነው አሉ። ማንኛውንም ሰብአዊ ፍላጎት ያሟላል። የተጠሉትን የሮማውያንን ኃይል ያንኮታኩታል። ይሁዳንና የሩሳሌምን ነጻ ያወጣል። በጦር ሜዳ የሚቆስሉትን ወታደሮች መፈወስ ይችላል። መላውን የጦር ሠራዊትም መመገብ ይችላል። ነገሥታትን ሁሉ አንበርክኮ ለእሥራኤል ሲጠበቅ የኖረውን የግዛት ሥልጣን ሊያስገኝ ይችላል።*

*“ከመጓጓታቸው ብዛት የተነሳ ሕዝቡ ወዲያውኑ ሊያነግሡት ዝግጁ ነበሩ። ለራሱ ክብር ለማግኘትና የሕዝብን አስተሳሰብ ለመሳብ ምንም ጥረት እንደማያደርግ ተረዱ። ይህን በተመለከተ ከቀሳውስቱና ከመኳንንቱ የተለየ ስለነበረ የዳዊት ዙፋን ይገባኛል ብሎ አይታገልም ይሆናል የሚል ስጋት ነበረባቸው። እርስ በእርሳቸው ከተመካከሩ በኋላ በኃይል የእሥራኤል ንጉሥ አድርገው ሊሰይሙት ተስማሙ። ደቀ መዛሙርቱም መሪያቸው የዳዊት ዙፋን ሕጋዊ ወራሽ ስለመሆኑ ከሕዝቡ ጋር ተስማሙ። ይህን ዓይነት ክብር ከመቀበል እንዲያፈገፍግ የሚያደርገው ትሕትናው ነው ብለው አሰቡ። ስለዚህ ሕዝቡ ራሳቸው ነጻ አውጪቸውን ከፍ ከፍ ማድረግ ነበረባቸው። እነዚያ እብሪተኛ ካህናትና መኳንንት ሳይወዱ በግድ ይህን የእግዚአብሔርን ሥልጣን ተጐናጽፎ የመጣውን ሰው እንዲያከብሩ መሆን አለባቸው።”*—The Desire of Ages, pp. 377, 378.

## ሀ. የሱስ ሕዝቡና ደቀ መዛሙርቱ እርሱን በምድራዊ ዙፋን ላይ የማስቀመጥ ዕቅዳቸውን እንዳይፈጽሙ ለመከላከል ምን አደረገ? ዮሐንስ 6፡15

"[ደቀ መዛሙርቱና ሕዝቡ] ዕቅዳቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በጉጉት አመቻቹ፣ የሱስ ግን ይካሔድ የነበረውን እንቅስቃሴ በማየት ለእነርሱ ያልተከሰተላቸው የዚያ እንቅስቃሴ ውጤት ምን እንደሚሆን አስተዋለ። በዚያን ወቅት ካህናቱና መኳንንቱ ሕይወቱን ለማጥፋት በማደን ላይ ነበሩ። ሕዝቡን ከእኛ እንዲሸሹ አድርጎአል የሚል ክስ መሠረቱበት። እርሱን በዙፋን ላይ ለማስቀመጥ በሚደረግ ጥረት ሁከትና ብጥብጥ መከተሉ የማይቀር ነበር፤ ይህ ከሆነም የመንፈሳዊዩ መንግሥት ሥራ መተጓጐሉ ነበር። ስለዚህ ያ እንቅስቃሴ ወዲያው መገታት ነበረበት። የሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠራና እርሱ ሕዝቡን ለማሰናበት ወደኋላ እንደሚቀር ጠቅሶ እነርሱ ግን ጀልባቸውን ይዘው ወዲያውኑ ወደ ቅፍርናሆም እንዲመለሱ አዘዛቸው።

"ከዚያ በፊት የሱስ እንደዚህ ለመፈጸም የሚከብድ ትእዛዝ ሰጥቶአቸው አያውቅም። ደቀ መዛሙርቱ የሱስን እንዲነግሥ የሚያደርግ እንደዚህ ያለ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲነሳ ለብዙ ጊዜ ይመኙ ስለነበር ለዚሁ ተግባርበሕዝቡ መካከል ይታይ የነበረው ጉጉት ከንቱ ይቅር የሚለውን አስተሳሰብ መቀበል አልቻሉም። ለፋሲካ በዓል የተሰበሰቡት ሳዎች አዲሱን ነቢይለማየት ጓጉተው ነበር። የየሱስ ተከታዮች ተወዳጁን ጌታቸውን በእሥራኤል ዙፋን ላይ ለማስቀመጥ አመቺው ወቅት ያንጊዜ መሰላቸው። ምኞታቸው እንደዚያ ተፋፍሞ እያለ የሱስን በምድረ በዳ ላይ ትተው መሔድ ከበዳቸው። ስለዚህ አሳቡን ተቃወሙ፣ የሱስ ግን ከዚያ በፊት በእነርሱ ላይአድርጎት የማያውቀውን በሥልጣን መንፈሱ ተናገራቸው። ከዚያ በኋላ ተቃውሞ ማቅረብ ፋይዳ እንደሌለው በማወቅ ጸጥ ብለው ወደ ባሕሩ ተመለሱ።"—The Desire of Ages, p. 378.

## ለ. ተአምሩ በተፈጸመ ማግስት ህዝቡ ምን አደረጉ? ዮሐንስ 6፡ 22-25

"የእንጀራው ተአምር ወራ በሩቅና በቅርብ ስለተሰራጨ ገና በጥዋት ብዙ ሰዎች የሱስን ለማየት ወደ ቤተሳይዳ ተጓዙ። ቁጥራቸው ብዙ የሆነ ሰዎች በየብስና በባሕር ላይ ተጉዘው መጡ። ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላው የባሕርዳርቻ የሚወስደው ጀልባ እንዳልነበረ በማወቅ ባለፈው ምሽት ከተሰናበቱት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ተአምሩን ከሠራበት ቦታ እናገኘዋለን በማለት ተመልሰው ሔዱ። ከዚያ ሊያገኙት ስላልቻሉ ብዙዎች እርሱን ፍለጋ ወደ ቅፍርናሆም ሔዱ።

ከአንድ ቀን በኋላ የሱስ ጌንሳሬጥ ደረሰ። ከዚያ መድረሱን እንዳወቁ ብዙ ሰዎች «በዚያ አገር ዙሪያ እየተራወጡ ኢየሱስ ወዳለበት ሥፍራ ሁሉ በሽተኞችን በአልጋ ተሸክመው ያመጡ ጀመር።» ማር. 6:55።"—Ibid., pp. 383, 384.

## ሀ. የሱስ ለሕዝቡ ምን ግልጽ ሆኖም ትኩረት የሚስብ መልእክት ነገራቸው? ዮሐንስ 6:26፣ 27

"የሱስ የሰዎቹን የማወቅ ፍላጐት ለማርካት አልሞከረም። እያዘነ «እናንተ" የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ ነው እንጂ ተአምር ስላያችሁ አይደለም፣» አላቸው። እርሱን የፈለጉት ለተከበረ ዓላማ ሳይሆን እንጀራ እንደተመገቡ ሁሉ ወደ እርሱ በመጠጋት ሌላ ሥጋዊ ጥቅም እናገኛለን በሚል ተስፋ ነው። በተጨማሪም አዳኛችን «ለሚጠፋ ምግብ አትሥሩ፣ ይልቅስ የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ የዘላለም ሕይወት ለሚሆን ምግብ ሥሩ፣» አላቸው። ሥጋዊ ጥቅም ብቻ አትፈልጉ። ዋና ጥረታችሁ መሆን ያለበት ለአሁኑ ሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት ሳይሆን መንፈሳዊ ምግብን ለመመገብና ወደዘላለም ሕይወት የሚቀጥለውን ጥበብ ለመቅሰም ነው።"—The Desire of Ages, p. 384.

## ለ. አይሁድ የእግዚአብሔርን ሥራ በተመለከተ የሱስን ምን ጥያቄ ጠየቁት? ዮሐንስ 6፡28 ጌታ የሰጠውን ምላሽ አብራራ። ዮሐንስ 6፡ 29

"ለጊዜው የሕዝቡ ስሜት ተቀሰቀሰና «ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ ይገባናል?» ብለው ጠየቁት። በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ ብዙ ከባድ ሥራዎችን ሲሠሩ ኖረዋል፣ አሁን ደግሞ የበለጠ ብቁ ሆኖ ለመገኘት አዲስ የአገልግሎት ሥርዓት ካለ ለመስማት ዝግጁ ነበሩ። የጥያቄአቸው መንፈስ ሰማይ ለእኛ ይገባን ዘንድ ምን እናድርግ የሚል ነው። የሚመጣውን ሕይወት ለማግኘት መክፈል ያለብን ዋጋ ስንት ነው?

"የሱስም የእግዚአብሔር ሥራማ እግዚአብሔር በላከው ማመን ነው ሲል መለሰላቸው። የሰማይ ዋጋ የሱስ ነው። ወደ ሰማይ የሚያደርሰው መንገድ «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፣» በሆነው ማመን ነው። ዮሐ.1:29።"—Ibid., p. 385.

"ንስሐ ከራስ ወደ ክርስቶስ መመለስ ማለት ነው፤ ክርስቶስን በመቀበል በእምነት እሱ ሕይወቱን በእኛ እንዲኖር መፍቀድ ሲሆን ይህም በመልካም ሥራዎች ይገለጣል።"—Thoughts From the Mount of Blessing, p. 87.

"ጌታ ህዝቡ ሊሰራው የሚገባ ልባዊ ስራ እንዳለ እንዲገነዘቡ ይርዳቸው። . . . በቤት፣ በቤተክርስቲያን እና በአለም ውስጥ የክርስቶስን ስራ መስራት አለባቸው። በርግጥም ብቻቸውን እንዲደክሙ አይተውም። መላእክት ረዳቶቻቸው ናቸው። ክርስቶስም ረዳታቸው ነውና።"—Testimonies for the Church, vol. 8, p. 18.

## ሀ. አይሁዶች ምን ምልክት ፈለጉ እና የትኛውን ታሪካዊ እውነታ ጠቀሱ? ዮሐንስ 6:30፣ 31 የሱስ ከሰማይ ስለመጣው እንጀራ ምን አለ? ዮሐንስ 6:32፣ 33

"አይሁዶች መናን የሰጠ እርሱ ነው በማለት ድርጊቱን የፈጸመውን ጌታ ረስተው መሣሪያ የሆነውን ሙሴን ያከብሩት ነበር። አባቶቻቸው በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፣ መለኮታዊ ተልዕኮውንም ተጠራጠሩ፣ ካዱትም። አሁንም ልጆቻቸው በዚያው መንፈስ የእግዚአብሔርን መልእክት ያመጣላቸውን ጌታ ናቁት። «በዚህ ጊዜ የሱስ እንዲህ አላቸው። ከሰማይ የወረደውን እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም።» መናውን የሰጣቸው ከመካከላቸው ቆሞ ነበር። ዕብራውያንን በምድረ በዳ የመራቸውና በየቀኑ ከሰማይ በወረደ ምግብ የመገባቸው ራሱ ክርስቶስ ነበር። ያ ምግብ የእውነተኛው ሰማያዊ ምግብ ምሳሌ ነበር። እውነተኛው መና ወሰን ከሌለው ከእግዚአብሔር ፍጹምነት የሚፈልቀው ሕይወት ሰጪ መንፈስ ነው።"—The Desire of Ages, pp. 385, 386.

## ለ. አእምሯቸው በተፈጥሯዊ፣ በሚታየው እንጀራ ላይ ብቻ በማተኮር ምን ልመና አቀረቡ—ጌታስ ምን ገለጸላቸው? ዮሐንስ 6፡34-36

"የሱስ የተጠቀመበት የንግግር ዘይቤ በአይሁዶች ዘንድ የተለመደ ነበር። ሙሴ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ «ሰው ሕይወቱ ተጠብቆ መኖር የሚችለው እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አለመሆኑን ሊያስተምርህ ነው» ብሎአል። ነቢዩ ኤርምያስም «ቃልህ ወደ እኔ እኔ በመጣ ጊዜ በላሁት፣ ልቤንም በደስታና በሐሴት ሞላው፣» ሲል ጽፎአል። ዘዳ.8:3፤ ኤር.15:16። ራሳቸው የአይሁድ ምሑራን እንጀራ መመገብ መንፈሳዊ ትርጉሙ ሕግን ማጥናትና ጥሩ ሥራ መለማመድ" እንደሆነና መሲሑ ሲመጣ ሕዝበ እሥራኤል በሙሉ እንደሚመገቡ ይናገሩ ነበር። የነቢያት ትምህርት ከእንጀራው ተአምር የሚገኘውን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርት ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል። የሱስ በምኩራቡ ሲያዳምጡት ለነበሩት ሰዎች ግልጽ ለማድረግ የፈለገው ይህን ትምህርት ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ተረድተው ቢሆን ኖሮ የሱስ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣» ያለውን ማስተዋል ይችሉ ነበር። ያ ሁሉ ሕዝብ የሱስ የሰጣቸውን ምግብ የበሉት ባለፈው ቀን ነበር። ከዚያ ምግብ ሥጋዊ ብርታትና ተሐድሶ እንዳገኙት ሁሉ እንደዚሁም ከክርስቶስ ለዘላለም ሕይወት የሚሆን መንፈሳዊ ብርታት ማግኘት ይችሉ ነበር።"—Ibid., p. 386.

## ሀ. ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር አንድ ለሚያደርጉ ምን ሁለት ተዛማጅ ተስፋዎች ተሰጥተዋል—ይህስ ለእያንዳንዱ ኃጢአተኛ ተስፋ የሚያመጣው እንዴት ነው? ዮሐንስ 6፡37-40

"[የሱስ] እርሱን በእምነት የተቀበሉት ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸው እንጂ አንድም እንኳ እንዳይጠፋ ቃል ገብቷል።"—The Desire of Ages, p. 387.

"ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ብቁ እስክትሆን ድረስ ራስህን እስክትሻሽል ድረስ ከክርስቶስ እንድትርቅ የሚናገረውን የጠላትን ምክር አትስማ። እንደዚያ እስክትሆን ድረስ ከጠበቅህ፣ በጭራሽ አትመጣም። ሰይጣን ወደ ቆሻሻ ልብስህ ሲጠቁም፣ 'ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም' የሚለውን የየሱስን ተስፋ ደግመህ (ዮሐንስ 6፡37) አስታውስ። የየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻ ለጠላት ንገረው። "እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ"፤ የሚለውን የዳዊትን ጸሎት የራስህ አድርግ። መዝሙረ ዳዊት 51:7

"ተነሥተህ ወደ አባትህ ሂድ። ገና በጣም ሩቅ ሳለህ እሱ ወጥቶ ይቀበልሃል። በንስሐ ወደ እርሱ አንድ እርምጃ እንኳን ከቀረብክ፣ እርሱ ወሰን በሌለው ፍቅር እቅፍ ውስጥ ሊያስገባህ ይቸኩላል። ለተጸጸተች ነፍስ ጩኸት ጆሮው ክፍት ነው። እግዚአብሔር የመፈለግ የልብ መነካት ገና ጅማሮ ላይ እንኳ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነውና። ማንኛውም ከምንቀጠቀጥ ከንፈር እንኳን ቢሆንም የወጣ ጸሎት፣ ማንኛውም በሚስጥር የፈሰሰ እንባ፣ ማንኛውም በፍጹም ቅን ልብ እግዚአብሔርን የመፈለግ ጥያቄ፣ ምንም ያህል ደካማ ቢሆኑም፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ግን እነዚህን ጥያቄዎች ለመቀበል ሊገናኘው ይወጣል። ጸሎቱ ከመቅረቡ ወይም የልብ መሻት ከመገለጹ በፊትም እንኳ የክርስቶስ ጸጋ በሰው ነፍስ ላይ የሚሠራውን ጸጋ ለማግኘት ይወጣል።"—Christ's Object Lessons, pp. 205, 206.

## ለ. የማያምኑት አይሁዶች ምን አጉረመረሙ እና የሱስ በእርሱ ለሚያምኑት ምን ተስፋ ደግሞ ሰጣቸው? ዮሐንስ 6፡41–51



1. ከእንጀራው ተአምር በኋላ የክርስቶስ ተከታዮች ምን ለማድረግ አስበው ነበር?
2. የሱስን እየተከተሉ ያሉት የብዙዎች ፍላጎት ምን እንደሆነ ግለጽ።
3. በዮሐንስ 6:29 ያለውን የየሱስን ቃል አብራራ።
4. ክርስቶስ የመንፈሳዊ ሕይወትን ምንጭ ለማመልከት የተጠቀመው ምሳሌ ምንድን ነው?
5. የአይሁድ መሪዎች ለክርስቶስ ያላቸውን ጭፍን ጥላቻ ያሳዩት እንዴት ነው?

# ቀውስ በገሊላ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።" (ዮሐንስ 6፡53)**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 5, pp. 573–580**

"ብቸኛው አስፈላጊ እምነት እውነትን የሚቀበል እና እምነት የህይወትና የተግባር አካል እንዲሁም ተነሳሽነት ሃይል እስከሆን ድረስ የሚያዋህደው ነው።"—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 576

## 1. ሕይወት በክርስቶስ ሥጋ እና ደም ውስጥ — እሁድ፣ መጋቢት 28

### ሀ. የክርስቶስ ቃላት በሃይማኖት መሪዎቹ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳድረዋል? ዮሐንስ 6፡52 ስለ ሥጋውና ደሙ እሱ ምን አስረዳቸው? ዮሐንስ 6፡53-55

"ምሑራት በቁጣ «ይህ ሰው ሥጋውን እንድንበላ እንዴት ሊሰጠን ይችላል?» ሲሉ ጮኹ። ኒቆዲሞስ «ታዲያ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል?» ብሎ እንደጠየቀ እነዚህ ምሑራንም የየሱስን ንግግርበጥሬ ንባቡ የተረዱት ለመምሰል ሞከሩ። ዮሐ.3:4። በመጠኑም ቢሆን የየሱስ ትርጉም ገብቷቸው ነበር። ነገር ግን ያ እንዲታወቅባቸው አልፈ ለጉም። ለተናገራቸው ቃላት ልዩ ትርጉም በመስጠት በእርሱ ላይ የሕዝቡን ጥላቻ ለመቀስቀስ ተመኙ።"—The Desire of Ages, p. 389.

### ለ. የእግዚአብሔርን ልጅ ሥጋ መብላትና ደሙን መጠጣት ማለት ምን ማለት ነው? ዮሐንስ 6:56፣ 57፤ 1ኛ ዮሐንስ 3:24፤ 5፡12።

"የየሱስን ሥጋ መብላትና ደሙንም መጠጣት ማለት እርሱን የግል አዳኝ አድርጐ መቀበልና ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚልልንና በእርሱ የተሟላን እንደምንሆን ማመን ማለት ነው። የእርሱ ባሕርይ ተሳታፊ የምንሆነው የእርሱን ፍቅር ስናይ፣ ስለ ፍቅሩ ያለ መታከት ስናስብና ፍቅሩን እንደ ውሃ ስንጠጣው ነው። ምግብ ለሥጋዊ አካላችን እንደሚያስፈልግ ሁሉ እንደዚሁም ክርስቶስ ለነፍሳችን አስፈላጊ ነው።"—Ibid., p. 389.

## ሀ. የሱስ የተናገራቸውን ቃላት ትርጉም ይበልጥ ግልጽ ያደረገው በምን ተጨማሪ ማብራሪያ ነው? ዮሐንስ 6፡63

*"እንደዚሁም ክርስቶስ ለነፍሳችን አስፈላጊ ነው። ምግብ ካልተበላና ከሰውነት ጋር ካልተዋሐደ የሚሰጠው ጥቅም የለም። እንደዚሁም ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን ካላወቅነው አይጠቅመንም። በተግባር የማይተረጐም የቲዮሪ እውቀትም ፋይዳ የለውም። የእርሱ ሕይወት የእኛ እንዲሆን ከፈለግን በልባችን ልንቀበለውና እንደ እህል ልንመገበው ይገባናል። ፍቅሩና ጸጋው ሊዋሐደን ይገባል። ...*

*"ለዓለም ሕይወትን የሚሰጠው የክርስቶስ ሕይወት የሚገኘው ከቃሉ ነው። የሱስ ሕሙማንን የፈወሰውና አጋንንትን ያስወጣው በቃሉ ነው። በቃሉም ባሕሩን ጸጥ እንዲል አደረገ፣ ሙታንንም አስነሳ። ቃሉ ኃይል እንዳለው ሕዝቡ የዓይን ምስክር ነበሩ። የሱስ በብሉይ ኪዳን በነቢያትና በመምህራን አማካይነት እንደተናገረው አሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ተናገረ። መላው መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ መግለጫ ነው፣ ስለሆነም አዳኛችን የተከታዮቹን እምነት በቃሉ ላይ ለመመሥረት ፈለገ። እርሱ በሥጋ በሚለያቸው ጊዜ የኃይላቸው ምንጭ የሚሆነው ቃሉ ነው። የሚኖሩት እንደ ጌታቸው «እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ» ነው። ማቴ.* 4:4።

*"ሥጋዊ ሕይወታችን የሚኖረው በምግብ ኃይል እንደሆነ ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታችንም የሚኖረው በእግዚአብሔር ቃል ነው። እያንዳንዱ ሰው በግሉ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ቃል ማግኘት አለበት። ከምግብ የሚገኘውን ድጋፍ ለማግኘት እያንዳንዳችን በግላችን መመገብ እንዳለብን ሁሉ ልክ በዚያው ዓይነት የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ አለብን። ቃሉን በሌላ ሰው አማካይነት ብቻ ማግኘት የለብንም። ቃሉን ለማስተዋል እንድንችል የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ ለማግኘት እግዚአብሔርን እየጠየቅን መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማጥናት ይገባናል። አንድን ጥቅስ ወስደን በዚያ ጥቅስ እግዚአብሔር ለእኛ ያስቀመጠልን ሐሳብ ምን እንደሆነ በትክክል ለማረጋገጥ አእምሮአችንን በጥቅሱ ላይ እንዲያተኩር አድርገን መመርመር አለብን። እግዚአብሔር ምን እንዳለ እስክናውቅና ሐሳቡ የእኛ እስኪሆን ድረስ መመርመር አለብን።"*—The Desire of Ages, pp. 389, 390.

## ለ. ነቢዩ ኤርምያስ ይህን ሁኔታ የገለጸው እንዴት ነው? ኤርምያስ 15:16

*"እግዚአብሔርን እንደቃሉ ከተቀበልን ማዳኑን እናያለን። . . . የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል አለብን። ቃሉን መብላት አለብን፣ በቃሉ እንኑር፤ እግዚአብሔር ልጅ ሥጋና ደም ይህ ነውና። ሥጋውን በመብላትና ደሙን በመጠጣት - በእምነት የእርሱን መንፈሳዊ ባሕርያት እንቀበላለን።"*—Testimonies for the Church, vol. 6, pp. 51, 52.

## ሀ. የክርስቶስ ቃላት በራሱ ደቀ መዛሙርት መካከል ምን ቀውስ አስነስተዋል — ይህስ ዛሬ ለእኛ ማስጠንቀቂያ የሚሆነው እንዴት ነው? ዮሐንስ 6:60፣ 61፣ 65፣ 66

*"ፈተናው በጣም ከባድ ነበር። በኃይል ሊያነግሡት የነበሩት ሰዎች ጉጉት እየቀዘቀዘ ሔደ። በምኩራቡ ያደረገው ንግግር ዓይናችንን ከፈተልን አሉ። አሁን አልተታለሉም። በእነርሱ አስተሳሰብ ከዚያ ያደረገው ንግግር መሲሕ ላለመሆኑ ቀጥተኛ ኑዛዜ ነበር። ስለዚህ ከእርሱ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ዓለማዊ ጥቅም እንደማያገኙ ገባቸው። ተአምር ሠሪ ኃይሉን ተቀበሉ፣ ከበሽታና ከስቃይ ነጻ የመውጣት ፍላጐትም ነበራቸው፣ ነገር ግን ራስን የመሠዋት ሕይወቱን ሊቀበሉ አልፈለጉም። ስለተናገረው ምስጢራዊይና መንፈሳዊ መንግሥት ደንታ አልነበራቸውም። እርሱን ይሹ የነበሩት ሐቀኛ ያልነበሩትና ራሳቸውን ወዳጆች ከዚያ በኋላ አልፈለጉትም። የነበረውን ኃይልና ታዋቂነት በመጠቀም እነርሱን ከሮማውያን ጭቀና ነጻ የማያወጣቸው ከሆነ ከእርሱ ጋር የነበራቸው ግንኙነት አከተመ።* …

*በእውነት ቃል ገለባው ከስንዴው ተለየ። ብዙዎቹ ከየሱስ የተለዩበት ምክንያት ግብዞችና ራሳቸውን ጻድቃን አድርገው የሚቀጥሩ ስለነበሩ ተግሳጽን መቀበል ስለማይችሉና ዓለምን አፍቃሪዎች ስለነበሩም የትሕትና ኑሮ መኖር ስለማይችሉ ነው። ዛሬም ብዙ ሰዎች ይህንኑ ነገር ያደርጋሉ። በቅፍርናሆም ምኩራብ ውስጥ እንደተደረገው ሁሉ እንዲሁም ዛሬ ነፍሳት ይፈተናሉ። እውነቱ ወደ ልባቸው ሲደርስ አንዳንድ ነፍሳት ሕይወታቸው የእግዚአብሔርን መንገድ ያልተከተለ መሆኑ ይታያቸዋል። ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ መለወጥ እንዳለባቸው ይገባቸዋል፣ ነገር ግን ራስን የመካድ እርምጃን ለመውሰድ ፈቃደኛ አይሆኑም። ስለዚህ ኃጢአታቸው ይፋ ሲወጣባቸው ይቆጣሉ። የየሱስ ደቀ መዛሙርት «ይህ ንግግር ከባድ ነው፣ ማን ሊቀበለው ይችላል?» እያሉ በማጉረምረም እንደተለዩት እነዚህም አኩርፈው ይሔዳሉ።"*—The Desire of Ages, pp. 391, 392.

## ለ. እነዚያ ደቀ መዛሙርት ትተውት ከሄዱ በኋላ፣ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ምን ጠየቃቸው? ዮሐንስ 6፡67 በዛሬው ጊዜ የጴጥሮስን ጥበብ የተሞላበት ምላሽ እንዴት ማስተጋባት እንችላለን? ዮሐንስ 6:68፣ 69

*"በመልካም እና በመጥፎ ዘገባዎች፣ በጨለማ ኃይላትና በሁሉም የሰይጣን ወኪሎች መካከል፣ የጽድቅ ፀሀይ፣ ክፋትን እያጸዳች፣ ኃጢአትን እየገፋች፣ እና የተዋረዱና የተጸጸቱትን መንፈስ እያነቃቃች በእርጋታ ታበራለች። ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ።"*—Testimonies to Ministers, p. 285.

## ሀ. ከክርስቶስ መንገድ ወደኋላ የተመለሱትን በተመለከተ በአጠቃላይ ምን ማለት እንችላለን? 1ኛ ዮሐንስ 2፡19 ቅር የተሰኙት ደቀ መዛሙርት ምን አሳዛኝ አቋም ወሰዱ?

"እነዚያ ቅሬታ የተሰማቸው ሰዎች ከየሱስ እንደተለዩ በልዩ መንፈስ ቁጥጥር ሥር ሆኑ። እነዚህ ሰዎች የሱስን በአንድ ወቅት በጣም ያደንቁት ነበር። አሁን ግን ምንም ነገር ወደ እርሱ የሚስባቸው ጠፋ። እነዚህ ሰዎች ከየሱስ ጠላቶች ጋር የመንፈስና የተግባር አንድነት ስለነበራቸው እነዚያን ሰዎች ለመፈለግ ሔዱ። የተናገራቸውን ቃላት አጣመው ተረጐሙ፣ ንግግሩን ውሸት አስመሰሉ፣ አስተሳሰቡ ሁሉ በጥርጣሬ ላይ እንዲወድቅ ለማድረግ ሞከሩ። እርሱን ለመጉዳት ይጠቅማል ያሉትን ነገር ሁሉ አሰባሰቡ፣ ሕይወቱ በአስጊ ሁኔታ ላይ እንዳለ አድረገው ያሰራጩት የሐሰት ወሬ የቁጣ መንፈስ ቀሰቀሰ።"—The Desire of Ages, pp. 392, 393.

## ለ. ሥጋዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰሚዎች ምን ይሆናሉ? ሮሜ 16:17፣ 18

"ምስጋናና ከንቱ ውዳሴ ያስደስታቸዋል፣ እውነተን ግን ስለማይቀበሉ ሊሰሙት አይችሉም። ሕዝቡ በብዛት ሲጐርፍ ሲመገብና የድል ጩኸት ሲያስተጋባ የእነርሱ ድምጽ ጐልቶ ይሰማል፣ ነገር ግን በእግዚአብሔርመንፈስ መርማሪነት ኀጢአታቸው ሲገለጽና ያን ኀጢአት እንዲተው ሲነገራቸው ፊታቸውን ከእውነት ይመልሱና ከየሱስ ጋር አብሮ መሔዱን ይተውታል።"—Ibid., p. 392.

## ሐ. የሱስን ጥለው ከሄዱት በተጨማሪ ከጠላቶቹ ጋር ሕብረት ያደረገው ማን ነው —ይህስ የግማሽ ልብ ታማኝነት እንዴት ተገለጸ? ዮሐንስ 6:70፣ 71

"የሱስ በምኩራብ ውስጥ ስለ ሕይወት እንጀራ ያስተማረው ትምህርት በይሁዳ የሕይወት ታሪክ የወሳኝነት ሚና ነበረው። ይሁዳ የሱስ «የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም፤» ሲል የተናገረውን ሰማ። ዮሐ.6:53። የሱስ ለመስጠት የተዘጋጀው ዓለማዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነገር መሆኑ ገባው። ራሱን እንደ አርቀ አሳቢ ይገምት ሴለነበረ የሱስ አይከበርም፣ ለደቀ መዛሙርቱም የክብር ቦታ አይሰጣቸውም የሚል አስተሳሰብ ያዘ። በመሆኑም ወደ የሱስ በጣም ከመጠጋት ይልቅ ለመራቅ ወሰነ። ቢሆንም ውጤቱን ለማየት ፈለገ፣ አየም።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ደቀ መዛሙርቱን የሚያደናግር አስተሳሰብ መሰንዘርጀመር። ካህናቱና ጸሐፍት የየሱስን መሲሕነት በመቃወም የሚጠቀሙብ ቸውን የክርክር ነጥቦች በመጥቀስ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ውዝግብና የስሕተት አስተሳሰብ እንዲኖር ለማድረግ ጣረ። በወንጌል የመስፋፋት ሒደት ላይ የደረሱትን ትንንሽና ትልልቅ ችግሮች ይሁዳ የወንጌል መልእክት እውነተኛ ላለመሆኑ ማስረጃ ናቸው የሚል ትርጉም ሰጣቸው።"—Ibid., p. 719.

## 5. ከሃዲውን መለየት

**ሐሙስ፣ ሚያዚያ 02**

### ሀ. በይሁዳ የታየውን ባሕርይ ግለጽ። ዮሐንስ 12:4–6፤ ምሳሌ 3፡ 32

“[ይሁዳ] የሱስ ያስተምረው ከነበረው እውነት ጋር ግንኙነት የሌላቸው ጥቅሶችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቃቀሰ። እነዚህ ከትክክለኛ ይዘታቸው ተገንጥለው የተጠቀሱ ጥቅሶች ደቀ መዛሙርቱን ግራ ከማጋባት በተጨማሪ ዘወትር ያስጨንቃቸው የነበረውን ተስፋ የመቁረጥ ስሜት አባባሱት። ይሁዳ ይህን ያደረገው ለወንጌል ሥራ አሳቢ በመምሰል ነው።”—The Desire of Ages, p. 719.

### ለ. በገሊላ እንደ ደረሰው ቀውስ ባሉ ጉዳዮችም መካከል ቢሆንም እንኳ በሃይማኖታችን ተሞክሮ ውስጥ ምን ተስፋ እናገኛለን? ሮሜ 8፡28።

“የሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎቹን እንዲያፈገፍጉ ያደረጋቸውን ፈታኝ እውነት በተናገረ ጊዜ ውጤቱ ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ያውቅ ነበር፣ ይሁን እንጂ ገና የሚያከናውነው የምሕረት ዕቅድ ነበረው። በችግር ጊዜ የሚወዳቸው ደቀ መዛሙርት እያንዳንዳቸው ክፉኛ እንደሚፈተኑ አስቀድሞ ታየው። በጌተሰማኔ የሚደርስበት ጭንቀት፣ አሳልፎ ሲሰጥና ሲሰቀል ማየት ለደቀ መዛሙርቱ እጅግ የከፋ ስቃይ ያደርስባቸዋል። አስቀድሞ ፈተና ባይሰጥ ኖሮ ለግል ጥቅም የቀሙ ብዙ ሰዎች ይቀላቀ ሉዋቸው ነበር። በፍርድ ሸንጎው አዳራሽ ጌታቸው ሲወገዝ፣ ንጉሣችን ነው እያሉ ያወድሱት የነበሩት ሰዎች የጥላቻ ድምጽ ሲያሰሙ፣ በማፌዝ ይስቅና ይሳለቅበት የነበረው ሕዝብ «ስቀለው!» እያለ ሲጮኽ፣ በማየት እነዚያ ለግል ጥቅማቸው ብቻ የቀሙት ሰዎች ዓለማዊ ጥቅማቸው መክሸፉን በመረዳት ለየሱስ የነበራቸውን ታማኝነት በሚተውበት ጊዜ የሚጓጉለት ተስፋቸው በመሰናከሉ ምክንያት ባዘኑት ደቀ መዛሙርት ላይየመረረና ልብን የሚሰብር ሐዘን ያደርስባቸው ነበር። በዚያ ቀውጢ ሰዓት ከየሱስ የሚያፈገፍጉት ሰዎች ሌሎች እንዲከተሉዋቸው አርአያ ይሆኑ ነበር። የሱስ ይህን ሁኔታ የፈጠረው እርሱ ገና ከእነርሱ ጋር ሳለ የእውነተኛ ተከታዮቹን እምነት ለማጠንከር ብሎ ነው።”—Ibid., p. 394.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

**አርብ፣ ሚያዚያ 03**

1. “የክርስቶስን ሥጋ የምንበላውና ደሙን የምንጠጣው” እንዴት ነው?
2. ወደ የሱስ መመልከት ማለት ምን ማለት ነው?
3. አንዳንዶች በክርስቶስ ቃል የተናደዱት ለምንድን ነው?
4. በኋላ ምን አደረጉ? ይህስ ለእኛ ማስጠንቀቂያ የሚሆነው እንዴት ነው?
5. ከዚህ በኋላ የይሁዳን መንፈሳዊ ሁኔታ እና ውጤቱን ግለጽ።

# የሱስ በዳስ በዓል

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ።” ሉቃስ 4፡32።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Thoughts From the Mount of Blessing, **pp. 31–35.**

*“የሱስ የነፍሳትን ፍላጐት ያውቃል። መሽቀርቀር፣ ሐብትና ክብርየልብን ፍላጐት ሊያረኩ አይችሉም። «ውሃ የጠማው ቢኖር ወደ እኔ መጥቶ ይጠጣ።» ሐብታሞች፣ ድኾች፣ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉትም ሆኑ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉት ሁሉ እኩል ተጋብዘዋል። ለተጨነቀ አእምሮ እረፍት ለመስጠት፣ ያዘኑትን ለማጽናናትና ተስፋ የቀረጡት ሁሉ ተስፋ እንዲኖራቸው ለማድረግ ቃል ገብቶአል።”*—The Desire of Ages, p. 454.

## 1. የየሱስ ሕይወት በቤት ውስጥ — እሁድ፣ ሚያዚያ 05

### ሀ. የሱስ በራሱ ቤት ውስጥ ምን ከባድ ፈተና አጋጥሞታል? ዮሐንስ 7፡5

*“የሱስ ገና ከሕጻንነቱ ጀምሮ ስለ ጸባዩ አመሠራረት በግሉ መጣርጀመረ፤ ለወላጆቹ የነበረው አክብሮትና ፍቅር እንኳን ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ሊገታው አልቻለም። ከቤተሰብ ባሕልና ልማድ የተለየ ለሚያደርገው ድርጊት ሁሉ ማስረጃው «ተጽፎዋልና» የሚል ነበር። ነገርግን የምሑራኑ ተጽእኖ ኑሮውን የመረረ አደረገው። ገና በወጣትነቱ በእርጋታና በትዕግስት ችግርን የመቋቋም ከባድ ትምህርት መማር ነበረበት።*

*ወንድሞቹ ተብለው የሚጠሩት የዮሴፍ ልጆች ከምሑራኑ ጋር ተባበሩ። ባሕላዊ ደንቦች እንደ እግዚአብሔር ሕግ መከበር አለባቸው ባዮች ነበሩ። ሰው ሰራሽ ሕግጋትን ከእግዚአብሔር ቃል አብልጠው ያከብሩ ስለነበርየሱስ በእውነትና በሐሰት መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ ማወቁ ያበሳጫቸው ነበር። የእግዚአብሔርን ሕግ በትክክል ስላከበረ በጽኑ አወገዙት። የምሑራኑን ጥያቄዎች በመመለስ ስላሳየው ዕውቀትና ጥበብ ተደነቁ። ከአዋቂዎቹ የቀሰመው ትምህርት አለመኖሩን ቢያውቁም ምሑራኑን ሊያስተምራቸው እንደሚችል ለመረዳት ተገደዱ። የእርሱ ዕውቀት ከእነርሱ ዕውቀት የላቀ መሆኑን ተገነዘቡ። ነገር ግን እነርሱ ከማያውቁት የዕውቀት ምንጭ ከሆነው ከሕይወት ዛፍ ጋር ግንኙነት እንደነበረው አላስተዋሉም።”*—The Desire of Ages, p. 86.

## ሀ. የክርስቶስ ወንድሞች አመታዊውን የዳስ በዓል ጠብቀው ለእርሱ ምን ሐሳብ አቀረቡለት? ዮሐንስ 7:3፣ 4

“[የክርስቶስ] ወንድሞች የሱስ ምሑራኑን ማራቁ ስሕተት ነው ብለው ያምኑ ነበር። ወንድሞቹ ምሑራኑ ትክክል እንደሆኑና የሱስ ከእነርሱ ጋር ተቃውሞ መፍጠሩ ስሕተት ነው የሚል ስሜት ነበራቸው። ይሁን እንጂ ሕይወቱ እንከን እንዳልነበረበት አይተዋል፣ የደቀ መዛሙርቱን ያህል ባይሆንም በሥራው ሥራ ልባቸው በጣም ተነክቶ ነበር። በገሊላ ያገኘው ዝና ምኞታቸውን የሚያረካላቸው ስለመሰላቸው ተደሰቱ፣ ፈሪሳውያን የእርሱን ማንነት እንዲያውቁ ለማድረግ ኃይሉን ያሳያል የሚል ተስፋም ነበራቸው። መሲሑ ወይም የእሥራኤል መስፍን ቢሆንስ! ይህን ሐሳብ በኩራትና በደስታ ማሰላሰላቸው አልቀረም።

ስለዚህ ነገር እጅግ ከመጓጓታቸው የተነሳ የሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሔድ ገፋፉት። «ከዚህ ውጣ፣ ወደ ይሁዳም ምድር ሒድ፣ ደቀ መዛ ሙርትህ ደግሞ የምትሰራትን ስራ ያዩ ዘንድ። ማንም በቀስታ (በምስጢር) ነገር የሚያደርገው የለምና እርሱም በግልጥ ይሆን ዘንድ ይወዳል። ይህንስ ማድረግ ትወድ እንደሆንህ ራስህን ለዓለም ኣሳይ፣» አሉት። «እንደ» የሚለው ቃል ጥርጣሬንና አለማመንን ያመለክታል። እርሱ ፍርሃትና ድክመት ያለበት መሰላቸው። መሲሕ መሆኑን ካወቀ ለምን ዝም ይላል? እውነትም ኃይል ካለው ለምን በድፍረት ወደ ኢየሩሳሌም ሔዶ ማንነቱን አያረጋግጥም? በገሊላ ፈጸማቸው የተባሉትን አስደናቂ ድርጊቶች ለምን በኢየሩሳሌም አይፈጽማቸውም? ባልታወቁ ቦታዎች ተደብቀህ አስገራሚውን ሥራህን ለምን ላልተማሩት ገበሬዎችና አሣ አጥማጆች ጥቅም ብቻ እንዲውል ታደረገዋለህ? አሉት። ወደ ርዕሠ ከተማው ሒድና የካህናቱንና የሹማምንቱን ድጋፍ በመያዝ አዲስ መንግሥት መስርተህ ሕዝቡን አስተባብር።”—The Desire of Ages, p. 450.

## ለ. ሁልጊዜ የዋሆችን የሚያጋጥሟቸውን ችግር ግለጽ። መዝሙር 86:14

“እነዚህ የየሱስ ወንድሞች ያስቡ የነበሩት ልታይ ልታይ የሚል ምኞት ያላቸው ሰዎች እንደሚያስቡት ነው። ይህ መንፈስ በዓለም ላይ የሰፈነ ነበር። የሱስ ዓለማዊ መንግሥትን ከመመኘት ፈንታ የሕይወት እንጀራ ነኝ ማለቱ አስቀየማቸው። ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎቹ ትተውት ስለሔዱ በጣም አዘኑ። እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ ለመሆኑ ሥራው የሚመሰክርለት መሆኑን ላለመቀበል ሲሉ እነርሱ ራሳቸው ፊታቸውን ከእርሱ አዙረው ነበር።”—Ibid., p. 451.

## ሀ. ስለ የሱስ ምን ተቃራኒ አስተያየቶች ተነስተዋል? ዮሐንስ 7:11፣ 12

"የሱስ ስለሠራቸው ተአምራት ወሬው ከኢየሩሳሌም ተነስቶ አይሁዶች ተበታትነው ወደሚኖሩበት ቦታ ሁሉ ተናኝቶ ስለነበር ምንም እንኳን የሱስ ለብዙ ወራት በበዓላቱ ላይ ባይገኝም ሕዝቡ ስለ እርሱ የነበረው ስሜት አልቀነሰም ነበር። የዳሱን በዓል ለማክበር ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡ ብዙ ሰዎች እርሱን ለማየት ተስፋ ነበራቸው። በዓሉ እንደተጀመረ ስለ እርሱ ብዙ ጥያቄዎች ተሰነዘሩ። ፈሪሳውያኑና ሹማምንቱ እርሱን ለማውገዝ ጥሩ አጋጣሚ እንዳገኙ በማሰብ ይፈልጉት ነበር። በጉጉት «የት ነው ያለ?» እያሉ ጠየቁ፣ ግን የሚያውቅ ሰው አልተገኘም። ሁሉም ስለ እርሱ ያስቡ ነበር። ካህናቱንና ሹማምንቱን በመፍራት የእርሱን መሲሕነት አምኖ ለመቀበል የደፈረ አይኑር እንጂ ብዙ ሰዎች በየቦታው ስለ እርሱ ከልባቸው ይነጋገሩ ነበር። ብዙዎቹ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን በመደገፍ ሲናገሩ ሌሎች ግን ሕዝብን አታላይ ነው እያሉ ተከራከሩ።"—The Desire of Ages, pp. 451, 452.

## ለ. የሱስ ስለ ራሱ የሚናገሩትን ተቃራኒ አስተያየቶች እንዴት ነበር ዝም ያሰኘው? ዮሐንስ 7:14–18፤ ሉቃስ 4፡32።

"በበዓሉ አጋማሽ ላይ ስለ እርሱ የሕዝቡ ስሜት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ወቅት ሕዝቡ ከዚያ እያለ ወደ ቤተ መቅደሱ አደባባይ ገባ። ከዚያ በፊት በበዓሉ ላይ ስላልተገኘ በካህናቱና በሹማምንቱ እጅ ላለመግባት ስለፈራ ነው ተብሎ ተወርቶ ነበር። አሁን ግን ከዚያ በመገኘቱ ሁሉንም ገረማቸው። ሁሉም ጸጥ አሉ። ሕይወቱን ለማጥፋት በተጠሙት ብርቱ ጠላቶቹ መካከል በእርሱ ላይይታይበት በነበረው ክብርና ድፍረት ያልተደነቀ ሰው አልነበረም።

የሱስ በዚህ አኳኋን የዚያን ብዙ ሕዝብ ትኩረት እንደሳበ ቀሞ ከማንም አንደበት ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ንግግር አደረገላቸው። በንግግሩ ስለ እሥራኤል ሕግጋትና ሥርዓቶች፣ ስለ መስዋዕት አገልግሎትና ስለ ነቢያት ትምህርት ከካህናቱና ከሊቃውንቱ በጣም የበለጠ እንደሚያውቅ ግልጽ ሆነ። የአባቶችን ወግና የሥርዓት አምልኮትን መሰናክል አፈራረሰው። የወደፊቱ ሕይወት ትዕይንት ግልጽ ሆኖ የሚታየው ይመስል ነበር። የማይታየውን አምላክ እንደሚያየው ሆኖ ስለ ዓለማዊና ሰማያዊ፣ ስለ ሰብአዊና መለኮታዊ ጉዳዮች በሙሉ ሥልጣን ተናገረ። አነጋገሩ ግልጽና አሳማኝ በመሆኑ በቅፍርናሆም እንደሆነው ሁሉ «በሥልጣን ቃል ይናገር ስለነበር፣» (ሉቃ.4:32) ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ። ... ስለ ሕግና ትንቢቶች የነበረው እውቀት ሁሉንም ስላስገረማቸው።"—Ibid., pp. 452, 453.

## ሀ. የሱስ በአይሁድ መሪዎች ውስጥ ምን ተገነዘበ እና ምን ጥያቄ አቀረበላቸው? ዮሐንስ 7፡19

ክርስቶስ በልባቸው ያስቡት የነበረውን በማወቅ ለአይሁድ ምሑራን ስለ መለኮታዊነቱ ምልክት አሳያቸው። እነዚህ ምሑራን የሱስ በቤተሳይዳ ከሰጠው የፈውስ አገልግሎት ጀምሮ ሕይወቱን ለማጥፋት ሲዶልቱ ቆይተዋል። ይህን በማድረጋቸው ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከሩለት የነበረውን ሕግ ራሳቸው ጣሱት። ስለዚህ የሱስ «ሙሴ ሕግን ሰጥቶአችሁ የለምን? ነገር ግን ከእናንተ ሕግን የሚፈጽም ማንም የለም። እናንተ ለምን ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ?» አላቸው።"—The Desire of Ages, p. 456.

## ለ. ለክርስቶስ በሰጡት ምላሽ፣ የአይሁድ መሪዎች ስለ ምን ከሰሱት— እርሱስ በተራው ምን ምላሽ ሰጠ? ዮሐንስ 7፡20-23

"የሱስ ግን ይህን የአሽሙር ንግግር ከቁም ነገር ባለመቁጠር የቤተሳይዳው ፈውስ የሰንበትን ሕግ የማይጻረርና በአይሁዶች ሕግ አተረጓጉም መሠረትም ቢሆን ትክክል መሆኑን አብራራላቸው። ቀጥሎም «ሙሴ የግዝረ ትን ሥርዓት ሰጣችሁ...ታዲያ እናንተ በሰንበትም እኮ ሰውን ትገርዛላ ችሁ፣» አላቸው። በሕጉ መሠረት እያንዳንዱ ሕጻን በተወለደ በስምንተ ኛው ቀን መገረዝ ነበረበት። ይህ ስምንተኛ ቀን ሰንበት ቢሆንም የግዝረቱ ሥርዓት መካሔድ ነበረበት። «በሰንበት ቀን የሰውን ሁለንተና፣» መፈወስ ከሕጉ መንፈስ ጋር የበለጠ ተስማሚ መሆን ነበረበት አላቸው።—Ibid., pp. 456, 457.

## ሐ. የክርስቶስ ቀጣይ ማስጠንቀቂያ የያዘውን ሰፊ ጠቀሜታ አብራራ። የዮሐንስ ወንጌል 7፡24

"ባለሥልጣኖቹ ዝም ኣሉ፣ ሕዝቡ ግን «ሊገድሉት የሚፈልጉት ሰው ይህ አይደለምን? እነሆ እርሱ በግልጥ ይናገራል፣ እነርሱም ምንም አላሉትም። ይህ ሰው መሲሕ መሆኑን ባለሥልጣኖች በእውነት ዐውቀው ይሆን?» ብለው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተናገሩ።"—Ibid., p. 457.

"[ክርስቶስ] ውጫዊውን ገጽታ አይመለከትም። እሱ ሰው እንደሚፈርድ አይፈርድም። ለሰው እንደ ደረጃው፣ እንደ ችሎታው፣ እንደ ትምህርቱ ወይም እንደ ሹመቱ ዋጋ አይሰጥም። "ወደዚህ ሰው እመለከታለሁ" ይላል፤ "ምስኪን መንፈሱም ወደ ተሰበረ በቃሌም ወደ ሚደነግጥ"። —The Signs of the Times, October 21, 1897.

## ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍት በዚህ ዓለም ውስጥ ብዙውን ጊዜ በጥንት ዘመን የታየው፣ በተለይ ደግሞ በዚህ ዘመን ያለውን የኅብረተሰብ አእምሯዊ ሁኔታ የሚገልጹት እንዴት ነው? ኢሳይያስ 59:14፣ 15

“የክፉ ወኪሎች ኃይላቸውን በማጣመርና በማጠናከር ላይ ናቸው። ለመጨረሻው ታላቅ ተጋድሎ እየተጠናከሩ ነው። በዓለማችን ውስጥ ታላቅ ለውጦች በቅርቡ ይከሰታሉ፣ እናም የመጨረሻዎቹ እንቅስቃሴዎች ፈጣን ይሆናሉ። . . .

“ጠላት ፍትህን በማጣመም እና የሰዎችን ልብ በራስ ወዳድነት ፍላጎት በመሙላት ተሳክቶለታል። . . . የተራቡ የሰው ልጆች ጩኸት ወደ አምላክ ፊት ዘውትር እየወጣ ነው፤ በጭቀናና ዝርፊያ ሰዎች ብዙ ሀብት እያከማቹ ነው።”—Testimonies for the Church, vol. 9, pp. 11, 12.

## ለ. በሁከት ውስጥ ቢንሆንም እንኳን፣ በእግዚአብሔር መንገድ ለምን እንታመናለን? ኢሳይያስ 55:8፣ 9

“ውስን የሆነው የሰዎች አዕምሮ ወደ ዘላለማዊው እግዚአብሔር ምክር ለመግባት ወይም የአላማውን ውጤት ሙሉ በሙሉ መረዳት ባይችልም፣ የሰማይን መልእክቶች እጅግ በደበዘዘ ሁኔታ የሚረዱት ግን በራሳቸው ስህተት ወይም ግድየለሽነት ምክንያት ነው። በፍጡር አመለካከቶች፣ በሰዎች ባህልና የሃሰት ትምህርቶች ምክንያት፣ እግዚአብሔር በቃሉ የገለጣቸውን ታላላቅ ነገሮች ሰዎች በከፊል ብቻ እንዲረዱት የሚያደርጋቸው፣ የእግዚአብሔርን ባርያዎች ጨምሮ፣ የሰዎች አእምሮ የሚታወርበት አጋጣሚ አልፎ አልፎ ነው የሚባል አይደለም።—The Great Controversy, pp. 344, 345.

“እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው ሃሳብ እጅግ ምጡቅ የተባለ የሰው ሃሳብ ሊደርስበት ከሚችለው ሁሉ በላይ ነው። በቅዱስ ሕጉ የባሕርይውን ቅጂ ሰጥቶናልና።”—Testimonies for the Church, vol. 8, p. 63.



1. የሱስ ያደገበትን ቤት ከባቢ ሁኔታ ግለጽ።
2. የክርስቶስ ወንድሞች ያሳዩት ዝንባሌ በዛሬው ጊዜ የሚደገመው እንዴት ነው?
3. ስለ የሱስ ምን ተቃራኒ አስተያየቶች ተሰራጭተዋል?
4. የአይሁድ መሪዎች ለየሱስ ያሳዩትን መንፈስ ግለጽ።
5. በሰው እና በእግዚአብሔር መንገድ መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ግለጽ።

# እንደዚህ ሰው ማንም ከቶ አልተናገረም

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “ሎሌዎቹ። እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም ብለው መለሱ።” (ዮሐ. 7፡46)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies to Ministers, **pp. 506–512.**

“የሱስ እውነትን ለመቀበልና በትክክል ለማስተዋል ከሕሊናዊ አስተሳሰብ ይልቅ የሚያስፈልገው የልብ ዝግጁነት መሆኑን ተናገረ። እውነት በነፍስ ተቀባይነትን ማግኘትና በልብም መከበርን ይጠይቃል።”—The Desire of Ages, p. 455.

## 1. የሰዎች ፍላጎት በየሱስ ላይ

**እሁድ፣ ሚያዚያ 12**

### ሀ. አንዳንድ አይሁዳውያን የሱስን በግልጽ ሲሰብክ ሲሰሙና ሲያዩ ምን ብለው ጠየቁ? ዮሐንስ 7:25፣ 26

“የየሱስን ንግግር ያዳምጡ ከነበሩት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ በኢየሩሳሌም የሚኖሩና የባለሥልጣኖቹንም ሴራ የሚያውቁ ሲሆኑ ምንም ነገር ሊገታው በማይችል ኃይል ወደ የሱስ ተሳቡ። የሱስ የእግዚአብሔርልጅ ስለመሆኑ እምነታቸው ጽኑ ነበር።”—The Desire of Ages, p. 457.

### ለ. ሰይጣን በገዢዎቹ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር የሠራው እንዴት ነው? ዮሐንስ ወንጌል 7፡27

“ሰይጣን ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው ለማድረግ ዝግጁ ነበር፣ ለዚህም ሰዎቹ ስለ መሲሑና ስለ አመጣጡ የነበራቸው የተሳሳተ ግንዛቤ አመቺ ሁኔታ ፈጠረለት። በዚያን ጊዜ ክርስቶስ በቤተልሔም እንደሚወለድ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚሰወርና ሁለተኛ ሲገለጥ ከየት እንደመጣ ማንም አያውቅም ተብሎ ይታመን ነበር። መሲሑ የሰብአዊነት ባሕርይ አይኖረውም ብለው የሚያምኑም ጥቂት አልነበሩም። የናዝሬቱ የሱስ በሕዝቡ አስተሳሰብ መሠረት መሲሑ ይኖረዋል ተብሎ የተጠበቀው ክብር ስላልታየበት ብዙ ሰዎች «ታዲያ እኛ ይህ ሰው ከወዴት እንደሆነ እናውቃለን፣ መሲሕ ሲመጣ ግን ከወዴት እንደሆነ የሚያውቅ ማንም የለም፣» አሉ።—Ibid.

## ሀ. የሱስ የተጠራጠሩትን አድማጮቹን ሐሳብ ባነበበ ጊዜ ምን አላቸው? ዮሐንስ 7፡28

"ሰዎቹ እንደዚህ በጥርጣሬና በእምነት መካከል በሚዋልሉበት ጊዜ የሱስ ከአስተሳሰባቸው በመነሳት «እኔን ታውቁኛላችሁ፣ ከወዴትም እንደመጣሁ ታውቃላችሁ፣ ነገር ግን እኔ በራሴ ሥልጣን አልመጣሁም፣ የላከኝ እውነተኛ ነው፣ እናንተም አታውቁትም» በማለት መለሰላቸው። የክርስቶስን መነሻ የሚያውቁ ይመስላቸው ነበር። ነገር ግን እርሱ ከየት እንደመጣ ፈጽሞ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነት ሕይወት ኖረው ቢሆን ኖሮ ልጁ በተገለጠላቸው ጊዜ ሊያውቁት ይችሉ ነበር።"—The Desire of Ages, p. 457.

## ለ. የሱስን ለመቃወም የሚያስችል መከራከሪያ ስለሌለ፣ የአይሁድ መሪዎች እሱን ዝም ለማሰኘት የሞከሩት በምን መንገድ ነው? ዮሐንስ 7፡30 (የመጀመሪያ ክፍል)። ታዲያ፣ ለምን ሊይዙት አልቻሉም? ዮሐንስ 7፡30 (የመጨረሻው ክፍል)።

"አዳማጮቹ ክርስቶስ የተናገራቸውን ቃላት በሚገባ አስተውለዋል። ይህ ንግግር የሱስ ከብዙ ወራት በፊት በአይሁድ ብሔራዊ ሸንጎ ፊት እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ የተናገረው ንግግር ማጠናከሪያ ነበር። በዚያን ጊዜ ባለሥልጣኖቹ የየሱስን ሕይወት ለማጥፋት ባቀዱት መሠረት አሁን ሊይዙት ፈልገው ነበር። ነገር ግን አንድ የማይታይ ኃይል ከዚህ ማለፍ አትችሉም በማለት አገዳቸው።"—Ibid.

## ሐ. ብዙዎች በየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት የገለጹት እንዴት ነው—ገዥዎቹስ በሕዝቡ ዘንድ ለእርሱ ያለውን ቦታ ሲገነዘቡ ምን ለማድረግ አሰቡ? ዮሐንስ 7:31፣ 32

"ሁኔታውን በጉጉት ይከታተሉ የነበሩት የፈሪካውያን መሪዎች ሕዝቡ ለየሱስ ያሳይየነበረውን የድጋፍ መግለጫ ተመለከቱ። በፍጥነት ወደ ካህናት አለቆቹ ሐደው እርሱን የሚይዙበትን ዕቅድ አመቻቹ። ከሕዝቡ መካከል ሊይዙት ስላልደፈሩ ብቻውን በሚሆንበት ጊዜ ሊይዙት ተዘጋጁ።"—Ibid., pp. 457, 458.

## ሀ. በበዓሉ የመጨረሻ ቀን የሱስ በኃጢአት የደከሙትን ነፍሳት ለማጽናናት የተጠቀመው ግሩም ምሳሌ ምንድን ነው? ዮሐንስ 7:37፣ 38

"የእግዚአብሔርን ቃል የሚቀበል ልብ በጸሐይ እንደሚደርቅ እቋሪ ውሃ ወይም እንደሚያፈስ ባሊ አይደለም። የተጠሙትን ሁሉ እንደሚያረካ፣ የደከሙትን እንደሚያበረታ ከተራራ ስር መንጭቶ በቋጥኞች መካከል እየተጣራ ሳያቋርጥ እንደሚወርድ ወንዝ ነው። አወራረዱ ጥልቅ ሆኖ ውኃው መሬትን ሁሉ እንደሚያጠጣ ወንዝ ነው። እያዜመ የሚወርደው ውኃ በመንገዱ ፍሬን እያበረከተ ያልፋል። በዳሩ የሚገኘው ስር የለመለመ ዛፎች ቅርንጫፋቸው የበዛ፣ አበባዎቹም በጣም የፈኩ (የደመቁ) ይሆናሉ። መሬት በድርቅ ምክንያት አቧራ ስትሆን የወንዙ ዳር ግን ለምለም ይሆናል።

"እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅም እንዲሁ ነው። የክርስቶስ ሃይማኖት ሕይወትን ያድሳል።ሕያውና መንፈሳዊ ጉልበት ነው። ልብ የሰማያዊውን ዕውነታዊ ተፅዕኖ ሲቀበልና በፍቅር ሲሞላ እንደነዚህ ውኖች በምድረ በዳ መካከል እየወረደ በድርቅ ፋንታ ልምላሜንና ፍሬን የሚያስገኝ የውኃ ቦይ (መስኖ) ይመስላል።"—Prophets and Kings, pp. 233, 234

" 'ማንም ሰው የሚያረጋጋ ተስፋን፣ ከኃጢአት ዝንባሌ መዳንን ቢጠማ፣ ክርስቶስ 'ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ' ይላል። ዮሃንስ 7:37።"—The Ministry of Healing, p. 179.

## ለ. ይህን ግብዣ የበለጠ ለመረዳት የሚቻለው እንዴት ነው? ዮሐንስ 7፡39

"ክርስቶስ የእውነትን መርሆች በወንጌል አቅርቧል። በእርሱ ትምህርት ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚፈሱትን ንጹህ ጅረቶች እንጠጣለን።"—Testimonies for the Church, vol. 8, p. 309.

"እኛ የምንፈልገው ሕያው ሃይማኖት ነው። ነፍሱ ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራኘችለት እና ለክርስቶስ በቅንዓት የተሞላ ስለ ግዴታው ሰፊ መረዳት ያለው አንድ ተራ ሰው ለበጎ ነገር የሚሆን በጎ ተጽዕኖ ያሳድራል። ከንጹሕ፣ ከምንጩ አጠገብ ካለው ውሃ እንጂ የተበላሸ፣ የደፈረሰና የረከሰውን ወንዝ አይጠጣምና አዲስ መንፈስ እና ኃይልን ለቤተ ክርስቲያን ማስተላለፍ ይችላል፡ ፡ ከውጪ የሚመጣው ጫና እየጨመረ ሲሄድ፣ እግዚአብሔር በሚያምናቸው በተቀደሰ፣ ጥብቅ እውነቶች ቤተ ክርስቲያኑን ያበረታታል። ከሰማይ የወረደው መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ጋር በመሥራት እንቅፋቶችን በማለፍ በጠላት እጅ ውስጥ ያለውን ምሽግ ይይዛል። አምላክ እውነትን ለሚወዱና ትእዛዛትን ለሚጠብቁ ሰዎች ታላቅ ድሎችን ይሰጣል።"—Ibid., vol. 5, p. 581.

## ሀ. ክርስቶስ ስለሕይወት ውኃ ያለውን በመጥቀስ ብዙዎች ምን መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል—ለምንስ? ዮሐንስ 7፡40 (ከዘዳግም 18፡15 ጋር አወዳድር)።

## ለ. አንዳንዶች እንዲህ ባለው ተስፋ ተነሳስተው ሳለ ሌሎችስ ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 7፡41-44

## ሐ. መኮንኖቹ ከአለቆቻቸው ምን ትዕዛዝ ተቀበሉ? ዮሐንስ 7፡45 ራሳቸው የሱስን መያዝና ማምጣት ያልቻሉት ለምንድን ነው? ዮሐንስ 7፡46

"*የሱስን ለመያዝ በካህናቱና በሹማምንቱ ተልከው የነበሩት ሰዎች በበዓሉ መጨረሻ ቀን ባዶ እጃቸውን በተመለሱ ጊዜ «ስለምን አላመጣችሁትም?» የሚል የቁጣ ጥያቄ ቀረበላቸው። እነርሱም ኮስተር ብለው «ይህ ሰው እንደሚናገረው ዐይነት ማንም ተናግሮ አያውቅም፣» ብለው መለሱላቸው።*

"*ደንዳናው ልባቸው በየሱስ ቃል ተነካ። እርሱ በቤተ መቅደሱ አደባባይንግግር በሚያደርግበት ጊዜ እርሱን ለመክሰስ የሚያስችል ነገር በመሻት በአካባቢው ሲያንዣብቡ ቆዩ። ንግግሩን በተመስጦ በማዳመጥ የተላኩበትን ተግባር ረሱት። ክርስቶስ ለነፍሳቸው ተገለጠላቸው። ካህናቱና ? ባለሥልጣናቱ ሊያዩት ያልቻሉት ሰብአዊነት በመለኮት ክብር ተጐናጽፎ አዩ።*"—The Desire of Ages, p. 459.

"[ክርስቶስ] *መለኮታዊውን እውነት ለማስረዳት የሚያውቁትን የተፈጥሮ ነገር ተጠቅሟል። በዚህ መንገድ ጥሩውን ዘር ለመቀበል የልብ አፈር ተዘጋጅቷል፡ ፡ አድማጮቹ የእሱ ፍላጎቶች ከነሱ ጋር አንድ እንደሆኑ፣ በደስታቸው እና በሀዘናቸው ልቡ አብሯቸው እንደሚመታ እንዲሰማቸው አድርጓል። በተመሳሳይ ጊዜ እጅግ ከተከበሩ መሪዎቻቸው መካከል ከሁሉም የሚበልጠዉ እንኳን ካለው ይልቅ እጅግ የላቀ የኃይል እና ክብር በእርሱ እንዳለም ተመልክተዋል። የክርስቶስ አስተምህሮዎች ከዚህ በፊት በማያውቋቸው ቀላልነት፣ ክብር እና ሃይል ያላቸው ነበሩ፣ እናም ያለፈቃዳቸው ከአፋቸው የሚወጣው ጩኸታቸው፡ - 'እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም' የሚል ነበር። ሕዝቡ በደስታ ያዳምጡት ነበር፤ ነገር ግን ራሳቸውን የእውነት ጠባቂዎች አድርገው በውሸት የሚያምኑት ካህናቱና አለቆቹ ህዝቡን ከእነርሱ ለይቶ የሕይወትን ብርሃን እንዲከተሉ ባደረገው በእርሱ ስለ ተገለጠው ጸጋ ክርስቶስን እርሱን አምርረው ጠሉት። የአይሁድ ነገዶች በእነሱ ተጽዕኖ ምክንያት መለኮታዊውን ባሕርይ ማወቅ ባለመቻላቸው አዳኙን አልተቀበሉም።*"—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 747.

## 5. በቅንነት የሚፈልግ እየበረታ ሄደ | ሐሙስ፣ ሚያዚያ 16

### ሀ. የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሎሌዎቹን እንዴት ገሠጹአቸው? ዮሐንስ 7፡47-49

### ለ. ከኒቆዲሞስ ጋር የተካሄደውን ውይይት አብራሩ—በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከክርስቶስ ጋር በምሽት ንግግር ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን እድገት ያሳያል። ዮሐንስ 7፡50–52።

"[ኒቆዲሞስ] እውነትን በልቡ ደበቀ፣ እናም ለሦስት ዓመታት ያህል ብዙም በግልጽ የማይታይ ፍሬ ነበረው። ይሁን እንጂ ኒቆዲሞስ ለክርስቶስ በይፋ እውቅና ባይሰጥም በአይሁድ መማክርት ሸንጎ ውስጥ ካህናት እሱን ለማጥፋት ያደርጉት የነበረውን ዕቅድ ደጋግሞ አከሸፈ።"— The Acts of the Apostles, p. 104.

"ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ [በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ላይ በምሽት ጉብኝት ወቅት] የሰጠው ትምህርት ከንቱ አልነበረም። ፅኑ እምነት በልቡ ላይ ተጣብቆ ነበር፣ እና በልቡ የሱስን ተቀብሏል። ከአዳኝ ጋር ካደረገው ቃለ ምልልስ ጀምሮ ፣ የብሉይ ኪዳንን ቅዱሳት መጻሕፍት በትጋት መርምሯል፣ እናም እውነት በወንጌል እውነተኛ መቼት (ጊዜና ቦታ) ውስጥ በትክክል ሲቀመጥ አይቷል።

"በእሱ የጠየቀው ጥያቄ ጥበብ የተሞላበት ነበር፣ እናም በጠላት ባይተታለሉ ኖሮ በሸንጎው ውስጥ የነበሩትን ሁሉን የሚያሳምንም ነበር። ነገር ግን በጭፍን ጥላቻ ተሞልተው ስለነበር የናዝሬቱን የሱስን የሚደግፍ ምንም ዓይነት ክርክር ምንም አሳማኝ ቢሆን በእነርሱ ዘንድ ተቀባይነትት አልነበረውም። ኒቆዲሞስ ከነሱ ያገኘው መልስ፡- "አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ ከገሊላ አይነሣምና መርምርና እይ" የሚል ነበር።

"ካህናቱና አለቆቹ ክርስቶስ ከገሊላ እንደ ወጣ እንዲያምኑ ሰይጣን ባቀደው እቅድ እነሱም መሠረት እነሱም ተታለሉ። በቤተልሔም እንደተወለደ የሚያውቁ አንዳንዶች ግን እነሱ ከተናገሩ ይህ የውሸት ክስ ኃይሉን እንዳያጣ በመስጋት ዝም አሉ።"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, p. 1136.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሚያዚያ 17

1. የሱስ የሰዎችን ትኩረት የሳበው ለምንድን ነው?
2. የአይሁድ ገዥዎች የሱስን ለማስቆም ያደረጉትን ጥረት የቀጠሉት እንዴት ነው?
3. የሱስ በበዓሉ የመጨረሻ ቀን ምን ግልጽ ጥሪ አቅርቧል?
4. በዚህ ምክንያት የተፈጠረውን ታላቅ ውዝግብ አስረዳ።
5. የማውቃቸውን ሰዎች ሳስብ፣ ስለ ኒቆዲሞስ ምን ማስታወስ አለብኝ?

## የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ

## ሰንበት፣ ሚያዚያ 25፣ 2017



# ለአለም ተልዕኮዎች



ዛሬ፣ ወቅታዊው መልእክት ይሰማል፡-

“በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የሚስዮናውያን መንፈስ መነቃቃት አለበት። እያንዳንዱ የቤተ ክርስትያን አባል በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የእግዚአብሐርን ሥራ እንዴት ማገዝ እንዳለበት ማጥናት አለበት። በሚስዮናዊነት መስኮች መከናወን ያለበት ሥራ አንድ ሺህኛው ክፍል ብቻ (በጣም ጥቂት) እየተሠራ ነው። እግዚአብሔር ሠራተኞቹን ለእርሱ አዲስ ግዛት እንዲጨምሩ ጠርቶአቸዋል። ታማኝ ሠራተኛን የሚጠብቁ ለም የሆኑ የሥራ መስኮች አሉ። አገልጋይ መላዕክት ደግሞ ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ ለመምህሩ አገልግሎት ከሚደክሙት እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባላት ጋር ይተባበራሉ።

“በምድር ላይ ያለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የተደራጀችው ለሚስዮናዊነት (ወንጌልን ለማድረስ) አገልግሎት ዓላማ ነው፣ እና ጌታ መላው ቤተክርስቲያን አባላት ትላልቆቹም ሆነ ትናንሾች፣ ሀብታሞችም ሆነ ድሆች፣ የእውነትን መልእክት የሚሰሙበት መንገዶችን እና ዘዴዎችን ሲቀይስ ማየት ይፈልጋል። ሁሉም በሌላ አገር በአካል ተገኝተዉ እንዲሠራ አይደለም የተጠሩት፣ ነገር ግን ሁሉም የሚስዮናዊነትን ሥራ ለመርዳት በጸሎታቸው እና በስጦታቸው አንድ ነገር ማድረግ ይችላሉ።

“አንድቅን ክርስቲያን የነበረ፣ አሜሪካዊ ነጋዴ፣ ከሥራ ባልደረባው ጋር ሲነጋገር፣ እሱ ራሱ በቀን ሃያ አራት ሰዓት ለክርስቶስ እንደሚሠራ እንዲህ ሲል ይናገራል። ‘በንግድ ግንኙነቴ ሁሉ ጌታዬን ለመወከል እሞክራለሁ። እድል ሳገኝ፣ ሌሎችን ወደ እሱ ለማሸነፍ እሞክራለሁ። ቀኑን ሙሉ ለክርስቶስ እየሰራሁ ነው። እና ማታ፣ እኔ ተኝቼ፣ ቻይና ውስጥ ለጌታዬ የሚሠራ ሰው አለኝ።’

አክሎም “በወጣትነቴ ሚስዮናዊ ሆኜ ወደ አረማውያን ለመሄድ ወሰንኩ። ነገር ግን አባቴ ሲሞት ለቤተሰቡ አስፈላጊዉን ነገር ለማሟላት ሥራ መሥራት ነበረብኝ። አሁን፣ ራሴ ከሚሄድ ይልቅ ሚስዮናዊ ሥራን እደግፋለሁ። በእንደዚህ ባለ የቻይና ግዛት ውስጥ ባለች ከተማ ሰራተኛዬ ይኖራል። እናም፣ እኔ ተኝቼ ሳለሁም፣ በተወካዬ አማካኝነት አሁንም ለክርስቶስ እየሰራሁ ነው።’”—Testimonies for the Church, vol. 6, pp. 29, 30

በአለም ተልእኮዎች በኩል በማድረግ በሰማይ ባንክ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ጊዜው አሁን ነው። ከዚህ የተሻለ ጊዜ አይመጣም፣ እንዲሁም በኋላ ስንል ሊዘገይ ይችላል። ነፍሶች ያለ ክርስቶስ እና የወቅቱን እውነት ሳይሰሙ እየጠፉ ነው፣ እንዲሁም ጌታ በምድራችን ዙሪያ እንዲሰራጭ ውድ ብርሃንን በአደራ ሰጥቶናልና።

እባካችሁን በልግስና ስጡ፣ እናንተንና ስጦታችሁን ጌታ አብዝቶ ይባርክ። እናመሰግናለን!

የጀኔራል ኮንፈረንስ ሰንበት ትምህርት ክፍል መምሪያ

# “እኔም አልፈርድብሽም”

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።” (ዮሐንስ 8፡11 (የመጨረሻው ክፍል)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 2, pp. 73–77.**

“ክርስቲያናዊ ፍቅር ለመገሰጽ የማይቸኩል፣ ንስሐ የመግባትን ምልክት ፈጥኖ የሚረዳ፣ ይቅር ለማለት፣ ለማበረታታት፣ የተሳሳተን ሰው ወደ ቅድስና ለመመለስና ከቅድስና መንገድ እንዳይወጣ ለማድረግ ዝግጁ ነው።”—The Desire of Ages, p. 462.

## 1. ለየሱስ የተዘጋጀ ወጥመድ — እሁድ፣ ሚያዚያ 19

### ሀ. የሱስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ እያስተማረ ሳለ ጻፎችና ፈሪሳውያን ምን አደረጉ? ዮሐንስ 8፡2-3

“[ክርስቶስ] ብዙም ሳይቆይ ትምህርቱን ማቋረጥ ነበረበት። ፈሪሳውያንና ጸሐፍት በድንጋጤ ግራ የገባት ሴት እየጐተቱ ሰባተኛውን ሕግ ስለመሻርዋ ክሳቸውን በከፍተኛ ድምጽ እያሰሙ ወደ የሱስ መጡ።”—The Desire of Ages, p. 460.

### ለ. ፈሪሳውያን ለህግ ከፍተኛ አክብሮት በማሳየታቸው ለክርስቶስ ምን ጥያቄ አቅርበው ነበር? ዓላማቸውስ ምን ነበር? ዮሐንስ 8፡ 4-6 (የመጀመሪያ ክፍል)።

“ለይምሰል ያህል ያሳዩት አክብሮት እርሱን ለማጥፋት የጠነሰሱት ሥርየሰደደ ሴራ ሽፋን ነበር። ምንም ዓይነት ውሳኔ ቢወስን እርሱን ለመክሰስ በቂ ምክንያት አናጣም በማለት ለውንጀላ እንዲያመቻቸው ሲሉ ይህን አጋጣሚ ተጠቀሙበት። ሴትዮዋን በነጻ ቢለቃት የሙሴን ሕግ ችላ ብሏል የሚል ክስ ይቀርብበታል፣ የሞት ፍርድ ቢወስንባትም የሮማውያንን ሥልጣን በመሻማት ይወነጀላል።”—Ibid., pp. 460, 461.

## ሀ. የሱስ ለፈሪሳውያን ውሸት ምን ምላሽ ሰጠ? ዮሐንስ 8፡6 (የመጨረሻው ክፍል)።

*"የሱስ ሁኔታውን አጤነ፣ ማለትም በሐፍረት የምትርበደበደውን ሴትና ሰብአዊ ርህራሄ የጐደለውን የመኳንንቱን የጭካኔ ገጽታ ተመለከተ። እንከን የሌለው ንጹሕ መንፈሱ በዚያ ትዕይንት ምክንያት ተሸማቀቀ። የሱስ ይህ ክስ ለምን ምክንያት ወደ እርሱ እንደመጣ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። ከዚያ የነበሩትን ሰዎች የእያንዳንዳቸውን ልብ በማንበብ ባሕርያቸውንና የሕይወት ታሪካቸውን ያውቅ ነበር። እነዚህ አቃቤ ሕግ መሆን የሚገባቸው ሰዎች የሱስን ለማጥመድ ሲሉ የእነርሱ ሰለባ የሆነችውን ሴት ኃጢኣት እንድ ትሠራ ያደረግዋት ራሳቸው ናቸው። የሱስም የከሳሾቹን ጥያቄ ያዳመጠ ባለመምሰል ጐንበስ ብሎ ወደ መሬት እየተመለከተ በአፈሩ ላይ መጻፍ ጀመረ።"*—The Desire of Ages, p. 461.

## ለ. የሱስ ከሳሾቹ ራሳቸው ኃጢአት አልባ እንዳልሆኑ ያሳየው እንዴት ነው? እነሱስ ምን አደረጉ? ዮሐንስ 8፡7-9

*"ከሳሾቹ ተረቱ። አሁን የይስሙላ ቅድስና ካባቸው ተቀድዶ ዘላለማዊ ንጽሕና ባለው ጌታ ፊት ኃጢአተኛና ወንጀለኛ ሆነው ቆሙ። ስውር ኃጢአ ታቸው ለሕዝቡ ይገለጽብናል ብለው በመፍራት እየተርበደበዱ የእነርሱ ሰለባ የሆነችውን ሴት ከርህሩሁ ጌታ ጋር ትተው አንገታቸውን አቀርቅረው አንድ በአንድ ሾልከው ጠፉ።"*—Ibid

## ሐ. በአጠቃላይ፣ የሱስ ለከሳሾቹ ከተናገራቸው ቃላት ምን እንማራለን? ሉቃስ 6፡42

*"ለእነርሱ ስህተት መስሎ የሚታያቸውን ነገሮች ለማሻሻል ብስለት የጎደለው ፍላጎት ያላቸው ሰዎች አሉ። ስህተት የሰራውን ሰው ለመተካት እኛ ራሳችን መመረጥ አለብን ብለው ያስባሉ። ሌሎች ዳር ቆመው እያዩ እና እየተቹ እነዚህ ሰራተኞች የሰሩትን ሥራ ዋጋ ዝቅ አድርገው ይመለከቱታል። በተግባራቸው እንዲህ ይላሉ፡- 'እኛ ታላቅ ነገሮችን ማድረግ እንችላለን። ሥራውን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን እንችላለን።' ለእንደነዚህ ላሉ ስህተትን እንዴት እንደሚያስወግዱ ጠንቅቀው የሚያውቁ ለሚመስላቸው፡- 'እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ' እንድል ታዝዣለሁ። ማቴዎስ 7፡1። እነዚህ ወንድሞች በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ስህተቶችን ሊያስወግዱ ይችላሉ፣ ነገር ግን በሌሎች ነገሮች ላይ ለማስተካከል በጣም ከባድ እና በስራው ውስጥ ግራ መጋባትን የሚያመጣ ከባድ ስህተቶችን የመስራት ትልቅ አጋጣሚ ያላቸው ናቸው። እነዚህ ስህተቶች ወንድሞቻችሁ ከሰሩት የበለጠ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ናቸው።"*—Testimonies for the Church, vol. 7, p. 279.

## ሀ. የሱስ ከሳሾቿ ከሄዱ በኋላ ሴቲቱን ምን ጥያቄ ጠየቃት? ሁኔታውን የያዘበት መንገድስ ሕይወቷን የሚነካው እንዴት ነው? ዮሐንስ 8:10፣ 11

*"ሴቲቱም በፍርሃት ተሸማቅቃ በየሱስ ፊት ቆመች። 'ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት' የሚለው የየሱስ ቃል የሞት ፍርድ ብያኔ ሆኖ ነው የተሰማት። ቀና ብላ የአዳኙን ፊት ለማየት አልደፈረችም፣ ነገር ግን በዝምታ ሞቷን እየጠበቀች ነበር። ከሳሾቿ ዝም ብለው ሲሄዱ አየቻቸውና በመገረም ግራ ተጋብታ ነበር፤ "እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂና ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ" የሚል የተስፋ ቃል በጆሯ ተሰማ። ልቧ ቀለጠ፣ በየሱስ እግር ስር ወድቃ፣ ከምስጋናና ፍቅር ብዛት እየተንሰቀሰቀችና እንባዋን እያፈሰሰች ኃጢአቷን ተናዘዘች።*

*"ያቺ ወቅት ለእርሷ የንጽህና፣ የሰላምና በእግዚአብሔር አገልግሎት የተቀደሰ የአዲስ ሕይወት ጅማሬ ነበረች። የሱስ የዘላለም ሞት የሚያስከትለውን የዚህችን ሴት መንፈሳዊ ደዌ በመፈወሱ አጅግ በጣም አስከፊ የሆነን ሥጋዊ በሽታ ሁሉ ከመፈወስ የበለጠውን ታላቁን ተዓምራት አከናወነ። ይህቺ የንስሓ የገባች ሴት ከፅኑ ተከታዮቹ አንዷ ሆነች። ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ ፍቅር እና ታማኝነት ለይቅርታው ምህረቱ ምስጋናዋን አሳይታለች። አለም ለዚች ለተሳሳተች ሴት ነበረው ንቀትና ጥላቻ ብቻ ነበር፤ ኃጢአት የሌለበቱ ግን ስለድካሟ አዘነ፣ የእርዳታ እጁን ዘረጋላት። ግብዞች ፈሪሳውያን ሲያወግዙት የሱስ "እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂና ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ" አላት።"*—The Ministry of Healing, p. 89.

*"ይህቺን ሴት ይቅር በማለቱና የተሻለ ሕይወት እንድትኖር በማደፋፈሩ የየሱስ ባሕርይ ፍጹም የሆነ የቅድስና ውበት ያንጸባርቃል። የሱስ ኃጢአትንና ኃጢአተኛነትን አድበስብሶ ማለፍ ባያውቅም ማዳን እንጂ መኮነን አይሻም። ይህቺ የተሳሳተች ሴት ከዓለም ያገኘችው ንቀትንና ጥላቻን ሲሆን የሱስ ግን የማጽናኛና የተስፋ ቃላት ተናገራት።"*—The Desire of Ages, p. 462.

## ለ. የክርስቶስን የማዳን ጸጋ ውጤት ግለጽ። ሉቃስ 7:37–40፣ 47፣ 48

*"የሱስ የእያንዳንዱን ነፍስ ሁኔታ ያውቃል። የኃጢአተኛው ጥፋተኝነት እንደበዛ መጠን አዳኙ አብልጦ ያስፈልገዋል። የእርሱ የመለኮት ፍቅር እና የርህራሄ ልቡ ከሁሉም ይልቅ በጠላት ወጥመዶች ውስጥ ተስፋ የለሽ ሆኖ ለተጠላለፈው ሰው የተዘጋጀ ነው። በገዛ ደሙ የሰው ዘር ነጻ መውጣቱን የሚያመላክተውን ሰነድ ፈረመ።"*—The Ministry of Healing, pp. 89, 90.

## ሀ. በተለይ ከሌሎች ጋር በተያያዘ አመለካከታችንን ሊሆን የሚገባው ምንድን ነው - እና ይህስ እንዴት ብቻ ሊሆን ይችላል? 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡3-5

*"ሁኔታዎችን ከነፍስ ልምምዶች ጋር የሚያገናኘው ጥቂት ነገር ነው። ለድርጊታችን ሁሉ መልክ የሚሰጠው በእኛ ዘንድ የሚወደደው መንፈስ ነው። ከእግዚአብሔር እና ከባልንጀሮቹ ጋር ሰላም ያለው ሰው አሳዛኝ ሰው ሊሆን አይችልም። ምቀኝነት በልቡ ውስጥ አይኖርም፤ ክፉ ሐሜት በእሱ ቦታ አያገኝም፤ ጥላቻ ከእሱ ዘንድ ሊኖር አይችልም። ከአምላክ ጋር የሚስማማ ልብ በዚህ ሕይወት ከሚያስጨንቁ ሁኔታዎችና ፈተናዎች በላይ ከፍ ከፍ ይላልና።"*—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 488.

*"የሱስ የማጽናናት አገልግሎት ያገኘው በመከራ ነው። በሰው ልጅ መከራ ሁሉ እርሱ ተጨንቋል፤ እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላል። ኢሳይያስ* 63:9፤ *ዕብራውያን* 2፡18 *ከክርስቶስ ጋር መከራ የመካፈልን ኅብረት የተቀላቀለ ነፍስ ሁሉ በዚህ አገልግሎት የመካፈል መብት አለው።"*—Thoughts From the Mount of Blessing, p. 13.

## ለ. የክርስቶስን ፈለግ በመከተል የምናገኘውን ልዩ ተስፋ እና እድል ግለጽ። 2ኛ ቆሮንቶስ 1:6፣ 7

*"የክርስቶስ መከራ ተካፋይ መሆን ክብር እንደሆነ ካልተሰማችሁ፤ ለጥፋት ለተዘጋጁት የነፍስ ሸክም ካልተሰማችሁ፤ ሊሠራ የሚገባው ሥራ እንዲሠራ ገንዘብንና ንብረትን ለመሠዋት ፍቃደኛ ካልሆናችሁ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ለእናንተ ቦታ አይኖራችሁም። በእያንዳንዱ እርምጃ ከክርስቶስ ጋር የመከራው እና ራስን የመካድ ተካፋይ መሆን አለብን።"*—Testimonies for the Church, vol. 9, pp. 103, 104.

## ሐ. በሦስቱ መላእክት መልእክት ውስጥ በአማኞች መካከል በጣም የሚፈለጉ ባሕርያት ግለጽ። 1ኛ ቆሮንቶስ 13:13፣ 4–8

*"የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ጠባቂ ሕዝቦች ልንከባከቧቸው የሚገቡ በጣም አስፈላጊዎቹ ባሕርያት ትዕግሥትና መቻል፣ ሰላምና ፍቅር ናቸው። ፍቅር ሲጎድል ወደ ሊካካስ የማይችል ኪሳራ ይኖራል።"*—Ibid., vol. 6, p. 398.

# 5. በየዋህነት ፍቅር መመለስ | ሚያዚያ 23

## ሀ. ሐሰተኛ ልብ ያላቸው አማኞች ብዙ ጊዜ ከሚያደርጉት በተቃራኒ አንድ ክርስቲያን በኃጢአት ቢወድቅ እውነተኛ አማኞች እሱን ለመመለስ እንዴት ይሠራሉ? ገላትያ 6:1-3፤ ሮሜ 15፡1-3

*"ኃጢዘተኛውን የመመለስ ስራ የኛ ሸክም መሆኑን አስታውስ። ይህ ሥራ በትዕቢት፣ በሥልጣን፣ በጌትነት የሚሠራ አይደለም። በእራስህ መንገድ፣ 'ሥልጣን አለኝና እጠቀምበታለሁ' አትበል፣ እናም በተሳሳተ ሰው ላይ ውንጀላ (ክስ) አትድፋ። አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን እየጠበቅህ፣ ኃጢአተኛውን የመመለስን ሥራ 'በየዋህነት መንፈስ አድርግ። ለወንድሞቻችንን እንድንሠራ ከፊታችን የተቀመጠው ሥራ እነርሱን ወደ ጎን እንድንጥላቸው አይደለም፣ 'አበሳጭተሀኛልና እኔም ልረዳህ አልፈልግም' በማለት ተስፋ እንዲቆርጡ ወይም እንዲጠፉ ማድረግ አይደለም። ራሱን በጥበብና በብርታት የተሞላ ሰውአድርጎ የሚያሳብ፣ የተጨቆነውንና የተጨነቀውን፣ እርዳታን የሚሻውን የማይረዳ፣ የፈሪሳዊውን መንፈስ የሚገልጥና ራሱን በራሱ ባዘጋጀው የክብር ልብስ የሚያጀቡን ሰው ነው። እርሱ በመንፈሱ እንደ ሌሎች ሰዎች ባለመሆኑ፣ አካሄዱ የተመሰገነ እንዲሁም ቢፈተን እንኳን የማይወድቅ በጣም ጠንካራ እንደሆነ አድርጎ በማሰቡ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ነገር ግን 'አንድ ሰው ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና።' ቁጥር 3"*—Testimonies for the Church, vol. 6, pp. 398, 399.

*"ስህተት የሚሠሩን ሰዎች ለማሳጣት ግንባርቀደም በመሆን እነዚህን ሰዎች ለመክሰስ ጉጉት ያለባቸው ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ በሕይወታቸው አንድ እንከን ያለባቸው ናቸው። ሰዎች ኃጢአትን እየወደዱ ኃጢአተኞችን ይጠላሉ። ክርስቶስ ኃጢአትን ይጠላል፣ ኃጢአተኞችን ግን ይወዳል። የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ይህ ዓይነት መንፈስ ሊኖራቸው ይገባል። ክርስቲያናዊ ፍቅር ለመገሰጽ የማይቸኩል፣ ንስሐ የመግባትን ምልክት ፈጥኖ የሚረዳ፣ ይቅር ለማለት፣ ለማበረታታት፣ የተሳሳተን ሰው ወደ ቅድስና ለመመለስና ከቅድስና መንገድ እንዳይወጣ ለማድረግ ዝግጁ ነው።"*—The Desire of Ages, p. 462.

# የግል የግምገማ ጥያቄዎች | አርብ ሚያዚያ 24

1. ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ለየሱስ ያዘጋጁትን ወጥመድ ግለጽ።
2. ግብዞች አይሁዳውያን ለህግ አክብሮት ያሳዩት እንዴት ነው?
3. ከሳሾቹ አይሁዶች ስለ ራሳቸው ምን እንዲያምኑ ተገደዱ?
4. በደል የደረሰባት ሴት ያገኘችሁን ተስፋ ግለጽ።
5. ከተሳሳቱ ነፍሳት ጋር በምንገናኝበት ጊዜ የሱስን መምሰል የምችለው እንዴት ነው?

ሰንበት፣ ግንቦት 02፣ 2017

6ኛ ትምህርት

# የሱስ የአለም ብርሃን

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "ደግሞም የሱስ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።" (ዮሐንስ 8፡12)**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 1, pp. 405–409.**

"በፀሐይ ዙሪያ የሚገኙ ጨረቃና ከዋክብት ከፀሐይ የሚያገኙትን ብርሃን በማንፀባረቅ እንደሚያበሩልን ሁሉ በዓለማችን የሚገኙ ሊቃውንት እውነትን እስካስተማሩ ድረስ የጽድቅ ፀሐይ ከሆነው ብርሃን ተቀብለው ያንፀባርቃሉ። እያንዳንዱ የሚፈልቀው ሐሳብ፣ እያንዳንዱ የዕውቀት ብልጭታ የዓለም ብርሃን ከሆነው አምላክ የሚመነጭ ነው።"—Education, p. 14.

## 1. ፍጥረትን ማስታውስ — እሁድ፣ ሚያዚያ 26

### ሀ. እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፍጥረት ቀን ምን ፈጠረ? ዘፍጥረት 1:3-5

"በመጀመሪያ እግዚአብሔር በቃሉ ዓለምን ሲፈጥር በጨለማው ላይ ብርሃን ወጣ።"—The Desire of Ages, p. 464.

### ለ. እንደ ተራ ተመልካች ሳይሆን ንቁ ተሳታፊ ሆኖ ዓለም ሲፈጠር ማን ነበር? ዘፍጥረት 1:1፣ 2፤ ዮሐንስ 1:1፣ 2፤ ቆላስይስ 1፡16

"በመጀመሪያ እግዚአብሔር በፍጥረት ሥራ ሁሉ ተገለጠ። ሰማያትን የዘረጋው፣ ምድርንም የመሰረተው ክርስቶስ ነው። . . . ምድርን በውበት፣ አየሩንም በዜማ የሞላው እርሱ ነው። በምድር ላይ፣ በአየር፣ በሰማይም ባሉት ነገሮች ሁሉ ላይ የአብ የፍቅር መልእክት ተጽፏል።"—Ibid., p. 20.

"ዓለማት ሁሉ በሕዋው ውስጥ እንዲቀዩ ያስቻላቸው እጅ በቅደም ተከተላቸውም በሥነ-ሥርዓት እንዲኖሩ አድርጐ የያዘ ያ እጅ በእግዚአብሔር ፍጥረተ-ዓለም ዩኒቨርስ ሁሉ ያሉትን ነገሮች እንቅስቃሴአቸው ሳይደክም እንዲቀጥል ያስተካከለ ያ እጅ ነው ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ የተቸነከረው።"—Education, p. 132.

## ሀ. የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ እንዴት ተመሩ? ዘጸአት 13:21፣ 22 በደመና ዓምድ እና በእሳት ዓምድ ውስጥ የተሸፈነውን መገኘት ግለጽ? ዘጸአት 13:21 (የመጀመሪያ ክፍል)፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1-4

"እግዚአብሔር ለሕዝቡ በተገለጠበት ጊዜ ሁሉ ብርሃን እርሱ የመገለጡ ምልክት በመሆን አገልግሎአል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በቃሉ ዓለምን ሲፈጥር በጨለማው ላይ ብርሃን ወጣ። የእሥራኤልን ሠራዊት ይመራ በነበረው የደመናና የእሳት አምድ ውስጥ ብርሃን ነበር።"—The Desire of Ages, p. 464.

## ለ. ክርስቶስ ከእስራኤላዊያን ጋር በምድረ በዳ ስለነበረው መገኘት የተጻፈው ምንድን ነው—አምላክስ ለሕዝቡ ምን ጥበቃ እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል? መዝሙር 105:39፤ ኢሳይያስ 4:5፣ 6

"ውብና አጽናኝ ከሆኑት የኢሳይያስ መልእክቶች ውስጥ አንዱ እንደሚነግረን በመጨረሻ ላይ ከክፉ ኃይላት ጋር በሚደረገው ታላቅ ፍልሚያ --የደመናና የእሳት አምድ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ጥንቃቄ እንደሚወክል ይነግረናል።"—Patriarchs and Prophets, p. 283.

## ሐ. ክርስቶስ በሲና ራሱን የገለጠው እንዴት ነው—ሙሴና ሕዝቡስ ምን ምላሽ ሰጡ? ዘጸአት 19:16–18፤ 20:18፣ 19፤ ዕብራውያን 12፡21

"በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት የጌታ ክብር እንደሚባላ እሳት ሆኖ በተራራው ጫፍ ላይ ተገለጠ። . . . የእግዚብሔር በስፍራው መገኘት ሕዝቡን በፍርሐት እንዲርድ ስላደረጋቸው፣ በእግዚአብሔርም ፊት በግምባራቸው ተደፉ።"—Ibid., p. 304.

"ሟች የሆነው የሰው ልጅ መሸከም እስከማይችል ድረስ የክርስቶስ መገኘት መገለጥ በጣም የከበረ ነበር። በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የተወደደው ሙሴ፣ 'እጅግ ፈርቻለሁ፣ እንቀጠቀጥማለሁ' ብሎ ጮኸ። አምላክ ግን ይህን ታላቅ ክብር እንዲቋቋምና ሕዝቡም ትኩር ብለው ማየት እስከማይችሉት ድረስ የሚያንጸባርቅ የብርሃኑ ነጸብራቅን ከተራራው ላይ ሲመለስ በፊቱ እስኪገልጥ ድረስ ብርታትን ሰጠው።"—Sons and Daughters of God, p. 225.

## ሀ. ክርስቶስ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ መገኘቱን ያሳየው እንዴት ነው? ዘጸአት 40:34፣ 35

"የእስራኤል ማሕበረሰብ የተጠናቀቀውን ቅዱስ ሥራ በታላቅ ጉጉት ተሰባስበው ተመለከቱ። ትዕይንቱን በታላቅ አክብሮትና እርካታ እያሰላሰሉ እያለ የደመና አምድ የመገናኛ ድንኳኑን ሸፈነ "የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ"። መለኮታዊው ክብር በመገለጡ ሙሴ እንኳ ለጊዜው ሊገባ አልቻለም ነበር። ሕዝቡ የእጆቻቸው ሥራ ተቀባይነት በማግኘቱ በጥልቅ ስሜት ተዋጡ። ድምጾቻቸውን ከፍ አድርገው ደስታቸውን እንዳይገልጹ ጽኑ ፍርሃት አድሮባቸው ነበር። እግዚአብሔር እራሱን ዝቅ አድርጎ ከእነርሱ ጋር በማደሩ ጥልቅ የምስጋና ቃላት በማንሾካሾክ የልባቸውን ሐሴት በደስታ እንባ ገለጹ።"—Patriarchs and Prophets, pp. 349, 350.

"ከምህረት መክደኛው በላይ የመለኮትን ህልዎት አመላካች የሆነው አምላካዊ ክብር (Shekinah) ይገኛል። አምላካዊው ፈቃድ በኪሩቤል መካከል ተገልጾአል። መለኮታዊ መልእክት አንዳንድ ጊዜ ከሰማይ --ከደመና ውስጥ በድምፅ ለሊቀ ካኅኑ ይመጣ ነበር። አንዳንድ ጊዜ አምላካዊውን አዎንታን ወይም ተቀባይነት ለማሳየት በቀኝ በኩል ባለው መልአክ ላይ ብርሃን ያርፋል። በተቃራኒው አለመስማማትን ወይም ተቃውሞን ለማሳየት ደግሞ በግራ በኩል ባለው መልአክ ላይ ደመና ወይም ጥላ ያጠላል።—Ibid.

## ለ. በኋላ ቤተ መቅደሱ ሲመረቅ (አገልግሎት ሲጀምር) ምን ተከሰተ? 2ኛ ዜና 7፡1

ለሙሴም በተራራው ላይ በኋላም በእግዚአብሔር ለዳዊት እንደ ተገለጠው ምሳሌ እጅግ ያማረ መቅደስ ተሠራ። ምድራዊው መቅደስ እንደ ሰማያዊ ተሠራ። ሰሎሞን በቃልኪዳኑ ታቦት አናት ላይ ካሉት ኪሩቤሎች በተጨማሪ ሌሎች ሁለት ትልልቅ መላእክትን ሠራ፤ በታቦቱ ጫፍና ጫፍ ላይ አቆማቸው፣ ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጠብቁትን የሰማይ መላእክትን የሚያመለክቱ ነበር። የዚህን ማደሪያ ውበት እና ግርማ መግለጽ አይቻልም። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዳለ፣ የቃልኪዳኑን ታቦት በታላቅ ክብር፣ በቅዱስ ሥርዓት ተሸክመው በስፍራው ከቆሙት ከከበሩ ኪሩቤሎች ክንፎች በታች አስቀመጡት።

"ቅዱሳን መዘምራን በድምፃቸው በአንድነት በማዘም፣ በሁሉም ዓይነት የዜማ መሣሪያዎች፣ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። በድምጻቸው በአንድነት እና በዜማ መሣሪያዎች፣ በመቅደሱ ውስጥ ሲዘምሩ፣ ድምጻቸውም በኢየሩሳሌም በአየር ላይ ሲሰማ፣ የእግዚአብሔር ክብር ደመና ቀድሞ ድንኳኑን እንደሞላው ሁሉ ቤቱን ሞላዉ።" ካህናቱም ከመቅደሱ በወጡ ጊዜ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው፥ የእግዚአብሔርም ክብር ስለ ሞላ ካህናቱ ከደመናው የተነሣ ለማገልገል መቆም እስኪሳናቸው ድረስ የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶ ነበርና።"—Spiritual Gifts, vol. 4a, pp. 113, 114.

## ሀ. በዮሐንስ 8፡12 ላይ ያለው ታላቅ ተስፋ የሚሰጠን የክርስቶስ መልእክት የትኛው ነው?

“የዚህ እውነት መረዳት የነበራቸውና ያንን እውነት በማወጅ ተግባር ላይም የተሰማሩት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎች አልነበሩም። እነዚህ [መሪዎች] ታማኝ ጠባቆች ቢሆኑ፣ በትጋትና በፀሎት ውስጥ ሆነው መጽሐፍ ቅዱስን የሚመረምሩ ቢሆኑ ኖሮ፣ የሌሊቱን ሰዓት ባወቁት ነበር፤ በቅርብ ሊሆኑ ያላቸውን ክስተቶች ትንቢቶቹ ይገልጡላቸው ነበር። ይህንን ደረጃ ግን አልያዙም ነበርና መልእክቱ የተላለፈው በሌላ መደብ ነበር። … እግዚአብሔር ከሰጠው ብርሐን ራሳቸውን የሚያገሉ፣ ወይም ሊደርሱበት በሚችሉበት ደረጃ ሆነው ሳለ ቸል የሚሉት እነርሱ በጨለማ ውስጥ ይተዋሉ።—The Great Controversy, p. 312

“ጌታ እጅግ የበለጸገ፣ የተትረፈረፈ፣ አስደሳች ተሞክሮ እንዲኖረን ሁሉንም ዝግጅት አድርጓል። ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ ሲጽፍ፡- “በእርሱ ሕይወት ነበረች። ሕይወትም የሰው ልጅ ብርሃን ነበረች።” ሕይወት ከብርሃን ጋር የተቆራኘ ነው፣ ከጽድቅ ፀሐይ ብርሃን ካላገኘን፣ በእርሱ ምንም ሕይወት አይኖረንም። ነገር ግን ይህ ብርሃን ለእያንዳንዱ ነፍስ ተዘጋጅቷል፣ ጨለማ የሚመጣብን ከብርሃን ስንወጣ ብቻ ነው። የሱስ “የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም” ብሏል። በአለም ውስጥ ያለ ብርሃን፣ ህይወት ሊኖር አይችልም። ፀሀይ ብርሃኗን ባታወጣ፣ የሁሉም እፅዋትና እንስሳት ህይወት ሁሉ መጨረሻ ይመጣ ነበር። ይህ የሚያሳየው እራሳችንን በጽድቅ ፀሃይ ጨረር ስር ካላደረግን መንፈሳዊ ህይወት ሊኖረን እንደማይችል ነው። አንድ የአበባ ተክል በጨለማ ክፍል ውስጥ ካስቀመጥን ብዙም ሳይቆይ ይደርቅና ይሞታል፤ ልክ እንዲዚሁ እኛም ያለንን መንፈሳዊ ህይወት በጥርጣሬ እና በጨለማ ከባቢ አየር ውስጥ በመኖራችን እናጣለን።”—Sons and Daughters of God, p. 281.

## ለ. ወደ የሱስ ስንዞር ምን ማረጋገጫ እናገኛለን? 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡ 18

“ብሩህ ጨረሯ ውበቷን እና ቀጥ ያለ አቋሟን እንድትጠብቅ እንድረዳት አንዲት የአበባ ተክል ወደ ፀሀይ እንደምትዞር ሁሉ፣ እኛም የሰማይ ብርሃን በላያችን ላይ እንዲያበራ፣ ባህሪያችን እንዲያሳድግ እና ልባዊና በእግዚአብሔር ዓላማ ጸንቶ የመኖር ተሞክሮ እንድሰጠን የክርስቶስ ተከታዮች ወደ ፅድቅ ፀሀይ ዘወር ማለት አለብን።”—Ibid., p. 26.

“የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ብቻ አላማዬ ያለ፣ ለተሰጠውም ብርሐን በትጋት ትኩረት የሚሰጥ እርሱ ታላቅ ብርሐን ይቀበላል። ወደ እውነት ሁሉ ይመራው ዘንድ፣ ለዚያ ነፍስ፣ ባለሰማያዊ ነፀብራቅ ኮከብ ይላክለታል።”—The Great Controversy, p. 312.

## 5. በልባችን ውስጥ ይበራል



### ሀ. ጳውሎስ ስለ ዓለም ብርሃን በሰጠው አበረታች ማጣቀሻ እንዴት ልንበረታ እንችላለን? 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6

"የእግዚአብሔር የከበሩ ሐሳቦች አእምሮአችሁን ይግዙ። ሕይወታችሁ ከየሱስ ሕይወት ጋር በተሰወሩ አገናኞች የተሰፋ ይሁን። በልባችሁ ውስጥ ከጨለማ ብርሃን እንዲበራ ወዶ ይብራ ያለው በየሱስ ክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን ሊሰጣችሁ ይፈልጋል። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ነገሮች ወስዶ ያሳያችኋል፣ ወደ ታዛዥ ልብም ሕያው ኃይል እንዲሆኑ ያስተላልፋል። ክርስቶስ ወደ ማለቂያ የሌለው ጫፍ ይመራል። ከመጋረጃው ባሻገር ያለውን ክብር ትመለከታለህ፣ በዚህም ስለ እኛ ስለሚማልደው ስለእርሱ ብቃት ለሰዎች ትገልጣለህ።"—Christ's Object Lessons, p. 149.

"በሰው ዘር የሚገለጠው የራሱ ክብር መንግሥተ ሰማያትን ወደ ሰዎች ያቀርባታል ስለዚህም የውስጡን ቤተመቅደስ የሚያስጌጠው ውበት አዳኝ በሚኖርበት ነፍስ ሁሉ ውስጥ ይታያል። ሰዎች በክርስቶስ ክብር ይማረካሉ። በዚህ መንገድ ከዳኑት ከብዙ ነፍሳት የውዳሴ እና የምስጋና ጅረት፣ እንዲሁም ክብር ወደ ታላቁ ሰጭ ይመለሳል።

"ብርሃንሽ መጥቶአልና፥ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፥ አብሪ። ኢሳ 60፡1 ሙሽራውን ለመገናኘት ለሚወጡት ሁሉ ይህ መልእክት ተሰጥቷል። ክርስቶስ በኃይልና በታላቅ ክብር ይመጣል። ከራሱና ከአብ ክብር ጋር ይመጣል። ከቅዱሳን መላእክት ሁሉ ጋር አብሮ ይመጣል። ዓለም ሁሉ በጨለማ በሚዘፈቅበት በዚያን ጊዜ፣ በቅዱሳን ማደሪያ ሁሉ ብርሃን ይሆናል። እነሱ የዳግም ምጻቱን የመጀመሪያውን ብርሃን ያያሉ። የማይደበዝዝ ብርሃን ከግርማው ይበራል፣ አዳኙ ክርስቶስ እርሱን ባገለገሉት ሁሉ ይደነቃል። ክፉዎች ከፊቱ ሲሸሹ የክርስቶስ ተከታዮች ደስ ይላቸዋል።"—Ibid., pp. 420, 421.

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች



1. መጽሐፍ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ ስለ አብ፣ ስለወልድና ስለመንፈስ ቅዱስ ምን ያስተምራል?
2. የሱስ ራሱን በምድረ በዳ ለሕዝቡ እንዴት እንደገለጠ ግለጽ።
3. የክርስቶስ ብርሃን በማደሪያው እና በቤተ መቅደሱ ውስጥ የበራው እንዴት ነው?
4. የሱስ በቤተ መቅደሱ ሲመረቅ ራሱን ያሳየው እንዴት እንደሆነ ግለጽ።
5. ክርስቶስ ለእኛ እና በእኛ በኩል ራሱን የገለጠው እንዴት ነው?

# ብርሃኑ ችላ ተባለ ወይስ ተንጸባርቀ?

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው? (መዝሙረ ዳዊት 27:1)**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church, **vol. 7, pp. 18–28.**

*ክርስቶስ «ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደዓለም ይመጣል፡ ፡» ዮሐ 1፡9 እያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር በክርስቶስ የሱስ ሕይወት እንደሚያገኝ ሁሉ እያንዳንዱ ነፍስም በእርሱ አማካይነት ከመለኮት ኃይል ከሚወጣው ብርሃን ጨረር ታገኛለች።"*—Education, p. 29.

## 1. የተተነበየው ብርሃን

**እሁድ፣ ግንቦት 03**

**ሀ. መንፈስ ቅዱስ በኢሳይያስ በኩል ስለየሱስ የተናገረው እንዴት ነው? ኢሳ 49፡6**

**ለ. የሱስን ለአምላክ ለመወሰን ወደ ቤተ መቅደሱ በቀረበ ጊዜ ስምዖን የገለጸው እንዴት ነው? ይህስ ስለ ምን ነገር እንድናስብበት ይገፋፋናል? ሉቃስ 2፡32።**

*"አረጋዊዩ ስምዖን የሱስ ይህን ትምህርት በሰጠበት ቤተ መቅደስ ውስጥ ሆኖ ስለ የሱስ «እርሱ ለአረማውያን እውነትን የሚገልጥ ብርሃን ይሆናል፤ ለሕዝብህም ለእሥራኤል ክብር ነው» በማለት ተናግሮ ነበር። ሉቃ.2:32። ይህን በተናገረ ጊዜ ስምዖን እሥራኤላውያን የሚያውቁትን ትንቢት ስለ የሱስ መጥቀሱ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ አማካይነት "ለአንተ ለአገልጋዬ ያዘጋጀሁልህ ታላቅ ሥራ አለ፣ ይኸውም ከጥፋት ለተረፉት የእሥራኤል ሕዝብ እንደገና የታላቅነትን ክብር መስጠት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ዓለም በመላው ይድን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ ብርሃን አድርጌሃለሁ» በማለት ተናግሮ ነበር። ኢሳ.49:6። ይህ ትንቢት የተነገረው ስለ መሲሑ መሆኑ ይታወቅ ስለነበር የሱስ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» ባለ ጊዜ እርሱ ይጠበቅ የነበረው መሲሕ መሆኑን እንደተናገረ ሕዝቡ በትክክል ገብቷቸዋል።"*—The Desire of Ages, p. 465.

*"አ! ይህ የቤተልሔም አስደናቂ ታሪክ ምን አይነት ትምህርት ነው! አለማመናችን፣ ኩራታችንና አንዳች-አይጎድለኝም ባይነታችንን እንዴት አድርጎ ይወቅሳል! በሚያስከስሰው ቸልተኝነታችን፣ የዘመኑን ምልክቶች ማወቅ ተስኖን የመጎብኘታችን ቀን ሳናውቀው እንዳንቀር፣ ጥንቁቅ እንድንሆን እንዴት አድርጎ እጅግ ያሳስበናል!"*—The Great Controversy, p. 315.

## ሀ. የአይሁድ መሪዎቾ ለክርስቶስ ተልእኮ ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 1:11፤ 8፡13።

*“መላው የክርስቶስ ህይወት እና ትምህርቶቹ ቀጣይነት ያለው የትህትና፣ የጎነት፣ የመልካምነት እና ራስን የመካድ ትምህርቶች ነበሩ። ይህ በራስ ጽድቅ ለሚያምኑ ለአይሁዶች የማያቋርጥ ተግሣጽ ነበር። ከነሱ ይልቅ የሕዝቡን ቀልብ እየሳቡ ስላሉ ስለ ክርስቶስ ድንቅ ሥራ በቅናት ሲናገሩ ያበዱ እስኪመስሉ ድረስ ሰይጣን መርቷቸዋል። እሱ አስመሳይ ነው ብለው ራሳቸው እንዲያምኑ እንዲሁም እሱን ለማጥፋት የሚጥሩበት ማንኛውም መንገድ ቢሆን መልካም እንደሆነ እንዲያምኑ አድርጓቸዋል።”*—Spiritual Gifts, vol. 4a, p. 117.

## ለ. የሱስ ለማያምኑት ፈሪሳውያን ምን ግልጽ ማብራሪያ ሰጥቷቸዋል—ነገር ግን እነሱ ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 8፡14-18

*“[ፈሪሳውያን] የክርስቶስን መለኮታዊ ባሕርይና ተልእኮ አላውቁም ነበር፣ ምክንያቱም መመርመር መብትና ግዴታቸው የሆነዉን መሲሑን በሚመለከት የተነገሩትን ትንቢቶች እነሱ ግን አልመረመሩም ነበር። ከእግዚአብሔር እና ከሰማይ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም፣ ስለዚህም የአለምን አዳኝ ስራ አልተረዱም፣ በዚህም ምንም እንኳን የሱስ አዳኝ መሆኑን በጣም አሳማኝ ማስረጃ ቢሰጣቸውም፣ ለመረዳት አእምሮአቸውን ለመክፈት አልፈለጉም። በመጀመሪያ ልባቸውን እርሱን በመቃወም አጠነከሩ፣ እናም የእርሱን አምላክነት የሚያረጋግጡበትን ጠንካራ ማስረጃ ለማመን ፍቃደኛ አልነበሩም፣ እናም በዚህ ምክንያት፣ እርሱን ላለማመን እና ላለመቀበል እስኪወስኑ ድረስ ልባቸው እየደነደነ ሄደ።”*—The Spirit of Prophecy, vol. 2, pp. 354, 355.

## ሐ. የሱስ በራሱ እና በማያምነው ፈሪሳዊያን መካከል ምን ልዩነት እንዳለ ተናግሯል? ዮሐንስ 8፡19-23

## መ. የአይሁድ ገዥዎች ክርስቶስን አለመቀበል የሚያስከትለው ገዳይ የሆነ ውጤት ምን ነበር? ዮሐንስ 8:24፤ ማቴዎስ 23፡38

## ሀ. ፈሪሳውያን በኃጢአታቸው ሊሞቱ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ የሱስን ምን አሉት? ለምንስ? ዮሐንስ 8፡25 (የመጀመሪያ ክፍል)።

"የተናገረውን ከቁም ነገር ያልቆጠሩ በመምሰል «አንተ ማነህ?» ብለው ጠየቁት። ይህን ያሉበት ምክንያት ክርስቶስ ነኝ እንዲል ለማድረግ ነበር። የየሱስ ሁኔታና ሥራ ሕዝቡ ይጠብቀው ከነበረው የተለየ ስለ ነበር እነዚህ መሰሪ ጠላቶቹ በቀጥታ መሲሕ መሆኑን ቢናገር ሕዝቡ እንደ አታላይ ቆጥረው ችላ ይሉታል የሚል ግምት ነበራቸው።"—The Desire of Ages, p. 465.

## ለ. ከአብ ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት በመግለጥ አዳኛችን እንዴት መለሰላቸው? ዮሐንስ 8፡25 (የመጨረሻው ክፍል)፣ 26–29

"ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ሕግ መሠረታዊ ሥርዓቶች ታማኝ ከመሆን ፈቀቅ አላለም። የአባቱን ፈቃድ የሚጻረር ነገር አላደረገም። በመላእክት፣ በሰዎች እና በአጋንንት ፊት እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ሁል ጊዜ አደርጋለሁ በማለት ከማንኛውም ከሰዉ ዘር ከንፈር ቢወጣ ስድብ ቃል ሊሆን የሚችለውን ቃል እርሱ ግን ሊናገር ይችላል። ዮሐንስ ወንጌል 8፡29። ቀን በቀን ለሦስት ዓመታት ጠላቶቹ ተከታተሉት፣ በባህሪው ውስጥ ትንሽ እድፍ እንኳን ለማግኘት ይሞክሩ ነበር። ሰይጣን፣ ከክፉ ተባባሪው ጋር፣ ሊያሸንፈው ፈለገ። ነገር ግን የሚያሸንፉበትን ምንም አላገኙበትም። ሰይጣናት እንኳ፡ 'አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነህ' ብለው እንዲናዘዙ ተገድደዋል።"—Testimonies for the Church, vol. 8, p. 208.

## ሐ. የክርስቶስን ከአባቱ ጋር ያደረገውን የዕለት ተዕለት ጉዞ እና ያንን ተሞክሮ እንዴት ማንጸባረቅ እንዳለብን ግለጽ። ዮሐንስ 15:10፤ ኤፌሶን 2፡4-6

"የሱስ በሰው ተፈጥሮ ሆኖ እንደተመላለሰ እንዲሁ የእግዚአብሔርም ተከታዮቹ እንዲሆኑ ነው። በእሱ ጥንካሬ አዳኝ የኖረበትን የንጽህና እና የቅድስና ህይወት መኖር አለብን።"—Ibid., p. 289.

"የአዳኙ በምድር ላይ የኖረበት ህይወት፣ ምንም እንኳን በተጋድሎ መካከል ቢኖርም፣ የሰላም ህይወት ነበር። የተቀጡ ጠላቶች ዘወትር ያሳድዱት ሳሉ እሱ ግን፡- "የላከኝ ከእኔ ጋር ነው፤ አብ ብቻዬን አልተወኝም፤ ሁልጊዜ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁና" አለ። ዮሐንስ ወንጌል 8፡29 የትኛውም የሰው ወይም የሰይጣን ቁጣ ከአምላክ ጋር ያለውን ፍጹም ኅብረትና መረጋጋት ሊረብሽ አይችልም።"—Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 15, 16.

## ሀ. ክርስቶስ ለፈሪሳውያን ጠቃሚ የሆኑ እውነቶችን በተናገረበት ወቅት የተናገራቸው ቃላት ቅን አድማጮችን ልብ የነካው እንዴት ነው? ይህስ ዛሬ እኛን ሊያበረታታን የምችለው ለምንድን ነው? ዮሐንስ ወንጌል 8፡30

"ክርስቶስ በተረጋጋ፣ አስተዋይ በሆነ መንገድ እንዴት መሥራት እንዳለበት እና እሱን ወደ ኩነኔ ለማምጣት የሚያወጡትን እቅዳቸውን እንዴት ከንቱ እንደሚያደርግ ተረድቷል። የጌታ ቃላቶች ወደ እላማው እንደሚነደፉ እንደተሳሉ ፍላጻዎች ነበሩና፣ የከሳሾቹን ልብ ያቆስሉ ነበር። ክርስቶስ ሰዎችን ባነጋገረ ቁጥር፣ ሰሚዎቹ በዕድሜ ትልቅም ይሁኑ ትንሽ፣ ቃላቱ በአንዳንድ አድማጮቹ ነፍስ ላይ የማዳን እርምጃን ይወሰዱ ነበር። ከክርስቶስ አንደበት የወጣ ማንኛዉም መልእክት በከንቱ አልጠፋም። የተናገራቸው ቃላት ሁሉ በሰሙት ላይ አዲስ ሃላፊነትን ይጥሉ ነበር። የመጨረሻውን የምሕረት መልእክት ለዓለም የሚያደርሱ፣ እውነትን በቅንነት የሚያቀርቡ፣ በእግዚአብሔር ኃይል የሚታመኑ አገልጋዮች፣ ጥረታቸው ከንቱ ይሆናል ብለዉ በፍጹም መፍራት የለባቸውም። የእውነት ፍላጻ ወደ እላማው አልሄደም፣ የሰሚውንም ነፍስ አልወጋም ሊል የሚችል ማንም የለምና። ምንም እንኳን የእውነትን ፍላጻ አካሄድ የሰው ዓይን ሊያየው ባይችልም፣ የቆሰለውንም ነፍስ ጩኸት የሰዉ ጆሮ ባይሰማም፣ እውነት ግን በጸጥታ ወደ ልብ መንገዱን ትገሰግሳለች። እግዚአብሔር ለነፍስ ተናግሯል፣ እናም በመጨረሻው የፍርድ ቀን የእግዚአብሔር አገልጋይ ክብር ለሚገባው ለክርስቶስ ክብርን ለመስጠት ከማዳን የጸጋ ሽልማቶች ጋር ይቆማል። በሰውር የሚያይ አምላክ፣ እውነትን በስሙ ለተናገሩት በግልጥ ይከፍላቸዋል።"—The Signs of the Times, February 6, 1896.

## ለ. ከአገልጋዮች በተጨማሪ የሰማይን ብርሃን በማንፀባረቅ የሚባረከ ማን አለ? መዝሙር 27:1፤ 147:15፤ ኢሳይያስ 55:10፣ 11

"ለአገልግሎት ያልተጠሩ ሰዎች እንደ ችሎታቸው መጠን ለመምህሩ እንዲሠሩ መበረታታት አለባቸው። በአሁኑ ጊዜ ያለ ምንም ሥራ የተቀመጡ በሙቶዎች የሚቆጠሩ ወንዶች እና ሴቶች ለአምላክ አስፈላጊ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ። እውነትን ወደ ጓደኞቻቸው እና ጎረቤቶቻቸው ቤት በማድረስ፣ ለመምህሩ ታላቅ ስራ ሊሰሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላም። ልክ እንደሌሎች ጥልቅ የሆነ ትምህርት ባይማሩም እንኳ እሱ ራሳቸውን የሰጡ ትሑት ክርስቲያኖችን ይጠቀማል። እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ እሱን እንዲያገለግሉ ይደረጉ። ትሑት፣ ልባም እና አምላካዊ ባሕርይ የተላበሱ ከሆኑ—አንድ የተቀባ አገልጋይ ማድረግ ከሚችለው በላይ የቤተሰብን እውነተኛ ፍላጎት ለማሟላት ብዙ ማድረግ ይችላሉና።"—Testimonies for the Church, vol. 7, p. 21.

## 5. ባርነት ከነጻነት ጋር ሲነጻጸር

**ሐሙስ፣ ግንቦት 07**

### ሀ. የሱስ እሱን ለተቀበሉት አይሁዶች ምን ብሏቸዋል? ዮሐንስ 8:31፣ 32 በአንጻሩ ግን የማያምኑት ከኃጢአት ነፃ የሚያደርገንን ብቸኛውን ሁኔታ ማየት የተሳናቸው እንዴት ነው? ዮሐንስ ወንጌል 8፡33-36

“[ፈሪሳውያን] የክፉ መንፈስ ተገዥ ስለነበሩ ከሁለም በከፋ ባርነት ሥር ነበሩ።

“ራሱን ለእግዚአብሔር ለማስረከብ ፈቃደኛ የማይሆን ነፍስ በሌላ ኃይል ቁጥጥር ሥር ነው። የራሱ አዛዥ አይደለም። ስለ ነፃነት ይናገር ይሆናል፤ ነገር ግን በጣም አሰቃቂ በሆነ ባርነት ሥር ነው ያለው። አእምሮውን ሰይጣን ስለሚቆጣጠረው የእውነትን ውበት ለማየት አይፈቀድለትም። ምንም እንኳን የራሴን የሕሊና ፍርድ ነው የምከተለው በማለት ራሱን ቢደልልም የጨለማውን መስፍን ፍላጐት ነው የሚፈጽመው። የሱስ የመጣው የኃጢአት ባርነትን እግር ብረት ሰብሮ ነፍስን ነፃ ለማውጣት ነው። …

“በማዳን ሥራ ማስገደድ የሚባል ነገር የለም። በውጫዊ ኃይል መጠቀምም የለም። በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት እያንዳንዱ ሰው ማንን ለማገልገል እንደሚፈልግ ራሱ እንዲወሰን ይደረጋል። አንድ ሰው ራሱን ለክርስቶስ በማስረከቡ ምክንያት በሚከሰተው ለውጥ ከፍተኛ የሆነ የነፃነት ስሜት ይፈጠራል። ኃጢአትን የመተው ሥራ የግለሰቡ ጉዳይ ነው። እርግጥ ነው ራሳችንን ከሰይጣን ቁጥጥር ነፃ ለማድረግ አቅም የለንም፣ ነገር ግን ከኃጢአት አርነት ለመውጣት ፍላጐት ሲያድርብንና ከእኛ ውጭና በላይየሆነ ኃይል ለማግኘት ስንጮህ ነፍሳችን መለኮታዊ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሞላና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በፍላጐት ይንቀሳቀሳል።

“ሰው ነጻነቱን ለማግኘት የሚያስችለው ብቸኛው ውል ከክርስቶስ ጋርአንድነት መፍጠር ነው። “እውነትም ነጻ ያወጣችኋል!» እውነቱም ክርስቶስ ነው። ኃጢአት በሰው ላይ ድል የሚጐናጸፈው አእምሮን በማዳከምና የነፍስን ነጻነት በመደምሰስ ነው። ለእግዚአብሔር መገዛት ማለት ወደ እውነተኛው ሰብአዊ ደረጃ ማለትም ወደ እውነተኛው ማዕረግና ሰብአዊ ክብር ተመልሶ መምጣት ማለት ነው። እንድንተዳደርበት የተደነገገ ልን መለኮታዊ ሕግ የነጻነት ሕግ ነው። ያዕ.2:12።”—The Desire of Ages, p. 466.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

**አርብ፣ ግንቦት 08**

1. ስምዖን ስለ የሱስ የተናገረውን ሐሳብ አስፈላጊነት ግለጽ።
2. ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በክርስቶስ ላይ የነበራቸውን አስተሳሰብ ግለጽ።
3. አይሁዳዊያን የሱስን በመቃወማቸዉ ምን ይደርስባቸዋል?
4. በዚያን ጊዜም ሆነ አሁን ቅን የሆኑ ነፍሳት ለክርስቶስ ምን ምላሽ ይሰጣሉ?
5. የ“ነጻነት” ጽንሰ-ሐሳብን በወንጌል እውነት ብርሃን አብራራ።

ሰንበት፣ ግንቦት 16፣ 2017

8ኛ ትምህርት

# የሱስ እና አብርሃም

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው።” (ዮሐ. 8፡56)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Christ’s Object Lessons, **pp. 269–271, 330–332;** Early Writings, **pp. 149–153.**

“[አብርሃም] ከመሞቱ በፊት መሲሑን ለማየት ይችል ዘንድ ከልቡ ጸለየ። ክርስቶስንም አየ።”—The Desire of Ages, p. 468.

## 1. የአብርሃም ልጆች

እሁድ፣ ግንቦት 10

**ሀ. ፈሪሳውያን ያለማቋረጥ የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው? ዮሐንስ 8:33፣ 39 (የመጀመሪያ ክፍል) ግን እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት ማረጋገጥ የሚቻለዉ በምንድነው? ዮሐንስ 8፡39 (የመጨረሻው ክፍል)፣ 56፤ ሮሜ 9፡6-8**

*“ፈሪሳውያን የአብረሃም ልጆች ነን ባዮች ነበሩ። የሱስ ግን ያ መብት ሊኖራቸው የሚችለው የአብርሃምን ሥራ ሲሠሩ ብቻ መሆኑን ነገራቸው። እውነተኛ የአብርሃም ልጆች የሆኑ ሁሉ እርሱ እንዳደረገው ለእግዚአብሔርታዛዥ የሆነ ሕይወት ይኖራሉ እንጂ ከአግዚአብሔር የተሰጠውን እውነት የሚናገርን ሰው ሕይወት ለማጥፋት አይሞክሩም። እነዚያ የኦሪት ሕግ ሊቃውንት በክርስቶስ ላይ ሲያሴሩ የአብርሃምን ሥራ መሥራታቸው አልነ በረም። በትውልድ ብቻ የአብርሃም ዘር መሆን ምንም ፋይዳ የለውም። እነዚህ ሰዎች የአብርሃም መንፈስ እንዲያድርባቸውና የእርሱንም ሥራ እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው ከእርሱ ጋር የሚያስተሳስራቸው መንፈሳዊ ግንኙነት እስካልኖራቸው ድረስ የአብርሃም ልጆች ሊሆኑ አይችሉም።*

*“ይህ መርሖ የክርስቲያኑን ዓለም ለረጅም ዘመን ሲያነታርክ ለኖረው የቤተ ክርስቲያን የመሪነት ሥልጣን አወራረስ ጥያቄ መፍትሔ ነው። የአብርሃም ዘር መሆን የሚረጋገጠው በሰምና በሥጋ ትውልድነት ላይሆን በባሕርይ ተመሳሳይነት ነው። እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን የመሪነት ሥልጣን አወራረስ የሚመሠረተው በሥልጣን ማስተላለፍ ላይ ሳይሆን በመንፈሳዊ ግንኙነት ላይ ነው። የሐዋርያትን ሥልጣን ለመረከብ ብቁ የሚያደርገው በሐዋርያት መንፈስ የታነጸ ሕይወትና እነርሱ ባስተማሩት እውነት ማመን ነው። ሰዎችን የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ተተኪ ለመሆን የሚያበቃቸው ይህ ነው።”*—The Desire of Ages, pp. 466, 467.

## ሀ. አይሁዳውያን የአብርሃም ዘር ቢሆኑም፣ ክርስቶስን ሲቃወሙ የማን ልጆች ሆኑ? ዮሐንስ 8፡41-44

*"የሱስ የአይሁዶችን የአብርሃም ልጅነት አላመነም። «እናንተ የምትሠሩት የአባታችሁን ሥራ ነው» አላቸው። እነርሱም በማፌዝ «እኛ በምንዝር የተወለድን ዲቃላዎች አይደለንም፣ አንድ አባት አለን፣ እርሱም እግዚአብሔር ነው» ሲሉ መለሱለት። እነዚህ ቃላት የየሱስን የአወላለድ ሁኔታ የሚነኩ ሲሆኑ በእርሱ ለማመን የጀመሩት ሰዎች በሚገኙበት የሱስን ለመበከል የተሰነዘሩ ነበሩ። የሱስ ግን የሰነዘሩበትን ጸያፍ የአሽሙር አነጋገርከምንም ሳይቆጥር «እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆንማ እኔን በወደዳችሁኝ ነበር፣ ምክንያቱም እኔ እዚህ ያለሁት ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቼ ነው» አላቸው።*

*"የእነዚህ ሰዎች ሥራ ሐሰተኛና ነፍስ ገዳይ ከሆነው ከሰይጣን ጋርየነበራቸውን ግንኙነት ይመሰክራል። ስለዚህ የሱስ «እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ። ፍላጐታችሁም የአባታችሁን ምኞት መፈጸም ነው። እርሱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ነፍሰ ገዳይ ነበረ። እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ... እኔ ግን እውነትን የምናገርስለሆንሁ አታምኑኝም» ሲል ነገራቸው። ዮሐ.8:44፣45። የሱስ በአይሁድ መሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያላገኘበት ምክንያት እውነትን በእርግጠኛነት ስለተናገረ ነው። እነዚያ እራሳቸውን ጻድቅ አድርገው ይቆጥሩ የነበሩት ሰዎች ያኮረፉት እውነቱ ስለተነገራቸው ነው። እውነት ስሕተታቸውን ስላጋለጠ፣ ትምህርታቸውንና ድርጊታቸውንም ስላወገዘ ተቀባይነት አጣ። ስሕተታቸውን አምነው ንስሐ ለመግባት እራሳቸውን ዝቅ ከማድረግ ይልቅ እውነትን ላለማየት ዓይኖቻቸውን መሸፈን መረጡ። ለእውነት ፍቅር አልነበራቸውም። እውነቱን ቢያውቁም የመቀበል ፍላጐት አልነበራቸውም።"*—The Desire of Ages, p. 467.

## ለ. የአብርሃም ልጆች የሚያደርገን ምንድን ነው? የአይሁድ መሪዎችስ እውነተኛ የአብርሃም ልጆች እንዳልሆኑ ያሳዩት እንዴት ነው? ገላትያ 3፡6–9፤ ዮሐንስ 8፡40

*"እናንተ ግን አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ ዳግመኛ ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና።" የባርነት መንፈስ የሚመነጨው በወግ (በስማዊ) ሀይማኖት መሰረት ለመኖር በመፈለግ የህግ ጥያቄዎችን በራሳችን ሃይል ለማሟላት በመታገል ነው። ለእኛ ተስፋ ያለን በአብርሃም ቃል ኪዳን ሥር ስንሆን ብቻ ነው፤ እርሱም በክርስቶስ የሱስ በማመን የሚገኘው የጸጋ ቃል ኪዳን ነው። ለአብርሃም የተሰበከለት፣ በእርሱም ተስፋ ያገኘበት ወንጌል ዛሬ ለእኛም የተሰበከልን፣ በእርሱም ተስፋ ያለንበት ወንጌል ነውና። አብርሃም የሱስን ተመልክቶ ነበር፤ እርሱም የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ ነው።"*—The Youth's Instructor, September 22, 1892

## ሀ. የየሱስ ጠላቶች ከነቁጣ አልባ ባሕርይው ጋር በተያያዘ መመለስ ያልቻሉት ጥያቄ ምንድነው? ዮሐንስ 8፡46 (የመጀመሪያ ክፍል)።

“ለአባቱ ትእዛዝ ፍጹም በመታዘዝ፣ በምድራዊ ህይወቱ ክርስቶስ ፍጹም ባህርይን አዳበረ። በሰው አምሳል ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ፣ ለሕግ ተገዥ ሆኖ፣ ለሰዎች ሕመማቸውን፣ ሐዘናቸውን፣ በደላቸውን እንደተሸከመ ሲገለጥ፣ በአንዳች ነጥብም ግን ኃጢአተኛ አልሆነም። ከፈሪሳውያን በፊት ‘ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው?’ ማለት ችሏል። በእርሱ ላይ አንድም የኃጢአት እድፍ አልተገኘበትም። ነውር የሌለው የእግዚአብሔር በግ ሆኖ በዓለም ፊት ቆመ።”—Sons and Daughters of God, p. 25.

“የሱስ በሰማይ፣ ባልወ ደቂት ዓለማትና በኃጢአተኛ ሰዎች ፊት ሕግን አክብሮ ኖረ። በመላእክት፣ በሰዎችና በአጋንንት ፊት ማንም ሊያስተባብለው በማይችል አኳኋንና በሌላ ሰው አንደበት ቢነገር የእግዚአብሔርን ስም እንደማርከስ የሚያስቆጥረውን «ዘወትር የማደርገው እርሱን (እግዚአብሔርን) ደስ የሚያሰኘውን ነገር» ነው ብሎ ለመናገር ቻለ።”—The Desire of Ages, p. 467, 468

## ለ. የሱስ የሰው ልጅ ተብሎ ከተነገረው በተጨማሪ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ ባሕርይ ምን ይናገራሉ? ዕብራውያን 4:15፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1:18፣ 19

“ሰዎች በክርስቶስ እንደ መሲህ አድርገው ያመኑት በሚታዩ ማስረጃዎች የተነሳ ወይም ከደም ግባቱ የተነሣ አልነበረም፣ ነገር ግን በሌላ በማንም ሊገኝ በማይችል በእርሱ ውስጥ ብቻ በተገኘው ከላቀ የጠባይ ባሕርይ የተነሳ ነው እንጂ።”—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 904.

## ሐ. በየሱስ ሕይወት እንዴት ልንነካ ይገባናል? ፊልጵስዩስ 2፡6-8

“አርአያችን እኛን ለማዳን አሰቸጋሪውን፣ እራስን የመካድና የመስዋዕትነት እንዲሁም የትህትና መንገድ አልሄደምን? እሱን ችግሮች አጋጥመውታል፣ የሚያበሳጩ ነገሮች አጋጥመውታል፣ እንዲሁም እኛን በማዳን ስራው ነቀፋና ስቃይ ደርሶበታል። ታዲያ የክብር ንጉስ እንድንሄድበት የመራንን መንገዱን ለመከተል እንቢ እንበልን? የቤዛችን መከራ ስናስታውስ በራሳችን የሥራ ድርሻ ውስጥ ስለሚደርስብን ችግር እና ፈተና ሊናማርር ይገባናል?”—Testimonies for the Church, vol. 3, p. 371.

## ሀ. የሁሉም እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ዓላማ ምንድን ነው? 1ኛ ጴጥሮስ 1:13-16

"*የእኛ ሥራ በተግባራችን መስክ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረው ሕይወት በእያንዳንዱ የባሕርይ ደረጃ ያገኘውን ፍጽምና ለማግኘት መጣር ነው።*"—That I May Know Him, p. 130..

## ለ. እዚህ ግብ ላይ እንዴት መድረስ እንችላለን? ዕብራውያን 12:1-4፤ ገላትያ 5:6 (የመጨረሻው ክፍል)፤ ፊልጵስዩስ 3:12–15፤ 4፡13።

"*ታላቁ መምህራችን የጌታችንና የመድኃኒታችን የየሱስ ክርስቶስ ፍጽምና ደረጃ ላይ መድረስ የምንችለው እንዴት ነው? የእሱን መስፈርት ማሟላትና ይህን ያህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለንን? አዎ እንችላለን፣ ያለበለዚያ ክርስቶስ እንዲህ እንድናደርግ ባላዘዘን ነበር። እርሱ ጽድቃችን ነው። በሰብአዊነቱ ከኛ በፊት ተመላልሶ የባህርይ ፍፁምነትን የምናገኝበትን መንገድ አሳየን። በፍቅር በሚሰራና ነፍስን በሚያነጻ በእርሱ ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል። የባህሪይ ፍፁምነት ክርስቶስ ለእኛ በሆነው ላይ የተመሰረተ ነው። በአዳኛችን ትሩፋቶች ላይ የማያቋርጥ ጥገኛ ከሆንን እና የእርሱን ፈለግ ብንከተል እንደ እርሱ ንጹሕና ርኩሰት የሌለን እንሆናለን።*"—Ibid

## ሐ. በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕና እንከን የለሽ መሆን የምንችለው እንዴት ነው? ሮሜ 5፡18-20፤ ዕብራውያን 10፡14

"ክርስቶስ ከተጸጸቱት በስተቀር ማንንም ይቅር አይልም፣ ይቅርታ የሚያደርግለትን ሰው ግን አስቀድሞ እንድጸጸት ያደርገዋል።"—Selected Messages, bk. 1, pp. 393, 394.

"ኃጢአተኛው ወደ ቀራንዮ ይመለከት፤ ልክ ህጻን ልጅ ባለ እምነት፣ ጽድቁን በመቀበል እና በምህረቱ በማመን፣ በክርስቶስ ትሩፋት ላይ ማረፍ አለበት። . . .

"ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ እንዲሞት የሚያደርግ ይህ—እንዴት የሚያስደንቅ፣ የማይመረመር ፍቅር—ምን ዓይነት ፍቅር ነው! የሕጉን ጠንከር ያለ የይገባኛል ጥያቄዎችን የምትረዳ ነገር ግን እጅግ የሚበዛውን የክርስቶስን ጸጋ ገና ያልተረዳች ነፍስ እንዴት ያለ ኪሳራ ላይ ናት!"—Ibid., p. 384.

## ሀ. ጥሪያችንን እና መመረጣችንን እንዴት እናረጋግጣለን? 2ኛ ጴጥሮስ 1:4-11፤ ራእይ 19፡8።

"*ያኔ እግዚአብሔር ከአዳም የፈለገውን ዓይነት ፍጹም መታዘዝን፣ እንከን የለሽ ጽድቅን፣ በዓይኑ ፊት ጉድለት የሌለበት ሆኖ መገኘትን ዛሬም ይፈልግብናል፡፡ ሕጉ የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን። የክርስቶስን ጽድቅ ወደ ዕለታዊው ተግባር ማምጣት የሚችል እምነት ከሌለን በስተቀር ይህን ማድረግ አንችልም።*"—Selected Messages, bk. 2, p. 381.

"*ሰይጣን እስከነገሰ ድረስ፣ ሕይወታችንም እስካለች ድረስ፣ ልንገዛው የሚገባን ራስ፣ ልናሸንፈው የሚገባን የኃጢአት ዝንባሌ አለ፣ ይህንን ማድረግ የምናቆምበት ቦታ አይኖርም፣ ሙሉ በሙሉ ደረስኩበት የምንልበት ነጥብም የለም። መቀደስ የዕድሜ ልክ ታዛዥነት ውጤት ነው።*"—The Acts of the Apostles, pp. 560, 561.

"*በእርሱ በማመን የመለኮታዊ ተፈጥሮ ተካፋዮች መሆን እና በዓለም ካለው በፍትወት ከመበስበስ ማምለጥ ዕድላችን እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። ያኔ ከኃጢያት ሁሉ፣ ከባሕርይ ጉድለት ሁሉ እንነጻለን። አንድም የኃጢያት ዝንባሌ ልንይዝ አይገባንም።* . . .

"*ከመለኮታዊ ተፈጥሮ ስንካፈል፣ በዘር የሚተላለፍና ያዳበርነውን የኃጢአት ዝንባሌዎች ከባህሪያችን ይቆረጣሉ፣ እንዲሁም ለበጎ ነገር ሕያው ኃይል እንሆናለን። ስለ መለኮታዊው መምህር ስንማር፣ በየቀኑ ከእርሱ ተፈጥሮ ተካፋይ በመሆን፣ የሰይጣንን ፈተናዎች በማሸነፍ ከእግዚአብሔር ጋር እንተባበራለን። ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንደሆነ ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ እንዲሆን እግዚአብሔር ይሠራል፣ ሰውም ለዚህ ዓላማ ይሠራል።* . . .

"*የማሸነፍ ኃይልን የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው። ቃሉን የሚሰሙና ትእዛዛቱን የሚታዘዙ ሰዎች ጻድቅ ባሕርያትን ለመመስረት ያስችላቸዋል።*"—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 7, p. 943.

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ግንቦት 15

1. ፈሪሳውያን በዘር ሀረጋቸው ላይ ተመስርተው የዘላለም ሕይወት ሊያገኙ ያልቻሉት ለምንድን ነው? ወይም ዛሬም ቢሆን የትኛውም ሰው ዘራቸውን ወይም ዲኤንኤ (ዘረመላቸውን) የመዳን ምልክት አድርገው ማመን የማይቻሉት ለምንድነው?
2. የአብርሃምን እውነተኛ ልጆች ባህሪያት ግለጽ።
3. የሱስ ስለ ባህሪይው ምን ማለት ችሏል?
4. በእያንዳንዱ ክርስቲያን ፊት ምን ዓላማ ተቀምጧል?
5. በእግዚአብሔር ፊት ፍጹምና ነውር የሌለን ሆነን ልንገኝ የምንችለው እንዴት ነው?




## የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ
## ሰንበት፣ ግንቦት 30፣ 2017

# በታሚል ናዱ፣ ህንድ ውስጥ ላሉ ሁለት አምልኮ ቤቶች



እንደ አርኪዮሎጂ (ታሪክ ቁፋሮ) ጥናት ማስረጃ መሠረት ከክርስቶስ ልደት በፊት 2600 ዓ.ዓ በከፍተኛ ከተሜነት የተስፋፋው የኢንዱስ ስልጣኔ ዛሬ ህንድ ተብሎ በሚታወቀው ክፍለ አህጉር ውስጥ ይገኝ ነበር። እዚህ ያለው ዋናው ሃይማኖታዊ ተጽእኖ ለረጅም ጊዜ ሂንዱዝም (79.8%)፣ ከዚያም እስልምና (14.2%)፣ ክርስትና (2.3%)፣ ሲክሂዝም (1.7%) እና ሌሎች ይጨምራል፡ ፡ ከ1920ዎቹ እና 1950ዎቹ ጀምሮ ከኤስዲኤ ሪፎርም እንቅስቃሴ ጋር የተወሰነ ግንኙነት እንዳለ ሪፖርቶች ቢኖሩም፣ ሰሜን ህንድ በኤስዲአርም አጠቃላይ ጉባኤ የውክልና ስብሰባ ላይ በይፋ የተወከለው በ1987 ነው።

በህንድ የደቡባዊው ዳርቻ -ታሚል ናዱ- በኢንዱስትሪ እና በእርሻ ውስጥ እንደ ሃይል ማዕከል ይቆጠራል። የጌታ ስራ እዚህ ላይ ከተመሠረተ ብዙ አመታትን አስቆጥሯል፣ ነገር ግን በዚህ ግዛት ውስጥ ከ72 ሚሊዮን በላይ የሆነዉን ሰፊውን ህዝብ ለማገልገል፣ ሰፊ ሥራ ያስፈልጋል።

በ2001 ዓ.ም በተካሄደዉ የሕንድ ሕዝብ ቆጠራ መሠረት የፓትቴዌራንፓቲ መንደር 7,744 ህዝብ ነበረው። አማካኝ የተማረ (ማንበብ የሚችል) ሰዉ በመቶኛ ሲሰላ 83% ነው፣ ከሀገር አቀፍ አማካይ 59.5% ከፍ ያለ ነዉ (ይህም ለሥነ ጽሑፍ ምቹ ነዉ)።

እዚህ አከባቢ ዋናው መተዳደሪያው ቡና ሲሆን ከዚያም ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ኮረሪማ፣ በርበሬ እና ሌሎች ቅመማ ቅመሞች ይከተላሉ። ፓላፓቲ ደግሞ 13,701 ህዝብ የሚኖርባት ትልቅ መንደር ነው።

ከፔሪያክላም የመጣ የወንጌል ሰባኪ ያላሰለሰ ሥራ፣ በተለይ በእነዚህ ሁለት አካባቢዎች የቤተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር እንዲጨምር ረድቷል። የተለያዩ ተግዳሮቶች በመኖራቸዉ በክራይ ቤቶች ውስጥ ለመቀጠል በጣም አስቸጋሪ አድርገውታል፣ ስለዚህ አሁን ባሉበት ሁኔታ፣ በፓቲቬራንፓቲ እና በፓላፓቲ መንደሮች ውስጥ ያሉ ወንድሞች የራሳቸው የአምልኮ ቦታ ያስፈልጋቸዋል።

ትንቢት መንፈስ ስለሕንድ በተላይ ሲናገር "በሚዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ፍቅሩ በክርስቶስ የተገለጠውን ያህል ሰምተው የማያውቁበት ቦታ እንደሆነ ይጠቅሳል። ይህንን እውቀት መቀበል መብታቸው ነው። የአዳኙ ምሕረት ከእኛ ጋር እኩል ይገባቸዋልና" ይላል።—Education, p. 263.

ስለዚህ በዓለም ዙሪያ ያሉ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ጌታ እዚህ እንዲበራ የብርሃን ማማዎችን ለመስራት በጎ ድጋፍ እንዲታደርጉ በአክብሮት እንጠይቃለን። "የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የማወጅና በእግዚአብሔር ህግ ላይ የተፈፀመውን ጥሰት በመጠገን፣ ለሚሰቃየው የሰው ልጅ ርህራሄን ማሳየት አለብን። ለእግዚአብሔር የላቀ ፍቅር ማሳየት አለብን፤ መታሰቢያውንም ከፍ ከፍ ማድረግ አለብን።"— Welfare Ministry, p. 32.

**አናመሰግናለን፣ እንዲሁም ጌታ ሰጦታዎቹንና ሰጭዎቹን ይባርክ!**

**ወንድሞቻችሁ እና እህቶቻችሁ ከፓትቬራንፓቲ እና ከፓላፓቲ**

ሰንበት፣ ግንቦት 23፣ 2017

9ኛ ትምህርት

# የሱስ እና ዓይነ ስውሩ ሰው

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “የሱስም። የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ አለ።” (ዮሐ. 9፡ 39)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church**, vol. 3, pp. 570–575.**

“በሰው ላይ መከራ የሚያመጣው ሰይጣን እንደሆነና አምላክም በምሕረቱ ሰዉን ከስቃይ እንደሚያድን የኢዮብ ታሪክ ያስረዳል።”—The Desire of Ages, p. 471.

## 1. የተሳሳተ መረዳት

እሁድ፣ ግንቦት 17

### ሀ. ደቀ መዛሙርቱ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ሲያዩ የሱስን ምን ጥያቄ ጠየቁት? ዮሐንስ 9:1፣ 2

### ለ. በአይሁድም ሆነ በደቀ መዛሙርቱ ስቃይን በተመለከተ ምን የተሳሳተ ሐሳብ ነበራቸው? ሰይጣንስ በዚህ የሚጠቀመው እንዴት ነው? ዮሐንስ 9፡34 (የመጀመሪያ ክፍል)።

“ሰው የኃጢአቱን ቅጣት በዚህ ዓለም እንደሚያገኝ በአይሁዶች ዘንድ በአብዛኛው ይታመንበት ነበር። እያንዳንዱ ደዌ የበሽተኛው ወይም የወላጆቹ ኃጢአት መቀጫ ነው ተብሎ ይታመን ነበር። ማንኛውም ስቃይየእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ እንደሚመጣ እሙን ነው፣ ነገር ግን ይህ እውነት ተዛብቷል። የኃጢአትና የኃጢአት ውጤት ሁሉ ጠንሳሽ የሆነው ሰይጣን ሰዎች ሕመምና ሞት ለኃጢአት መቀጫ እንዲሆን እግዚአብሔርበአምባገነንነት የወሰነው ነገር እንደሆነ አድርገው እንዲያምኑ አደረጋቸው። ስለዚህ ደዌ ወይም መቅሰፍት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት ችግር በተጨማሪ የትልቅ ኃጢአተኛነትን ቀንበር መሸከም ነበረበት።

“ስለዚህ አይሁዶች የሱስን ችላ የሚሉበት መንገድ ተዘረጋላቸው። «እኛ ልንሸከመው የሚገባንን መከራና ሕማም» የተሸከመውን ጌታ አይሁዶች «ከእግዚአብሔር የተላከ ቅጣት…ከመከራና ከሕማም የማይለይ የሐዘን ሰው» እንደሆነ አድርገው ስለገመቱት እርሱን ላለማየት ፊታቸውን ሸፈኑ።”—The Desire of Ages, p. 471.

## ሀ. የሱስ መከራንና ኃጢአትን በተመለከተ ብርሃንን የሰጠው በየትኛው ምላሹ ነው? ዮሐንስ 9፡3-5

"የየሱስ ደቀ መዛሙርት በኃጢአትና በስቃይ መካከል ስላለው ግንኙነት አይሁዶች እንደሚያምኑት ያምኑ ነበር። የሱስ የደቀ መዛሙርቱን ስሕተት ቢያርምም የሰውን ስቃይ መንስኤ ሳይገልጽ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ግን ነገራቸው። በዚያ ስቃይ ምክንያት የእግዚአብሔር ሥራ እንደሚገለጥ ነገራቸው። «በዓለም ላይ ሳለሁ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» አለ።"—The Desire of Ages, p. 471.

## ለ. የሱስ ከዚያ ብዙም ሳይቆይ ምን አደረገ? ዓይነ ስውሩ ከእሱ ጋር የተባበረው እንዴት ነው? ዮሐንስ 9፡6፣ 7

"ይህን ብሎ የሱስ የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ወደ ሰሊሆም መጠመቂያ ሔዶ እንዲታጠብ ላከው፣ ሰውየውም ለማየት ቻለ። አብዛኛውን ጊዜ ለማወቅ ከመጓጓት የሚጠየቀውን ጥያቄ እንደሚመልሰው ሁሉ የሱስ በዚህ አኳኋን የደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ በተግባር መለሰላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ የሚጠበቀው የሰውየውን ሕመም በተመለከተ ማን ኃጢአት እንደሠራ ወይም እንዳልሠራ በተነሳው ጥያቄ ላይ እንዲከራከሩ ሳይሆን ዓይነስውሩን ሰው እንዲያይ ያደረገውን የእግዚአብሔርን ኃይልና መሐሪነት እንዲያስተውሉ ነው። የማዳኑ ኃይል የክርስቶስ እንጂ የጭቃው ወይም ሰውየው የታጠበበት መጥመቂያ አለመሆኑ ግልጽ ነው።"—Ibid.

## ሐ. የዓይኑ ብርሃን የተመለሰለት ሰው ጎረቤቶች ምን ዓይነት ምላሽ እንደሰጡ ግለጽ፤ እንዲሁም በእሱና በጎረቤቶቹ መካከል የተደረገውን ውይይት አብራራ። ዮሐንስ 9፡8-12

"የዚያ ወጣት ጐረቤቶችና ዓይነስውር በነበረ ጊዜ ያውቁት የነበሩ ሁሉ «ይህ ሰው ያ ተቀምጦ ይለምን የነበረው አይደለምን?» አሉ። ዓይኖቹ ስለተከፈቱና ፊቱ ብሩህ ሆኖ በመለወጡ ሌላ ሰው ስለመሰለ በጥርጣሬ ተመለከቱት። ጥያቄው ከአንዱ ወደ ሌላው ተላለፈ። «አንዳንዶቹ አዎ እርሱ ነው! አሉ። ሌሎች ደግሞ እርሱን ይመስላል እንጂ እርሱ አይደለም አሉ።» ነገር ግን ትልቅ በረከት ያገኘው ሰው «እኔው ነኝ» በማለት ክርክሩን አቀመው።"—Ibid., pp. 471, 472.

## ሀ. የአይሁድ መሪዎች ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ወደማን ወሰዱት? ለምንስ? በምን ቀን ነበረው ሰውየው የተፈወሰው? ዮሐንስ 9:13፣ 14

## ለ. የፈሪሳውያንን ምላሽ ግለጽ። ዮሐንስ 9:15፣ 16

*“ፈሪሳውያን የሱስን ኃጢአተኛ በማድረግ መሲሕ አይደለም ለማለት ተመኙ። እነዚህ ፈሪሳው ያን ዓይነስውሩን ሰው የፈወሰው ጌታ ሰንበትን እንዳቋቋመና የሰንበትንም አከባበር እንደሚያውቅ አልተገነዘቡም። ስለ ሰንበት አከባበር የሚያስደንቅ ቀናኢነት ያላቸው ይመስሉ ነበር፣ ይሁን እንጂ በዚያው ሰንበት ቀን ነፍስ ለማጥፋት ያቅዱ ነበር።”*—The Desire of Ages, p. 472.

## ሐ. ፈሪሳውያን ስለ ተፈወሰው ሰው እንዲመስከሩ የጠሩት ማንን ነው? ዮሐንስ 9:18፣ 19

*“[ፈሪሳውያን]የሰውየውን ወላጆች ጠሩና «ዕውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን?» ብለው ጠየቁዋቸው።*

*“ሰውየው ራሱ ዓይነስውር እንደ ነበረና በኋላም ለማየት እንደቻለ ቢነግራቸውም ፈሪሳውያኑ ግን ስሕተታቸውን ከማመን ይልቅ የሚያዩትን መረጃ ለመካድ መረጡ።”*—Ibid

## መ. ቀስሞ በውስጣችን የሰረጸ አመለካከት ካለን ሊያመጣብን ከምችለው ክፋ እንድንጠበቅ ማስጠንቀቂያ የተሠጠን እንዴት ነው? ምሳሌ 18፡13

*“በሰሙት ነገር ላይ ተሞርኩዘው ሐሳቡን ተናጋሪው ለመግለጽ ከሞከረው ፈጽሞ በተለየ መልኩ በመቀበል በራሳቸው ውሳኔ ላይ የሚደርሱ ብዙዎች ናቸው። አንዳንዶች የራሳቸውን ጭፍን ጥላቻ ወይም አስቀድሞ የያዙትን አስተሳሰብ በመጠቀም ጉዳዩን ለዓላማቸው በተሻለ ሁኔታ እንዲስማማ አድርገው እንደፈለጉ ይገነዘባሉ።”*—Testimonies for the Church, vol. 5, p. 695.

## ሀ. ፈሪሳውያን ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ወላጆች ለማስፈራራት የሞከሩት እንዴት ነው? እነሱስ ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 9:20፣ 21 ገለልተኛ መልስ የሰጡት ለምንድን ነው? ዮሐንስ 9:22፣ 23

*"ፈሪሳውያን አንድ ምርጫ ነበር የቀራቸው፣ ያውም የሰውየውን ወላጆች ማስፈራራት ነበር። እውነተኛ በመምሰል «አሁንስ እንዴት ማየት ቻለ?» ብለው ጠየቁዋቸው። የክርስቶስን መሲሕነት የተቀበለ ሰው ለሰላሳ ቀናት ከምኩራብ ይገለላል የሚል ትእዛዝ ወጥቶ ስለነበር የሰውየው ወላጆች ለመከራከር ፈሩ። በነዚህ ሰላሳ ቀናት ውስጥ ሕጻናት አይገረዙም፣ በጥፋ ተኛው ሰው ቤትም ለቅሶ አይለቀስም። ይህ ቅጣት እንደትልቅ መቅሰፍት ይቆጠር ስለነበር ቅጣቱ የተበየነበት ሰው ንስሐ ካልገባ ከዚያ የበለጠ ቅጣት ይደርስበታል። ለልጃቸው የተደረገው ትልቅ ድርጊት የሰውየውን ወላጆች በየሱስ እንዲያምኑ አድርጓቸው ነበር፣ ይሁን እንጂ «ይህ ሰው ልጃችን መሆኑንና ዕውር ሆኖ መወለዱን እናውቃለን። ነገር ግን አሁን እንዴት እንደሚያይና ዓይኖቹንም ማን እንዳዳነለት አናውቅም። እርሱን ጠይቁት። እርሱ በዕድሜው ሙሉ ሰው ስለሆነ ስለ ራሱ መናገር ይችላል» ሲሉ መልስ ሰጡ። ስለ ክርስቶስ መመስከር ስለፈሩ ኃላፊነታቸውን ከራሳቸው ወደ ልጃቸው አሳለፉ።"*—The Desire of Ages, pp. 472, 473.

## ለ. ማስፈራሪያ ሲደርስብን ምን ማስታወስ አለብን? መዝሙር 118:6

*"ጽንታችሁ ቁሙ፣ ፈሪ ተብላችሁ ከመጠራት ብላችሁ የተሳሳተ እርምጃ አትውሰዱ። በተለይ ሕሊናህን እንድትሸጥ የሚያነሳሳህ ሰላቅ፣ ዛቻና ወሬ እንድኖር በፍጹም አትፍቀድ።"*—Fundamentals of Christian Education, p. 93.

*"እውነተኛ ክርስቲያናዊ ባሕርይ በዓላማ ጽናት፣ በማይበገር ቆራጥነት፣ በምድርም ሆነ በገሃነም ሊቀየር ወይም ሊጠፋ የማይችል መሆን አለበት። ለዓለማዊ ክብር ስህበት የታወረ የማይሆን፣ ለዛቻ ደንታ የሌለው እና በተንኮል የማይነቃነቅ ያልሆነ ሁሉ ሳይታሰብ በሰይጣን ዘዴዎች ይወድቃል።"*—Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 543, 544.

*የእግዚአብሔርን ህግ ከሚቃወሙት አድቬንቲስቶች በጣም ከባድ ተቃውሞ ይደርስብናል። ነገር ግን የኢየሩሳሌምን ግንብ እንደገነቡት ሰዎች በዘገባዎች፣ ውይይትን ወይም ክርክንር በሚፈልጉ መልእክተኞች፣ በማስፈራራት፣ በውሸት ሕትመቶች ወይም ሰይጣን ሊጠቀምባቸው በሚችልባቸው ማናቸውም ዘዴዎች ከሥራችን መዘናጋትና መደናቀፍ የለብንም።"*—Ibid., vol. 3, p. 574.

## ሀ. የአምላክን ትእዛዝ የሚጠብቁ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ትዕይንቶችና ለትዕዛዙ ምን ምላሽ መስጠት እንዳለብን ግለጽ። ራእይ 12:17፤ የሐዋርያት ሥራ 4፡18-20

"ተቃርኖው (ተጋድሎው) ወደ አዳዲስ ስፍራዎች ሲገባና የሰዎችም አዕምሮ ወደ ተረገጠው ህገ-እግዚአብሔር እንዲያተኩር ሲጠራ፣ ሰይጣን በመታወክ የራወጣል። መልእክቱን የሚያጅበው ኃይል የሚያደርገው ነገር ቢኖር የሚቃወሙትን የበለጠ ማበሳጨት ይሆናል። በመንጎቻቸው ላይ እንዳያንፀባርቅ ብርኃኑን ለመጋረድ የቤተ ክርስቲያን ባለስልጣናት (ካህናት) ከሰው አቅም በላይ ሊባል የሚችል ጥረት ያደርጋሉ። ማድረግ በሚችሏቸው መንገዶች ሁሉ የእነዚህን አስፈላጊ ጥያቄ ውይይቶች ለመጨቆን ይማስናሉ። ቤተ ክርስቲያን የመንግሥታዊ ኃይልን ጽኑ ክንድ [እርዳታ] ትጠይቃለች፤ በዚህም ተግባር ላይ ጳጳሳዊያኑና ፕሮቴስታንቶች ያብራሉ። እሁድን አስገዳጅ የሚያደርገው ንቅናቄ እየተባና የበለጠ ቀራጥ እየሆነ ሲመጣ [የእግዚአብሔርን] ትዕዛዛት በሚጠብቁ ላይ ሕጉ እንዲሰለጥን ይደረጋል። በቅጣትና በእስር ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል። አንዳንዶቹም እምነታቸውን እንዲክዱ ማባበያ ይሆን ዘንድ ተጽዕኖ ፈጣሪ እርከኖች፣ ሽልማቶችና ጥቅማ ጥቅሞች ይበረከቱላቸዋል። ነገር ግን የማያወላውለው መልሳቸው፣ ልክ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሳለ፣ ሉተር ያቀረበው ጥያቄ (አቤቱታ) ይሆናል፦ "ስህተታችንን ከእግዚአብሔር ቃል ዘንድ አሳዩን።" በፍርድ ሸንጎዎች እንዲቀርቡ የሚደረጉ እነርሱ እውነትን ነፃ የሚያወጣ ጠንካራ መከራከሪያ ያደርጋሉ። ከሚሰሟቸው መካከል አንዳንዶቹም ሁሉንም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ጠብቀው እንደ እነርሱ ለመቆም ይመራሉ። በዚህ ሁኔታ እነዚህ እውነቶች በሌላ በምንም አይነት መንገድ ሊደርሳቸው የማይችሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ብርሐን ይደርሳቸዋል።"—The Great Controversy, p. 607.

## ለ. ተቃውሞ ሲያጋጥመን ምንጊዜም ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለብን ምንድነው? ዮሐንስ 9:39፤ የሐዋ. 4:33፤ ማቴዎስ 10፡28

(ደቀ መዛሙርት) በዛቻ ሊገቱ ወይም ሊፈሩ አይችሉም።"—The Acts of the Apostles, p. 48.



1. የአይሁድ መሪዎች በበሽተኞችና በሚሰቃዩት ላይ የሚፈርዱት እንዴት ነው?
2. ዓይነ ስውሩን ማንና ምን ፈወሰው?
3. የዓይነ ስውሩ ጎረቤቶች ለምን ግራ ገባቸው?
4. ወጣቱ ከተፈወሰ በኋላ ምን ሁኔታ አጋጥሞታል?
5. በወላጆቹ ላይ በደረሰው ዓይነት ወጥመድ እንዳልወድቅ ማስወገድ የምችለው እንዴት ነው?

ሰንበት፣ ግንቦት 30፣ 2017

**10ኛ ትምህርት**

# *መንፈሳዊ እውርነትን መጋፈጥ*

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም። በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።” (ማቴ 12፡31፣ 32)**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Testimonies for the Church**, vol. 2, pp. 489–497.**

*“የሰዎችን ዓይን የሚያሳውር ወይም ልባቸውን የሚያደነድን እግዚአብሔር አይደለም። ስሕተታቸውን ያስተካክል ዘንድ በጸጥታም መንገድ ይመራቸው ዘንድ ብርሃንን ይልካል። ዓይኖቹ የሚታወሩትና ልብም የሚደነድነው ይህን ብርሃን ባለመቀበላቸውና ችላ በማለታቸው ነው።”*—The Desire of Ages, p. 322.

## 1. ዳግም የምርመራ ጥያቄ

**እሁድ፣ ግንቦት 24**

**ሀ. የሱስ አይኑን ያበራለትን ወጣት ለሁለተኛ ጊዜ አስጠርተው ፈሪሳውያን ምን እንዲያደርግ ሊያስገድዱት ሞከሩ? ዮሐንስ 9፡24**

*“ፈሪሳውያን የሱስ የፈጸመውን ድርጊት በሕዝቡ ዘንድ ታዋቂነት እንዲያገኝ ማድረጋቸውን ተገነዘቡ። ተአምሩን መካድ አልቻሉም። ዓይነስውር የነበረው ሰው በደስታና በአመስጋኝነት መንፈስ ተሞላ፣ አስደ ናቂውን ሥነ ፍጥረት ተመለከተ፣ በሰማይና በምድር ውበትም ተደሰተ። ስለተደረገለት ነገር ያለ ስጋት ተናገረ፣ ፈሪሳውያኑ ግን «አንተ እውነቱን በመናገር እግዚአብሔርን አክብር፣ ይህ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን» በማለት ዝም ሊያሰኙት ሞከሩ። ይህን ማለታቸው እግዚአብሔር እንጂ ይህ ሰው የዓይኔን ብርሃን ሰጠኝ አትበል ለማለት ነው።”*—The Desire of Ages, p. 473.

**ለ. ወጣቱ ምን የማያዳግም መከራከሪያ አቀረበ? ዮሐንስ 9፡25**

## ሀ. ፈሪሳውያን ዓይኑ የበራለትን ወጣት እንደገና ምን ብለው ጠየቁት? ዓላማቸውስ ምን ነበር? ዮሐንስ 9፡26

*"[ፈሪሳውያን]ያን ጊዜ እነርሱ «ምን አደረገልህ? ዓይኖችህንስ ያዳነው እንዴት ነው?» አሉና ጠየቁት። ተሞኝቻለሁ ብሎ እንዲያምን ለማድረግ በቃላት ጋጋታ ግራ ሊያጋቡት ሞከሩ። ሰይጣንና መላእክቱ በፈሪሳውያኑ ጐን በመሆን የየሱስን ታዋቂነት ለመቃረን ኃይላቸውንና ስውር ደባቸውን ከሰው እስተሳሰብ ጋር አጣምረው ተሰለፉ። በብዙ ሰዎች አእምሮ የነበረውን የእምነት ስሜት አደነዙት።"*—The Desire of Ages, p. 473.

## ለ. ወጣቱ እንዴት መለሰላቸው—እና እሱን ለማበረታታት ከጎኑ ማን ቆመው ነበር? ዮሐንስ 9፡27

*"የዓይኑ ብርሃን የተመለሰለትን ሰው ለማበረታታት የእግዚአብሔር መላእክት ከዚያው ቦታ ነበሩ።*

*"ፈሪሳውያኑ እውር ሆኖ ከተወለደው መሐይም ሰው ሌላ የተጋፈጣቸው ኃይል መኖሩን አልተገነዘቡም፤ ከማን ጋር ክርክር እንደገጠሙም አላወቁም። መለኮታዊ ብርሃን ዓይነስውር ወደ ነበረው ሰው ነፍስ ሰርጾ ገባ። እነዚያ ግብዞች እምነቱን ሊያስጥሉት በሚሞክሩበት ጊዜ ኃይለኛና ቀጥተኛ መልስ በመስጠት በወጥመዳቸው እንደማይያዝላቸው ለማሳየት እንዲችል እግዚአብሔር ረዳው።"*—Ibid., pp. 473, 474.

## ሐ. በዛሬው ጊዜ ተመሳሳይ እርዳታ እንደምናገኝ እንዴት እርግጠኞች እንሆናለን? ሉቃስ 12:11፣ 12

*"አሁን፣ ከመጽሐፍ ቅዱሶቻችሁ ጋር በእግዚአብሔር ፊት ቅረቡ፣ በእግዚአብሔር ፊት ክፈቷቸው፣ እና እግዚአብሔርን ለምኑ። ግንዛቤህ እንዲነቃቃ ፈልግ፤ የእውነትን ትክክለኛ መርሆች እንደምታውቅ ለማወቅ ፈልግ ፣ ከዚያም ከተቃዋሚዎች ጋር ስትገናኝ የሚታገኛቸው በራስህ ጥንካሬ አይሆንም። ለሚጠየቁህ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ለመስጠት የእግዚአብሔር መልአክ ከጎንህ ይቆማል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ሰይጣን ተቃዋሚዎችህ ለአንተ ለመመለስ የሚከብድ ነገርን እንዲናገሩ ያስነሣሣቸው ዘንድ፥ አንተም ደግሞ ያለ ምክር እንድትናገር ለማድረግ ያነሳሳችኋል። ነገር ግን ንግግርህ ሰይጣን ከአንደበትህ በሚወጣው ቃልህ ሊጠቀምበት እንዳይችል የሚያደርግ ይሁን።"*—The Review and Herald, May 3, 1887.

## ሀ. ፈሪሳውያን ዓይኑ የበራለትን ወጣት ማታለል ባለመቻላቸው እሱን እንዴት ናቁት—እንዲህ ያለው ድንቁርና በታሪክ ዘመናት የታየው እንዴት ነው? ዮሐንስ 9:28፣ 29፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 1:18፣ 19፣ 26–28

"እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ በእያንዳንዱ ትውልድ ልዩ እውነትና ልዩ ሥራ አለው። ከዓለማዊ ጥበበኛና አስተዋይ የተሰወረው እውነት እንደሕፃን ለሆኑ ለትሑታን ይገለጣል። የራስን ጥቅም መሥዋዕት ማድረግን ይጠይቃል። ይህንን ለማግኘት መታገል እና ማሸነፍ ያሉብን ድሎች አሉ። ስለእውነት ተሟጋቾች ጥቂት ናቸው። በዓለም ታላላቅ ሰዎች እና ከዓለም ጋር አንድ በሆኑ ቤተ ክርስቲያን ተቃውሞ እና ንቀትም ይገጥማቸዋል። . . .

"በዚህ ትውልድ ውስጥ ያሉ ታላላቅ የሀይማኖት መሪዎች ከዘመናት በፊት የእውነትን ዘር የዘሩትን ሰዎች በማወደስ ሀውልት ገነቡላቸው። ዛሬ ከዛው ዘር የሚወጣውን ችግኝ እድገት ለማቀምና ለመርገጥ ብዙዎች ፊታቸውን አያዞሩምን? እንዲህ የሚለው ያ የቀድሞ ጩኸት እየተደገመ ነው፣ 'እኛ እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እንውቃለን፤ ይህ ሰው [ክርስቶስ] ግን ከወዴት እንደ ሆነ አናውቅም። ዮሐንስ 9፡29 ቀደም ባሉት ዘመናት እንደነበረው ሁሉ በዚህ ጊዜ ያሉት ልዩ እውነቶች የሚገኙት በቤተ ክርስቲያኒቱ ባለ ሥልጣናት ሳይሆን በጣም ያልተማሩ ወይም የአምላክን ቃል ለማመን ጥበበኞች ካልሆኑ ወንዶችና ሴቶች ጋር ነው።"—Christ's Object Lessons, pp. 78, 79

## ለ. ከወጣቱ እውነተኛ ምስክርነት እና ከሌሎች የክርስቶስ ታማኝ አማኞች ምን ምሳሌ እንማራለን? ዮሐንስ 9:30–33፤ የሐዋ. ሥራ 4:19፣ 20

"በጭምትነት ሁሉ፣ በጸጋ መንፈስ እና በእግዚአብሔር ፍቅር ጌታ እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ መሆኑን እና ሰባተኛው ቀን የጌታ ሰንበት መሆኑን ለሰዎች ልንጠቁም (ልንናገር) ይገባናል።

"በጌታ ስም፣ ባንዲራውን እያውለበልብን ቃሉን እየሰበክንወደ ፊት እንሂድ፡ ፡ ባለ ሥልጣናቱ ይህን እንዳናደርግ ሲያዝዙን፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እና የየሱስን ኃይማኖት እንዳንሰብክ ሲከለክሉን፣ ያን ጊዜ እንደ ሐዋርያት "እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም" እንላቸዋለን። የሐዋርያት ሥራ 4:19፣ 20 —Testimonies for the Church, vol. 6, p. 395.

## ሀ. የተበሳጩት ፈሪሳውያን ማስረጃውን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ስለ ፈውሱ የመሰከረውን ወጣት ምን አደረጉ? ዮሐንስ 9፡34

*"ሰውየው መርማሪዎቹን እንዳመጣጣቸው ተጋፈጣቸው። የአስተሳሰብ ስልቱን መቋቋም አልተቻለም። ፈሪሳውያኑ እንደ ጦር በሚወጋውና ቁርጠኛ በሆነው አነጋገሩ ተገርመውና ፈዝዘው ዝም አሉ። በዚህ ጊዜ የተበሳጩት ካህናትና የሕግ ምሑራን ከእርሱ ጋር በመነካካት እንረክሳለን ብለው የፈሩ በመምሰል ቀሚሶቻቸውን ሰብስብ አደረጉና የእግሮቻቸውን አቧራ በማራገፍ "ሁለንተናህ በኃጢአት ተወርሶ የተወለድህ! አንተ እኛን ልታስተምር ነውን?» በማለት አሳጡትና አወገዙት።"*—The Desire of Ages, p. 474.

## ለ. በአንጻሩ የሱስ ወጣቱን የያዘው አያያዝ እንዴት ነበር? ዮሐንስ 9፡35-38

*"ሰውየው በክርስቶስ እግር ሥር ወድቀ ሰገደለት። ሰውየው ያገኘው ፈውስ ለሥጋዊ ዓይኑ ብቻ ሳይሆን የማስተዋል ዓይኑም ተከፍቶለታል። ክርስቶስ ለነፍሱ ስለተገለጠለት ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን አምኖ ተቀበለ።"*—The Desire of Ages, p. 475.

## ሐ. በተቃዋሚ አማፂያን እና እግዚአብሔርን በፍቅር የሚታዘዙትን ነፍሳት ከሚያሳድዱ ክርስቶስን ከሚቃወሙ እልከኞች መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ያብራሩ። 1ኛ ነገሥት 9:6–9፤ ማቴዎስ 12:31፣ 32፤ መዝሙር 11:3

*"[ዋይክሊፍ] የእግዚአብሔርን ኩነኔ በራሱ ላይ ካላመጣ በስተቀር ማንም ሰው ሊወገዝ እንደማይችል አስተማረ።"*—The Great Controversy, p. 84.

*በእነርሱ ዘመን መነገር ያለበትን፣ ለዚያ ጊዜ አስፈላጊ የሆነውን የተለየ መልእክት እንዲናገሩ እግዚአብሔር የሚገለገልባቸው ሁሉ፣ ተቃውሞ ዕጣ ፈንታቸው ይሆናል። ለዚያ ጊዜ የተለየ አስፈላጊነት የነበረው ወቅታዊ እውነት በሉተር ዘመን ነበር፤ ለቤተ ክርስቲያንዋ ዛሬም ወቅታዊ እውነት አለ። ... ለዚህ ዘመን ያለውን ወቅታዊ እውነት የሚያቀርቡ እነርሱ፣ ያለፉት የተሐድሶ አራማጆች ከነበራቸው ተቀባይነት የተሻለ ተቀባይነት እናገኛለን ብለው መጠበቅ የለባቸውም። በእውነትና በሐሰት፣ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል ያለው ታላቁ ተቃርኖ(ተጋድሎ) የዚህ ዓለም ታሪክ ሊዘጋ በተቃረበ ቁጥር እየጨመረ የሚሄድ ነው።"*—Ibid., pp. 143, 144.

## ሀ. የሱስ ስለ ሥራው ውጤት ምን አለ? ዮሐንስ 9፡39

*"ጥቂት ፈሪሳውያን በአቅራቢያው ስለነበሩ እነርሱን ባየ ጊዜ የሱስ በቃሉና በሥራው ምክንያት የሚከሰተው ልዩነት ትውስ ስላለው «የማያዩ እንዲያዩ፣ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጥቼአለሁ» ሲል ተናገረ። ክርስቶስ የመጣው የታወሩ ዓይኖችን ለመክፈትና በጨለማ የሚኖሩ ብርሃን እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። የሱስ የዓለም ብርሃን መሆኑን ተናግሯል፣ አሁን የሠራው ተአምር ስለ ተልዕኮው ይመሰክራል። ክርስቶስ መጀመሪያ በመጣ ጊዜ ያዩት ሰዎች ከዚያ በፊት ለዓለም ተገልጾ በማይታ ወቅ አኳኋን መለኮት የበለጠ ተሟልቶ ተገልጾላቸዋል። ስለ እግዚአብሔር የበለጠ ለማወቅ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላቸው። እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ ከተሰጣቸው እድል ጋር ፍርድ ተላለፈባቸው። ባሕርያቸው ተፈተነ፣ የመጨረሻ መዳረሻቸውም ተወሰነ።"*—The Desire of Ages, p. 475.

## ለ. ፈሪሳውያን ለክርስቶስ ቃላት ምን ምላሽ ሰጡ? ዮሐንስ 9፡40 የሱስ ሲነግራቸው፣ ዓይነ ስውርነታቸው የዳረጋቸውን ጥፋታቸውን እንዴት ገለጠላቸው? ዮሐንስ 9፡41

*"ዓይነስውር የነበረው ሰው ሥጋዊና መንፈሳዊ ብርሃን እንዲያገኝ ያደረገው መለኮታዊ ኃይል ፈሪሳውያኑን ወደባሰ ጥቅጥቅ ጨለማ እንዲገቡ አደረጋቸው። ከአዳማጮቹ ጥቂቶቹ የሱስ የተናገረው እነርሱን የሚመለከታቸው ስለመሰላቸው «ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን ነውን?» ብለው ሲጠይቁት የሱስ «ዕውሮች ብትሆኑማ ኖሮ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር» ሲል መለሰላቸው። እግዚአብሔር እውነትን ለማየት እንዳትችሉ አድርጓችሁ ቢሆን ኖሮ አለማወቃችሁ ኃጢአት አይሆንባችሁም ነበር። «አሁን ግን እናያለን» ትላላችሁ። ማየት እንችላለን ብላችሁ ስለምታምኑ ብርሃን ለማግኘት የምትችሉበትን ብቸኛ መንገድ ችላ ትላላችሁ። ፍላጐታቸውን ለሚያውቁ ሁሉ ክርስቶስ ወሰን የሌለው እርዳታ ይዞላቸው መጥቷል። ፈሪሳውያን ፍላጐት አለን ብለው ስላልተናዘዙና ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ስላልፈለጉ እውር ሆነው ቀሩ፣ ለዚህም እውርነታቸው ኃላፊነቱ የራሳቸው ነው። ስለዚህ የሱስ «ኃጢአተኞች ሆናችሁ ትቀራላችሁ» አላቸው።*—Ibid.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

**አርብ፣ ግንቦት 29**

1. *ፈሪሳውያን ዓይነ ስውር የነበረውን ሰው ለማሳመን የሞከሩት ነገር ምንድን ነው?*
2. *የማያምኑትን ፈሪሳውያን የሚጠቀምባቸው ማን ነበር?*
3. *ወጣቱ ግልጽና አሳማኝ መልስ እንዲሰጥ የረዳው ማን ነው?*
4. *እሱ በድፍረት ክርስቶስን ሲመሰክር ምን ሆነ?*
5. *ከሁሉ የከፋው የዓይነ ስውርነት ዓይነት ምን እንደሆነና ለምን እንደሆነ ግለጽ።*

ሰንበት፣ ሰኔ 07፣ 2017

**11ኛ ትምህርት**

## የሱስ፣ መልካም እረኛ

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።” (ዮሐ. 10፡11)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** The Desire of Ages, **pp. 476–484.**

“*ደጁም እረኛውም ክርስቶስ ነው። እሱ ብቻውን ይገባል። በጎቹንም የሚጠብቀው በራሱ መስዋዕትነት ነው።*”—The Desire of Ages, p. 477.

## 1. ሌባ እና እረኛው

**እሁድ፣ ሰኔ 01**

### ሀ. የሱስ በሌባውና በእረኛው መካከል ያለውን ልዩነት የገለጸው እንዴት ነው? በዚህስ ምን መንፈሳዊ ትምህርት እየሰጠ ነው? ዮሐንስ 10:1፣ 2

“*ክርስቶስ እነዚህ ትንቢቶች [በኢሳይያስ 40:9–11፤ መዝሙር 23:1፣ እና ሕዝቅኤል 34:23፣ 16፣ 25፣ 28] ስለ እርሱ የተነገሩ መሆኑን በመግለጽ በእርሱ ባሕርይና በእሥራኤል መሪዎች ባሕርይ መካከል ያለውን ልዩነት አሳየ። ከጥቂት ጊዜ በፊት ፈሪሳውያን አንድ አባል ስለ ክርስቶስ ኃይል ለመመስከር ስለ ደፈረ ከመንጋው ለይተው አባርረውታል። እውነተኛው እረኛ ወደ እርሱ እየሳበው የነበረውን ነፍስ ከመንጋው ለይተውታል። ይህን በማድረጋቸው የተሰጣቸውን ሥራ እንዳላወቁና የመንጋው እረኛ ለመሆንም ብቃት እንደሌላቸው አሳዩ! ስለዚህ የሱስ በእነርሱና በመልካሙ እረኛ መካከል ያለውን ልዩነት በማሳየት እርሱ የእግዚአብሔር መንጋ እውነተኛ ጠባቂ መሆኑን ገለጸ።*”—The Desire of Ages, p. 477.

“*ረዳት አልባና በእርሱ ጥገኛ ስለሆንን ክርስቶስ ይወደናል።*”—Sermons and Talks, vol. 1, p. 248..

### ለ. በበጎቹና በእረኛቸው መካከል ምን ዝምድና አለ? ዮሐንስ 10:3፣ 4 በጎቹ በእንግዳ ፊት ምን ያደርጋሉ? ዮሐንስ 10፡5

## ሀ. የሱስ ከፈሪሳውያን ጋር ያለውን ልዩነት የገለጠው እንዴት ነው? ዮሐንስ 10፡7-10

“ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር መንጋ መግቢያ በር ነው። ከጥንት ጀምሮ ልጆቹ የሆኑት ሁሉ የገቡት በዚህ በር ነው እነዚህ ልጆቹ በምሳሌነት በቀረቡት መስዋዕቶች፣ ለነቢያት በተገለጹት ራእዮች፣ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማራቸው ትምህርቶችና ለሰው ልጆች በሠራቸው ተአምራት የሱስ «የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ» መሆኑን ለማየት በቅተዋል፣ በእርሱም ከጸጋው መንጋ ጋር ለመቀላቀል ችለዋል። ብዙዎች ለዓለም ሃይማኖት ሌላ ዓላማ ይዘው ተነስተዋል፣ እንደዚሁም ሰዎች . ከእግዚአብሔር ይቅርታና ሰላም ለማግኘትና ከመንጋው ጋር ለመቀላቀል ይችሉ ዘንድ አገልግሎቶችንና ሥርዓቶችን ቀይሰዋል። ብቸኛው በርክርስቶስ ነው። በክርስቶስ ምትክ ሌላ ነገር የሚያስገቡ ወይም በሌላ መንገድ ወደ መንጋው ለመግባት የሚሞክሩ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው።

“ፈሪሳውያኑ በዚህ በር በኩል አልገቡም። ወደ መንጋው የገቡት በክርስቶስ በኩል ሳይሆን በሌላ በኩል ተንጠላጥለው ስለሆነ የእውነተኛውን እረኛ ተግባር አልፈጸሙም። ካሕናቱ፣ ሹማምንቱ፣ ጸሐፍቱና ፈሪሳውያን የበጎቹን መሰማሪያ ቦታ አጠፉት፣ የሕይወት ውሃ ምንጩንም በከሉት። የመንፈስ ቃል እነዚህን የሐሰት እረኞች «ለደከሙት ክብካቤ አላደረጋ ችሁላቸውም፣ የታመሙትንም አላዳናችሁም፣ የተሰበሩትን አልጠገናች ሁም፣ የባዘኑትን አልመለሳችሁም፣ የጠፉትን አልፈለጋችሁም፣ ይህን በማድረግ ፈንታ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው» በማለት ምንነታቸውን በትክክል ገልጾታል። ሕዝ. 34:4”—The Desire of Ages, pp. 477, 478.

## ለ. እውነተኛው እረኛ ከተቀጣሪ የሚለየው እንዴት ነው? ዮሐንስ 10፡11-13

“በቃል የሚያስተምሩ ብቻ ሳይሆኑ በተግባራቸው እውነትን ለሌሎች የሚገልጡ ሰዎች ያስፈልጋሉ። የክርስቶስ አገልጋይ መሆን የሚያኮራቸውና ተሸከሙ ያላቸውን መስቀል መሸከም የተማሩ ሰዎች በብዛት ይፈለጋሉ።

አንድ ቄስ (ወንጌላዊ) የሚያገለግላቸውን ሰዎች በቅርብ ማወቁ ይጠቅመዋል፡ ፡ በቀላሉ ሊያስተምራቸው እንዲችል አስተሳሰባቸውን ማወቅ አለበት። ያን ጊዜ ተፈጥሮንና ሰዎችን በቅርብ ለሚከታተሉ ሰዎች የሚሰጠው የማስተዋል ጸጋ ይሰጠዋል።”—Gospel Workers, p. 191.

## ሀ. የሱስ የገለጠው ሌላኛው የመልካም እረኛ ባሕርይ ምንድነው? ዮሐንስ 10:14፣ 15

*"ዓለማዊ የበግ እረኛ በጐቹን እንደሚያውቅ ሁሉ እንዲሁም መለኮታዊዩ እረኛ በዓለም ላይ ተበታትነው የሚገኙትን በጐቹን ያውቃቸዋል። «በበጐች የተመሰላችሁትና እኔ የምመግባችሁ መንጋ እናንተ የእሥራኤል ሕዝብ ናችሁ። እኔም አምላካችሁ ነኝ።» የሱስ «አንተ የእኔ ነህ፣ በስምህም ጠርቼሃ ለሁ» ይላል። «ስምሽን በእጄ መዳፍ ላይ ጽፌዋለሁ።» ሕዝ.*34:31፤ *ኢሳይያስ* 43:1፤ 49:16።

*የሱስ እያንዳንዳችንን ያውቀናል፣ በድካማችንም ይራራልናል። ሁላችንንም በስም ያውቀናል። የምንኖርበትን ቤትና በውስጡም የሚኖሩትን ሁሉ ያውቃል። አንዳንድ ጊዜ ከበጐቹ አንዱን ለመገናኘት አገልጋዮቹን ወደ እንደዚህ ያለ ከተማ፣ ወደ እንደዚህ ያለ መንገድና ወደ እንደዚህ ያለ ቤት ሒዱ ብሎ አዞአል።*

*እያንዳንዱ ነፍስ ክርስቶስ ለእርሱ ብቻ የሞተለትን ያህል ይታወቃል። የእያንዳንዱ ሰው ስቃይ የየሱስን ልብ ይነካል። እርዳታ ለማግኘት የሚደረግ ጩኸት ሁሉ ወደ ጆሮው ይደርሳል። እርሱ የመጣው ሰዎችን ሁሉ ወደ እርሱ ለመሳብ ነው። እርሱ «ተከተሉኝ» እያለ ይጠራል፤ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲሳቡ ለማድረግ መንፈሱ ልባቸውን ይቀሰቅሳል። ብዙዎች ለመከተል ፈቃደኛ አይደሉም። የሱስ እነርሱንም ያውቃቸዋል። ጥሪውን በደስታ ተቀብለው ወደ እርሱ ጥበቃ ሥር የሚመጡትንም ያውቃቸዋል። «እኔ በጐቼን አውቃለሁ! በጐቼም እኔን ያውቁኛል» ይላል። በዓለም ላይ ሌላ በግ እንደ ሌለ ያህል እርሱ ለእያንዳንዱ በግ ይጠነቀቃል።"*—The Desire of Ages, pp. 479, 480.

## ለ. የሱስ ያሰበላቸው ለሌሎቹ ለየትኞቹ በጎች ነው? ዮሐንስ 10፡16

*"የሱስ በዓለም ስላሉት በሐሳዊ እረኞች ስለተሳሳቱት ነፍሳት አሰበ። ከበጐቹ ጋር ሊቀላቅላቸው የፈለገው በጐች በተኩላዎች መካከል ተበታት ነው ይገኙ ስለነበር፣ «በዚህ መንጋ ውስጥ ያልሆኑ ሌሎች በጐች አሉኝ፡ እነርሱንም ማምጣት ይገባኛል! እነርሱ ድምጼን ይሰማሉ፣ አንድ መንጋም ይሆናሉ፣ እረኛውም አንድ ይሆናል፣» ሲል ተናገረ። ዮሐ.*10:16።"—Ibid., p. 483.

*"እግዚአብሔር በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ውስጥ ዕንቁዎች አሉት፣ እኛ ሃይማኖተኞች ነን በሚሉት ዓለም ላይ ሰፊ ውግዘት ልንሰጥ አይገባንም፤ ነገር ግን እውነት በትሕትናና በፍቅር በየሱስ እንዳለ ሁሉ እንዲሁ አቅርቡላቸው። ሰዎች በእኛ ውስጥ እግዚአብሔርን መምሰልና መታመንን፣ እንዲሁም ክርስቶስን የሚመስሉ ባሕርያትን ይዩ፣ በዚያን ጊዜ ወደ እውነትም ይሳባሉና።"*—The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 4, p. 1184.

## ሀ. የሱስ ምን ዓይነት መለኮታዊ ኃይል እንዳለው ተናግሯል? ዮሐንስ 10:17፣ 18

“«እንደገና መልሼ የምወስዳትን ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለ ሆንሁ አብ እኔን ይወድደኛል።» ይህም አባቴ እናንተን እጅግ ከመውደዱ የተነሳ እኔ እናንተን ለማዳን ሕይወቴን ስለሰጠሁ የበለጠ ወደደኝ ማለት ነው። ሕይወቴን አሳልፌ በመስጠት፣ የእናንተን እዳና በደል በመረከብ ቤዛችሁና አለ ኝታችሁ በመሆኔ በአባቴ ዘንድ ተወዳጅነትን አተረፍሁ።

«ሕይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም። ሕይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት አለኝ።» የሰብአዊ ቤተሰብ አባል በመሆኑ ሟች ሆነ፣ አምላክ በመሆኑ ደግሞ ለዓለም የሕይወት ምንጭ ሆነ። ላለመሞትና በሞት ሥልጣን ሥርላለመግባት አሻፈረኝ ማለት ይችል ነበር። ነገር ግን ሕይወትንና አለሟች ነትን ለማስገኘት ሲል ሕይ ወቱን በፈቃዱ አሳልፎ ሰጠ። ሰዎች ለዘላለም ሞተው እንዳይቀሩ ሲል የዓለ ምን ኃጢአት ተሸከመ፣ እርግማንዋንም ተጋፈጠ፣ ሕይወቱንም ለመስዋዕትነት አሳልፎ ሰጠ። «እኛ ልንሸከመው የሚገባንን መከራና ሕማም እርሱ ተሸከመ። ይህ በእርሱ ላይ የደረሰበት ግርፋትና መከራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተላከ ቅጣት እንደሆነ አድርገን አሰብን። ይሁን እንጂ እርሱ ተወግቶ የቆሰለው ስለ ኃጢአታችን ሲሆን በመገረፍ የደቀቀውም ስለ ፈጸምነው በደል ነው። እርሱ በተቀበለው ቅጣት እኛ ሰላምን አገኘን። እርሱም በመቁሰሉ እኛ ተፈወስን። እኛ እያንዳንዳችን ከመንገድ ወጥተው በመባዘን እንደ ጠፉ በጐች ሆነን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እኛ ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት ሁሉ በእርሱ ላይ አኖረ።» ኢሳይያስ 53:4-6።”—The Desire of Ages, pp. 483, 484.

## ለ. ሰዎች ክርስቶስን እንዲከተሉ የሚመራቸው ምንድን ነው? ዮሐንስ 10:27፤ 1ኛ ዮሐንስ 4:10፣ 19

“የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ክርስቶስን የሚከተሉት ቅጣት በመፍራት ወይም የዘላለም ዋጋ ለማግኘት በመመኘት አይደለም። እነርሱ ክርስቶስን የሚከተሉበት ምክንያት ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ በእንግድነት ከቤተልሔም በረት እስከ ቀራንዮ መስቀል ድረስ በኖረ ጊዜ የተከሰተውን ወደር የሌለውን ፍቅሩን ስላዩና እርሱን ማየት ደግሞ ነፍስን ስለሚስብ፣ ስለሚያረጋጋና ትሑት እንዲሆን ስለሚያደርግ ነው። ፍቅር የተመልካቹን ልብ ያነቃቃል። ስለዚህ ድምጹን ሰምተው ይከተሉታል።”—Ibid., p. 480.

“በምድር ላይ ያለውን ህይወቱን፣ ለእኛ ሲል የከፈለውን መስዋዕትነት፣ በሰማይ አማላጃችን ሆኖ የሚሰራውን ስራውን እና ለሚወዱት የሚያዘጋጃቸውን መኖሪያ ቤቶች ስናሰላስል፣ የክርስቶስ ፍቅር እንዴት ያለ ታላቅ እና ጥልቅ ነው! በማለት እንደነቃለን።”—The Acts of the Apostles, p. 334.

## 5. የመዳን ዋስትና | ሐሙስ፣ ሰኔ 05

### ሀ. የሱስ ለበጎቹ ምን ማረጋገጫ ሰጣቸው? ዮሐንስ 10:28፣ 29

ምንም እንኳን አሁን የሱስ እግዚአብሔር አብ ወዳለበት ቦታ ያረገና የዩኒቨርስን (የዓለማትን) ዙፋን ቢጋራም ቀሉ ርህሩህ ባሕርዩ አልተለየውም። ዛሬም ያው ደግና አዛኝ ልቡ የሰብአዊ ዘርን ሰቀቃ ለማስወገድ ክፍት ነው። ዛሬም በምስማር የተወጉት እጆቹ በዓለም የሚኖሩትን ሕዝቦቹን በበለጠ ለመባረክ ተዘርግተዋል። «እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፣ ስለዚህ ከቶ አይጠፉም፣ ከእኔ እጅ ማንም ነጥቆ አይወስዳቸውም።»

ራስዋን ለክርስቶስ ያስረከበች ነፍስ በእርሱ ዘንድ ከመላው ዓለም የበለጠ የተከበረች ናት። ያችን አንዲት ነፍስ ለመንግሥቱ ለማዳን ሲል አዳኛችን የቀራንዮን ስቃይ መቀበሉ አይቀርም ነበር። የሞተላትን ነፍስ ፈጽሞ ችላ አይላትም። ተከታዮቹ ከእርሱ ተለይተው ለመሔድ ካልፈለጉ በስተቀር እርሱ አጥብቆ ይይዛቸዋል።"—The Desire of Ages, pp. 480–483.

### ለ. የእኛ መንፈሳዊ ደህንነት እና የመዳን ዋስትና በምን ላይ ያርፋል? ሮሜ 8፡31-39

"በሰማዩ አደባባይ፣ ክርስቶስ ስለ ቤተክርስቲያኑና በደሙ ዋጋ ለከፈለላቸው ይማጸናል። ምዕተ-አመታት፣ ዘመናት፣ የእርሱን የኃጢያት ክፍያ መስዋዕትነት በፍፁም ሊቀንሱት አይችሉም። ሕይወትም ቢሆን ሞትም ከፍታም ቢሆን ዝቅታም በክርስቶስ የሱስ ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም። ይህም የሆነው እርሱን አጥብቀን ስለያዝነው ሳይሆን እርሱ አጥብቆ ስለሚይዘን ነው። መዳናችን በራሳችን ጥረት ላይ የተመሰረተ ከሆነ መዳን አንችልም ነበር፤ ነገር ግን መዳናችን ከተስፋዎቹ ሁሉ ጀርባ ባለው አካል ላይ የተመካ ነው። እርሱን የያዝንበት አያያዛችን ደካማ ሊመስል ይችላል፣ ነገር ግን ፍቅሩ የታላቅ ወንድም ነው። ከእርሱ ጋር ያለንን አንድነት እስካጠናከርን ድረስ ማንም ከእጁ ሊነጥቀን አይችልም።"—The Acts of the Apostles, pp. 552, 553.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሰኔ 06

1. በእረኛና በሌባ መካከል ያለውን የምግባር ልዩነት ግለጽ።
2. የሱስ ራሱን የገለጸው በምን ሌላ ምሳሌ ነው?
3. እውነተኛ እረኞች ከበጎቻቸው ጋር ምን ያደርጋሉ?
4. በጎቹ እረኛውን እንጂ እንግዳ የማይከተሉት ለምንድን ነው?
5. ስለመዳናችን እንዴት እርግጠኞች መሆን እንዳለብን ግለጽ።

ሰንበት፣ ሰኔ 14፣ 2017

## 12ኛ ትምህርት

# የሱስ እና አልዓዛር

**የመታሰቢያ ጥቅስ፦ “የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው።” (መዝ. 116፡15)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** The Ministry of Healing, **pp. 219–224.**

“የክርስቶስ ሕይወትነት፣ ከጥንት ከመሠረቱ ከራሱ የመነጨ እንጂ በብድር በውሰት ከሌላ የተገኘ አይደለም። . . . የክርስቶስ መለኮትነት ለአማኞች የዘላለም ሕይወት ማግኛ ዋስትና ነው።”—The Desire of Ages, p. 530.

## 1. በቢታንያ ያለ ቤተሰብ | እሁድ፣ ሰኔ 08

### ሀ. የሱስ በቢታንያ ምን ዓይነት ደቀ መዛሙርት ነበሩት? ዮሐንስ 11፡5

“[የክርስቶስ] በቢታንያ ከሚገኝ አንድ ቤተሰብ ጋር ልቡ በጠንካራ የፍቅር ሰንሰለት ተያይዞ ስለነበር ከዚያ ቤተሰብ ለአንዱ በጣም አስደናቂ ድርጊት ፈጸመለት።

ብዙውን ጊዜ አዳኞችን በአልዓዛር ቤት እፎይታ ያገኝ ነበር። አዳኛችን የራሱ የሆነ ቤት ስላልነበረው በወዳጆቹና በደቀ መዛሙርቱ እስተናጋጅነት ይገለገል ነበር። ብዙውን ጊዜ ሰውነቱ በዛለና ከሰዎች ጋር ሆኖ መዝናናት ባስፈለገው ጊዜ ከእልኸኞቹ ፈሪሳውያን ቅናትና ጥርጣሬ ርቀ ሰላም ወደ ሰፈነበት ወደነአልዓዛር ቤት ጐራ ማለት ያስደስተው ነበር። በዚያ ቤት ውስጥ ልባዊ አቀባበል፣ ንጹህና የተቀደሰ ወዳጅነት ያገኝ ነበር። ንግግሩን እንደሚያስተውሉና በልባቸውም እንደሚቀበሉት በማወቅ በቀላል አነጋገርና ፍጹም በሆነ ነጻነት ይጫወታል።”—The Desire of Ages, p. 524.

### ለ. እግዚአብሔር በምን ዓይነት ቤት ውስጥ ነው ከምርጥ በረከቶች የሚገኘው? ምሳሌ 3፡33 (የመጨረሻው ክፍል)።

“አዳኛችን አደብ የገዛ ቤተሰብንና መስማት የሚፈልጉ አዳማጮችን ይወድዳል። ሁል ጊዜ ሰብአዊ ርህራሄን፣ አክብሮትንና ፍቅርን ለማግኘት ናፍቆት ነበረው። እርሱ ለማካፈል ሁል ጊዜ ዝግጁ የሆነበትን ሰማያዊ ትምህ ርት የተቀበሉ ሁሉ ከፍተኛ በረከት አግኝተዋል።”—Ibid.

## ሀ. የአልዓዛር እህቶች ወንድማቸው በጠና ሲታመም ምን እርምጃ ወሰዱ? ምን ምላሽስ አገኙ? ዮሐንስ 11፡1-4

"የሱስ በሚያርፍበት ሰላማዊ ቤት ውስጥ ሐዘን ገባ። አልዓዛር በድንገት ስለታመመ እህቶቹ «ጌታ ሆይ! ወዳጅህ ታሞአል» የሚል መልእክት ወደ የሱስ ላኩ። እህቶቹ ወንድማቸውን የያዘው ሕመም ኃይለኛ መሆኑን ቢያዩም ክርስቶስ ማንኛውንም የደዌ ዓይነት ለመፈወስ የሚችል መሆኑን እንዳሳየ ያውቁ ነበር። የሐዘናቸው ተካፋይ እንደሚሆን ስላመኑ ፈጥኖ እንዲደርስ አስቸኳይ ጥያቄ ሳያቀርቡ «ወዳጅህ ታሞአል» የሚል በእርሱ መተማመናቸውን የሚገልጽ መልእክት ብቻ ላኩ። የሱስ መልእክታቸው እንደደረሰው አፋጣኝ መልስ እንደሚሰጥና በተቻለው ፍጥነት ወደ ቢታንያ እንደሚመጣ አመኑ።

"ከየሱስ መልእክት ለማግኘት በጉጉት ተጠባበቁ። የወንድማቸው እስትንፋስ እስካልተቋረጠች ድረስ የሱስ እንዲመጣላቸው እየጸለዩ ተጠባበቁ። ነገር ግን መልእክተኛው የሱስን ሳይዝ ብቻውን ተመልሶ መጣ። ሆኖም መልእክተኛው «ይህ ሕመም ለሞት የሚያደርስ አይደለም» የሚል መልእክት ስላመጣ እትማማቾቹ አልዓዛር ከሞት ይተርፋል የሚል ተስፋ አደረባቸው። ስለሆነም ሕሊናውን በመሳት ላይ ለነበረው ሕመምተኛ በለሰለሰ አንደበት የተስፋ ቃል ለመናገር ሞከሩ።"—The Desire of Ages, pp. 525, 526.

## ለ. በቀጣዮቹ ጥቂት ቀናት የነበሩትን የክርስቶስን ቃላት እና ድርጊቶች ግለጽ። ዮሐንስ 11፡5-8

"የሱስ በሁለቱ ቀናት ውስጥ ስለ አልዓዛር ምንም ነገር ባለመናገሩ የመጣለትን መልእክት ፈጽሞ የዘነጋው ይመስል ነበር። በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የየሱስ መንገድ ጠራጊ የነበረው የዮሐንስ መጥምቁ ነገር ትዝ አላቸው። ታላላቅ ተአምራት የመሥራት ኃይል እያለው የሱስ ለምን ዮሐንስ በእስር ቤት እንዲማቅቅና በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲሞት እንደፈቀደ ገረማቸው። ይህ ዓይነት ኃይል እያለው የሱስ ለምን የዮሐንስን ሕይወት አላዳነም? ፈሪሳውያን ይህን ጥያቄ የሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ላለመሆኑ መልስ የማይገኝለት የመከራከሪያ ነጥብ አድርገው ያቀርቡ ነበር። አዳኛችን ደቀ መዛሙርቱን ስለፈተና፣ ጉዳትና ስደት አስጠንቅቋቸዋል። ፈተና ሲደርስባቸው ችላ ይላቸው ይሆን? አንዳንዶቹ ተልዕኮው አልገባን ይሆን ብለው ተጠራጠሩ። ሁሉንም ጭንቀት ያዛቸው። ...

"ደቀ መዛሙርቱ የሱስ ወደ ይሁዳ መሔዱ የማይቀር ከሆነ ለምን ሁለት ቀን ቀየ የሚል ጥያቄ አነሱ። በዚያ ወቅት ከፍተኛ ጭንቀት የፈጠረባቸው የክርስቶስና የራሳቸው ደህንነት ጉዳይነበር። የሱስ ያሰበው ጉዞ አደጋ ከማስከተል በቀር ሌላ ጥቅም እንደማያመጣ ስለተሰማቸው።"—Ibid., pp. 526, 527.

## ሀ. ክርስቶስ በአልዓዛር ሕመም ዙሪያ የተፈጸሙትን ውስብስብ ክስተቶች እንዴት እንደያዘ በሚያሳየው ጊዜ ከማይሸረው መልእክት ምን እናገኛለን? ዮሐንስ 11:9፣ 10

“ከክርስቶስ ጋር ተባባሪዎች ሊሆኑ የሚችሉ፣ ነገር ግን መልእክተኞቹን እና መልእክታቸውን የናቁ ሁሉ፣ ያላቸውንም ያጣሉ። የሚሰናከሉበትን ሳያውቁ በጨለማ ይጓዛሉ። እነዚህ ሰዎች በመጨረሻዎቹ ቀናት ሸንገላ ለመታለል ዝግጁ ናቸው። አእምሯቸው በጥቃቅን ጉዳዮች የተጠመደ ሲሆን ከክርስቶስ ጋር የመተሳሰርና ከአምላክ ጋር አብረው የሚሠሩ ሠራተኞች የመሆንን የተባረከ አጋጣሚ ያጣሉ።”— Fundamentals of Christian Education, p. 471.

## ለ. የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን አስደናቂ መገለጥ እየሰጣቸው ነበር—ነገር ግን እነሱ ቃሉን እንዴት ተረዱ? ዮሐንስ 11:11፣ 12

“«የሱስ ይህን ካላቸው በኋላ ወዳጃችን አልዓዛር አንቀላፍቶአል፣ እኔ ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ» አለ። «ወዳጃችን አልዓዛርአንቀላፍቶአል» የሚለው አነጋገር ልብን የሚነካና ርህራሄ የተሞላበት ነው። ደቀ መዛሙርቱ ጌታቸው ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ ስለሚደርስበት አደጋ እየተጨነቁ ስለነ በር በቢታንያ በሐዘን ላይ የነበሩትን ቤተሰብ ረሱዋቸው። ክርስቶስ ግን አል ረሳቸውም። ይህ ለደቀ መዛሙርቱ ግሳጼ ነበር። አልዓዛርስለመታመሙ መል እክት እንደደረሰው የሱስ ወዲያውኑ አንድ ነገርአለማድረጉ ደቀ መዛሙር ቱን ቅር አሰኝቷቸው ነበር። እነርሱ የገመቱትን ያህል የሱስ አልዓዛርንና እህ ቶቹን ቢወዳቸው ኖሮ ወዲያውኑ ከመልእክተኛው ጋር ይሔድ አልነበረምን የሚል ጥርጣሬ አድሮባቸው ነበር። ነገር ግን «ወዳጃችን አልዓዛር አንቀላፍቶ አል» የሚለው አነጋገርአስተሳሰባቸውን እንዲያስተካክሉ አደረጋቸው። ክርስ ቶስ በስቃይ ላይየነበሩትን ወዳጆቹን እንዳልረሳቸው አመኑ።”—The Desire of Ages, p. 527.

## ሐ. በትክክል የክርስቶስ ቃላት ምን ለማለት እንደነበረ ግለጽ። ዮሐንስ 11:13፣ 14

“የሱስ ለአማኝ ልጆቹ ሞትን በእንቅልፍ ይመስልላቸዋል። የሞቱት አማኝ ልጆቹ በእግዚአብሔር ዘንድ ሕይወታቸው በክርስቶስ ተከልሎ የመጨረሻው መለከት እስኪነፋ ድረስ በእርሱ እንዳንቀላፉ ይቆያሉ።”—Ibid.

## ሀ. የሱስ አልዓዛር መሞቱን ካወቀ በኋላም ወደ ቢታንያ ሳይመጣ የቆየው ለምንድን ነው? ዮሐንስ 11፡15

"*ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶስ «አልዓዛር ሞቶአል… እዚያ ባለመኖሬ…ደስ ብሎኛል» በማለቱ ተገረሙ። አዳኛችን እያወቀ ጉዳት ወደ ደረሰባቸው ወዳጆቹ ቤት ላለመሔድ ወሰነ? ማርታ፣ ማርያምና ሟቹ አልዓዛር ብቻቸውን የተተው ይመስል ነበር። ነገር ግን ጠቅላላ ሁኔታው በክርስቶስ ቁጥጥር ሥር ስለነበረና አልዓዛር ከሞተ በኋላም ወንድማቸው የሞተባቸው እህትማማቾች በክርስቶስ ጸጋ ስለተጽናኑ ብቻቸውን አልነበሩም። ወንድማቸው ኃይለኛ ጠላቱ ከሆነው ከሞት ጋር በሚታገልበት ጊዜ የሱስ የእህትማማቾቹን በሐዘን የተጐዳ ልብ ተመልክቷል። ጌታ የሱስ ለደቀ መዛሙርቱ «አልዓዛር ሞቶአል» ባላቸው ጊዜ ሐዘንና ጭንቀት ተሰማው። ክርስቶስ በቢታንያ ስለነበሩት ወዳጆቹ ብቻ ሳይሆን ስለ ደቀ መዛሙርቱም ስልጠና ጭምር ያስብ ነበር። የአብን በረከት ለሁሉ ለማዳረስ እነዚህ ደቀ መዛሙርት በዚች ምድር ላይ የእርሱ ተወካዮች መሆን ነበረባቸው። ለእነርሱ ሲል አልዓዛር እንዲሞት ፈቀደ። ገና ሳይሞት ከሕመሙ ፈውሶት ቢሆን ኖሮ የመለኮታዊ ባሕርዩ ዋና መስረጃ የሆነው ተአምር አይታይም ነበር።*"—The Desire of Ages, p. 528.

## ለ. ታላቁ ፈዋሽ ወዳጁ አልዓዛርን በጠና ታሞ እንዲሞት ከፈቀደበት ሁኔታ ማስተዋል ያለብን ምንድነው? 1ኛ ቆሮንቶስ 15:17–19፤ መዝሙር 18:28

"[የክርስቶስ] *ሥራ በበሽታ ላይ ኃይሉን በማሳየት አልቀመም። እያንዳንዱን የፈውስ ሥራ የፍቅሩንና የቸርነቱን መለኮታዊ መመሪያዎች በልብ ውስጥ የመትከል አጋጣሚ አድርጎታል።*"—Counsels on Health, p. 249.

"*ክርስቶስ አልዓዛር ታሞ በተኛበት ክፍል ውስጥ ቢኖር ኖሮ ሰይጣን ኃይል ስለማይኖረው አልዓዛር አይሞትም ነበር። ሕይወት ሰጭ የሆነው ጌታ በሚገኝበት ቦታ ሞት ቀስቱን በአልዓዛር ላይ ማነጣጠር አይችልም። ስለዚህ ክርስቶስ ከቦታው ርቆ ቆየ። ሰይጣንን የተሸነፈ ጠላት ኣድርጐ ለማባረርበማሰብ ኃይሉን እንዲያሳይ ፈቀደለት። ስለዚህ አልዓዛር በሞት ግዛት ሥርእንዲወድቅ ፈቀደ፣ ያዘኑት እህቶቹም ወንድማቸው በመቃብር ውስጥ ሲጋደም ተመለከቱ። ሁለቱ ሴቶች የሞተውን ወንድማቸውን ፊት ሲመለከቱ በአዳኛቸው ላይ የነበራቸው እምነት በከባድ ፈተና ላይ እንደሚወድቅ የሱስ ያውቅ ነበር። ነገር ግን አሁን በሚያደርጉት ትግል ምክንያት ሃይማኖታቸው የበለጠ ኃይል እንደሚያገኝ ያውቅ ነበር። እርሱም የሐዘናቸው ተካፋይ ነበር። በመዘግየቱ ለእነርሱ የነበረው ፍቅርአልተቀነሰም። ለእነርሱ፣ ለአልዓዛር፣ ለራሱና ለደቀ መዛሙርቱ አንድ ድል እንደተዘጋጀላቸው ያውቅ ነበር።*"—The Desire of Ages, p. 528.

## 5. ሁልጊዜ እንደጠበቅነው አይሆንም . . . ሐሙስ፣ ሰኔ 12

### ሀ. የአምላክ ታማኝ አገልጋዮች ሞት ምንም ይሁን ምን ምንጊዜም ምን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን? መዝሙር 116:15 ለዚህ አንድ ምሳሌ ጥቀስ።

"ኤልሳዕ ጌታውን በእሳት ሠረገላ አልተከተለም። ጌታ ለብዙ ጊዜ እንዲታመም ፈቀደ። በድካሙና በስቃዩ ጊዜ እንኳ እምነቱ እንደ ፀና ቆየ። የእግዚአብሔርን ተስፋ አጥብቆ ያዘ። መጽናናትንና ሰላምን የሰማይ መልዕክተኞች አመጡለት። . . . በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት እየበረታ ሄደ። ሞት ጥሪውን ሲያሰማ ከሥራው ለማረፍ ዝግጁ ነበር።"—Prophets and Kings, pp. 263, 264.

### ለ. የሱስ ከመምጣቱ በፊት በቢታንያ ምን ነገሮች ተከናውነዋል? የሱስ ሲደርስ ሌላ ማን እዚያ ነበር? ዮሐንስ 11፡17-19

"ክርስቶስ ወደ አልዓዛር ፈጥኖ ያልሔደበት ሌላው ምክንያት በእርሱ ለማያምኑት ሰዎች በመራራት ነው። የዘገየበት ምክንያት አልዓዛርን ከሞት በማስነሳት ልበ ደንዳናና ተጠራጣሪ ለሆኑት ሰዎች እርሱ «ትንሣኤና ሕይወት» መሆኑን እንዲያውቁ ሌላ እድል ለመስጠት ነበር። የሱስ ከእሥራኤል ቤት ተለይተው እንደ ጠፉ በጎች ስለሚንከራተቱት ምስኪን ሰዎች ገና ተስፋ አልቆረጠም ነበር። የሱስ እነዚህ ሰዎች ንስሐ ባለመግባታ ቸው ልቡ ተጨነቀ። የተበላሸውን የሚያድስ፣ ሕይወትንና ዘላለማዊነትን የሚሰጥ እርሱ ብቻ መሆኑን እንዲያውቁ በምህረቱ አንድ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሰጣቸው አሰበ። ይህ ማስረጃ ካህናቱ አጣምመው ሊተረጉሙት የማይችሉ ነበር። ይህ ነበር የሱስን ወደ ቢታንያ ከመሔድ እንዲዘገይ ያደረገው። ይህ አልዓዛርን ከሞት የማስነሳት የተአምር ሁሉ ተአምር የሱስ ስለ ሥራው የእግዚአብሔር ሙሉ ድጋፍ እንዳለው የታየበትና መለኮታዊነቱንም ያስመሰከረበት ተአምር ነው።"—The Desire of Ages, p. 529.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች አርብ፣ ሰኔ 13

1. የአልዓዛር ቤተሰብ አባላት እነማን ነበሩ?
2. የሱስ የወዳጆቹን ጥያቄ ወዲያውኑ ያልፈጸመው ለምንድን ነው?
3. ደቀ መዛሙርቱ ለክርስቶስ አመለካከት ምን ምላሽ ሰጡ?
4. የክርስቶስ አማኞች ሞትን እንዴት ሊመለከቱት ይገባል?
5. ክርስቶስ አልዓዛር እንዲሞት የፈቀደው ለምን ዓላማ ነው?

ሰንበት፣ ሰኔ 21፣ 2017

13ኛ ትምህርት

# ትንሳኤ እና ህይወት

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "የሱስም። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። (ዮሐንስ 11፡25)።**

**ለንባብ የተመረጠዉ መጽሐፍ፡** Selected Messages**, bk. 1, pp. 296–300.**

*"ለሚያምን ሰዉ ሞት ከባድ ነገር አይደለም። ክርስቶስ ሞት የአጭር ጊዜ ጉዳይ መሆኑን ይናገራል። . . . ለክርስቲያን ሞት የእንቅልፍ፣ በጨለማ ዝምታ የሰፈነበት ጥቅት ጊዜ ነው። ሕይወቱ ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ተሰውሮአልና።"*—The Desire of Ages, p. 787.

## 1. የሱስ በቢታንያ — እሁድ፣ ሰኔ 15

### ሀ. ማርታ የሱስ ወደ ቢታንያ እንደሚመጣ ስትሰማ ምን አደረገች? ምን እምነት ነበራት? ዮሐንስ 11፡20-22

*"ከሐዘንተኞቹ መካከል አንዳንዶቹ በየሩሳሌም ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸውና ከሟቹ ቤተሰብ ጋር ዝምድና የነበራቸው ነበሩ። ከነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ክርስቶስን አምርረው የሚጠሉ ነበሩ። ክርስቶስ ሐሳባቸውን ስለሚያውቅ ወዲያውኑ ማንነቱን አላሳወቀም።*

*"በክፍሉ ውስጥ አብረዋት የነበሩት ሰዎች ሳይሰሙ የየሱስ መምጣት በምስጢር ለማርታ ተነገራት። . . .*

*"ማርታ ልብዋ በሚጋጩ ስሜቶች እየታወከ ጌታን ለመገናኘት ገሰገሰች። ስሜቱ ጎልቶ በሚታይበት በጌታ ፊት ላይ ምንጊዜም የማይጠፋው የርህራሄና የፍቅር ስሜቱ ታያት። በእርሱ የነበራት እምነት የማይናወጥ ቢሆንም የሱስ ያፈቅረው ስለነበረው ውድ ወንድምዋ ታስብ ነበር። ክርስቶስ ቀደም ብሎ ባለመምጣቱ የሐዘን ስሜት እየተናነቃት አሁንም ቢሆን እነርሱን ለማጽናናት አንድ ነገር ማድረግ እንደሚችል ተስፋ በማድረግ «ጌታ ሆይ! አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባልሞተም ነበር» አለችው። በሐዘንተኞቹ ሁካታ መካከል እህትማማቾቹ እነዚህን ቃላት በመደጋገም ይናገሩ ነበር።*

*"የሱስ በመለኮታዊና በሰብአዊ ርህራሄ ስሜት በሐዘንና በጭንቀት የዛለውን የማርታን ፊት ተመለከተ። ማርታ ያለፈውን ሁኔታ የመዘርዘር ዝንባሌ ሳይኖራት ሁሉንም ነገር «ጌታ ሆይ! አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድሜ ባልሞተም ነበር» በሚሉ የሐዘን ቃላት ገለጸችው። የፍቅር ገጽታውን እየተመለከተች «አሁንም የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ ዐውቃለሁ» አለች።*—The Desire of Ages, pp. 529, 530.

## ሀ. የሱስ ለማርታ ምን አረጋገጠላት? ዮሐንስ 11፡23 በዚህም ምን ተረዳች? ዮሐንስ 11፡24

*“የሱስም “ወንድምሽ ከሞት ይነሣል» በማለት እምነትዋን አጠናከረላት። የክርስቶስ መልስ ቅጽበታዊ ለውጥ ተስፋ የማድረግ ስሜትን የሚቀሰቅስ አልነበረም። ይህ የየሱስ መልስ የማርታን አስተሳሰብ ከጊዜያዊዩ የወንድምዋ ከሞት መነሳት ባሻገር ወደ ጻድቃን ትንሣኤ እንዲያተኩርአደረገው። የሱስ ይህን ያደረገበት ምክንያት የአልዓዛር ከሞት መነሳት የሞቱ ጻድቃን ሁሉ ከሞት የሚነሱ ለመሆኑ ማረጋገጫ መሆኑንና ይህም የሚከናወነው በአዳኛችን ኃይል የመሆኑን እርግጠኛነት እንድትረዳ ለማድረግ ነበር።*

## ለ. የሱስ ማርታ የነበራትን እምነት እውቅና የሰጠው በምን ቃል ነው? ዮሐንስ 11:25፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡12

*“አሁንም እምነትዋን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ ሲል የሱስ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ» ሲል ገለጸላት። የክርስቶስ ሕይወትነት ከጥንት ከመሠረቱ ከራሱ የመነጨ እንጅ በብድር ወይም በውሰት ከሌላ የተገኘ አይደለም። «የእግዚአብሔር ልጅ ያለው ሕይወት አለው» 1ዮሐ.5:12። የክርስቶስ መለኮታዊነት ለምዕመናን የዘላለም ሕይወት ማግኛ ዋስትና ነው።”*—Ibid.

## ሐ. ከመቃብር ባሻገር ስላለን ተስፋ መሠረት የሆነው የትኛው ተስፋ ነው? የማርታ እምነት ከክርስቶስ ተአምር ጋር ምን ግንኙነት አለው? ዮሐንስ 5:26፤ 11:26፣ 27

*“ከዚህ ላይየሱስ ዳግመኛ የሚመጣበትን ጊዜ ያስታውሳል። በዚያን ጊዜ የሞቱ ጻድቃን ይነሳሉ፣ በሕይወት ያሉ ጻድቃንም ሞትን ሳያዩ ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት በማስነሳት የሠራው ተአምር የሞቱ ጻድቃንን ትንሣኤ ያመለክታል። የሱስ በቃሉም ሆነ በተግባሩ የትንሣኤ ሥልጣን ያለው መሆኑን ገለጸ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በመስቀል ላይ የሚሞተው አምላክየሞትን ቁልፍ በመያዙና የመቃብር አሸናፊ በመሆኑ የዘላለም ሕይወት ለመስጠት ያለውን መብትና ኃይል አረጋገጠ።”*—Ibid.

## ሀ. በሐዘን የተደቆሰችውን የማርያምን ድርጊትና ቃል ግለጽ። ዮሐንስ 11፡28-32

## ለ. የሱስ ማርያምና አንዳንድ አይሁዳውያን ሲያለቅሱ ሲመለከት ምን አደረገ? ለምንስ? ዮሐንስ 11፡33-35

"«የሱስ እርስዋ ስታለቅስና አብረዋት የመጡትም አይሁዳውያን ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ በመንፈሱ አዝኖ ታወከ።» የሱስ ከዚያ የተሰበሰቡትን ሰዎች ልብ አነበበ። ከዚያ ከነበሩት ሰዎች መካከል ብዙዎቹ የገለጹት የሐዘን ስሜት ለማ ስመሰል እንጅ ከልባቸው አለመሆኑን ተመለከተ። ከሕዝቡ ጋርተቀላቅለው ልባዊ ያልሆነ የሐዘን ስሜት ይገልጹ የነበሩት ሰዎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታላቅ ተአምር የሚሠራውን ሰው ብቻ ሳይሆን ከሞት የሚነሳውንም ጭምር ለመግደል እንደሚያስቡ ያውቅ ነበር። ክርስቶስ የግብዝነታቸውን ካባ ከላያቸው አንስቶ በመጣል ሊያጋልጣቸው ይችል ነበር። ነገር ግን የጽድቅ ቁጣውን ከመግለጽ ተቆጠበ። በሐዘን በእግሩ ሥርለተንበረከከችው እውነተኛ አማኝ ሲል ተወው እንጂ ሐቁን ይፋ ማውጣት ይችል ነበር።

"የሱስ «የት ነው የቀበራችሁት?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ «ጌታ ሆይ! ና እይ» አሉት። ከዚያ ቀጥሎ ሁሉም ወደ መቃብሩ ሔዱ። አልዓዛር በጣም ተወዳጅ ስለነበር እህቶቹ አምርረው ሲያለቅሱና ወዳጆቹም ከሟቹ እህቶች ጋር በእንባ ሲራጩ ማየት በጣም አሳዛኝ ትእይንት ነበር በዚህ አስከፊ ሰብአዊ ስቃይ ምክንያትና የዓለም አዳኝ በአጠገባቸው እያለ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ስለሞተ ሰው ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ "የሱስም እንባውን አፈሰሰ።»

"ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም የሱስ ሰብአዊ ባሕርይን ስለተላበሰ በሰብአዊ ሐዘን ልቡ ተነካ። ለሚሰቃዩ ሁሉ ልቡ ርህሩህና አዛኝ ነው። ከሚያለቅሱ ጋር ያለቅሳል፣ ከሚደሰቱም ጋር ይደሰታል።"—The Desire of Ages, p. 533.

## ሐ. በየሱስ ሕይወት ውስጥ ይህ አጋጣሚ ለእኛ ምሳሌ የሚሆንልን እንዴት ነው? ሮሜ 12፡15

"አስደናቂው የክርስቶስ ምሳሌ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲሆን ስሜቶቻቸውን የተካፈለበት፣ ከሚያለቅሱት ጋር እያለቀሰ፣ ከሚደሰቱት ጋር አብሮ የሚደሰትበት ወደር የለሽ ርህራሄ፣ በቅንነት እርሱን በሚከተሉት ሁሉ ባህሪይ ላይ ጥልቅ ተጽእኖ ሊኖረው ይገባል። በዚያን ጊዜ በደግነት ቃላትና ድርጊቶች ለደከሙ እግሮች መንገዱን ቀላል ለማድረግ ይጥራሉ።"—The Ministry of Healing, pp. 157, 158.

## ሀ. የሱስ በዙሪያው ላሉት ምን ትእዛዝ ሰጣቸው? ዮሐንስ 11፡39 (የመጀመሪያ ክፍል)። ማርታ ምን ምላሽ ሰጠች እና የሱስ ምን አላት? ዮሐንስ 11፡39 (የመጨረሻው ክፍል)።

*"ሁል ጊዜ አምላክ አንድ ነገር ለማድረግ ሲነሳ ሰይጣን የሚቃወም ሰው ያቀርባል። የሱስ «ድንጋዩን አንሱት» አለ። በተቻለ መጠን ለእኔ ሥራ ሁኔታዎችን አመቻቹልኝ ማለቱ ነው። ማርታ ግን በቀና አስተሳሰብዋ ጽኑ አቋም ነበራት። በመፍረስ ላይ የነበረው የወንድምዋ አካል እንዲታይፈ.ቃደኛ አልነበረችም። ሰብአዊ ልብ የክርስቶስን ቃል ለማስተዋል ዳተኛ በመሆኑ ማርታ የክርስቶስን ተስፋ ትክክለኛ ትርጉም በእምነት መቀበል አዳገታት።*

*"«ካመንሽ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብየሽ አልነበረምን?» በማለት የሱስ ርጋታ በተሞላበት መንፈስ ማርታን ገሰጻት። ይህንም ሲል ለምን በእኔ ኃይል ትጠራጠሪያለሽ፣ እኔ አስፈላጊ ነው ከምለው ጋርየሚጻረር አስተሳሰብ ለምን ይኖርሻል፣ ቃሌ በእጅሽ ሳላለልሽ ካመንሽ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ማለቱ ነበር። ተፈጥሮአዊ ችግር የኃያሉን አምላክ ሥራ ሊገታ አይችልም። ጥርጣሬና አለማመን እንደ ትሕትና አይቆጠሩም። እውነተኛ ትሕትናና ራስን ማስገዛት ማለት ያለ አንዳች ጥርጣሬ በክርስቶስ ቃል ማመን ማለት ነው።*

*"«ድንጋዩን አንሡት» አለ የሱስ። ክርስቶስ ድንጋዩን ተነስ ብሎ ቢያዝዘው ትእዛዙን ባከበረለት ነበር። ወይም በአጠገቡ የነበሩትን መላእክት ድንጋዩን እንዲያነሱት ሊያዝዛቸው ይችል ነበር። ነገር ግን ድንጋዩ በሰው እጅ መነሳት ነበረበት። ይህን በማድረጉ የሱስ ሰብአዊ ፍጡራን ከመለኮት ጋር መተባበር እንዳለባቸው አሳየ። ሰው ሊሠራው የሚችለውን ነገርመለኮት እንዲሠራው መጠየቅ የለበትም። እግዚአብሔር የሰውን ትብብርይሻል። ሰው በተሰጠው ኃይልና ችሎታ እንደሠራ መጠን እግዚአብሔር ይተባበረዋል፣ ያበረታዋልም።"*—The Desire of Ages, p. 535.

## ለ. ዛሬ አለማመናችንን በእርጋታ የሚገስጸው የትኛው የክርስቶስ ቃል ነው? ዮሐንስ 11፡40

*"ብዙዎች ሕያው እምነት የላቸውም። የእግዚአብሔርን ኃይል በበለጠ ሆኔታ የማያዩት ለዚህ ነው። ድክመታቸው የአለማመናቸው ውጤት ነው። . . . ያቅዳሉ እና ያዘጋጃሉ፣ ነገር ግን ጥቂት ይጸልያሉ፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እውነተኛ እምነት በጣም ትንሽ ነው። እነሱ እምነት እንዳላቸው ያስባሉ፣ ነገር ግን የሚያሳዩት ጊዜያዊ ሞቅታ ብቻ ነው። የገዛ ፍላጎታቸውን ወይም አምላክ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለመሆኑ በትክክል ማስተዋል ባለመቻላቸው፣ ልመናቸውን በጌታ ፊት በትጋት በማቅረብ አይጸኑም።"*—Christ's Object Lessons, pp. 145, 146.

## 5. የሱስ አልዓዛር ከሞት አስነሳው | ሐሙስ፣ ሰኔ 19

### ሀ. የሱስ ከመቃብሩ አጠገብ ሆኖ ምን ጸሎት አቀረበ? ዮሐንስ 11:41፣ 42

"ክርስቶስ ባዘዘው መሠረት ድንጋዩ ተነሳ። ሁሉም ነገር ግልጽና ይፋ ሆኖ ተከናወነ። ምንም ዓይነት የማጭበርበር ነገር እንዳልተደረገ ሁሉም የማየት እድል ነበራቸው። አልዓዛር በሞት ኃይል ቀዝቅዞና ጸጥ እንዲል ተደርጐ በዋሻው መቃብር ውስጥ ይታይ ነበር። አልቃሾቹ ጸጥ ብለው በመቃብሩ ዙሪያ በመሰብሰብ የሚሆነውን ይጠባበቁ ነበር። …

"አሁን ክርስቶስ እግዚአብሔር አባቱ መሆኑን በመግለጽ በሙሉ ልብ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አሳወቀ።"—The Desire of Ages, pp. 535, 536.

### ለ. የሱስ አልዓዛርን ያስነሳው በምን ቃል ነው? ዮሐንስ 11፡43 ወዲያው ምን ሆነ? ዮሐንስ 11፡44


"[የክርስቶስ] ድምጹ ግልጽና ምንም ነገር የማያግደው ስለነበረ የሙቱን ጆሮ በስቶ ገባ። እርሱ በተናገረ ጊዜ መለኮት በሰብአዊነት ውስጥ ቦግ አለ። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ክብር በበራው ፊቱ ላይ ኃይል እንደነበረው ለማረጋገጥ ቻሉ። ዓይን ሁሉ ወደ ዋሻው በር አተኮረ፣ ጆሮም ማንኛውንም ድምጽ ለማዳመጥ ተዘጋጀ። ከዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ የክርስቶስን መለኮታዊነት ማስረጃ ለማየት በከፍተኛ ጉጉት ይጠባበቁ ነበር። ይህ ማስረጃ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ይህ ካልተሳካ ግን ተስፋ ለዘላለም ተደመሰሰ ማለት ነበር።

"ጸጥ ባለው መቃብር ውስጥ እንቅስቃሴ ታየ፣ ሞቶ የነበረው አልዓዛር በመቃብሩ በር ላይ ቆመ። … አሁንም በድጋሚ የሱስ ሰብአዊ ሠራተኛ ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር እንዳለበት አሳያቸው። ሰው ለሰው መሥራት አለበት። አልዓዛር ተፈትቶ በሕዝቡ ፊት የቆመው በመካከለኛ እድሜ ላይ እንዳለ ጤነኛ ሰው እንጅ እንደ ደከመና እጅና እግሮቹ እንደሚንቀጠቀጡ ሕመምተኛ ሆኖ አልነበረም። ዓይኖቹ በማስተዋልና ለአዳኛችን በነበረው ፍቅር ይንጸባረቁ ነበር። በታላቅ አክብሮት በክርስቶስ እግር ሥር ወድቆ ሰገደ።"—Ibid., p. 536.

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች | አርብ፣ ሰኔ 20

1. የአልዓዛር እህቶች በየሱስ ላይ ያላቸውን እምነት ግለጽ።
2. የሱስ ለማርታ፣ ለማርያም እና ለሁሉም አማኞች ምን ቃል ገብቷል?
3. የሱስ ያለቀሰው ለምንድን ነው?
4. በዚህ ተአምር የሰው ልጅ ከመለኮት ጋር እንዴት ተባበረ?
5. ለየሱስ ጥሪ አልዓዛር የሰጠውን ምላሽ ግለጽ።

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታዎች




## ሰንበት፣ መጋቢት 27

### በፕሮክሆሮቭካ ፣ ሩሲያ ውስጥ ቤተክርስቲያኑ እንደገና መገንባት

በዓለም ላይ በትልቁ አገር እያደገ ያለው ሥራ አካል ይሁኑ! (ገጽ 4 ተመልከት)



## ሰንበት፣ ሚያዝያ 25

### የዓለም ተልዕኮዎች

ገና የሚቀሩ ብዙ አዳዲስ ቦታዎች አሉ፣ ስለዚህ ይህን መለኮታዊ ተግባር ለመፈጸም እንደግፍ! (ገጽ 25 ተመልከት)




## ሰንበት፣ ግንቦት 30

### በታሚል ናዱ፣ ሕንድ ውስጥ ሁለት የጸሎት ቤቶች ግንባታ

ደቡብ ህንድ ወንጌልን በጣም ትፈልጋለች፤ አሁን ለውጥ ለማምጣት ለመርዳት ዕድላችን ነው (ገጽ 46 ይመልከቱ)